# እውነት


እውነት - ቅጽ 2፣ ቁጥር 1 | የማይሸጥ | እውነትም አርነት ያወጣችኋል/ዮሐ8፡32/ | ወርኃ መስከረም 1995 ዓ. ም.


## ኢዮሣፍጥና ዓለማዊነት /2ዜና መዋዕል ምዕራፍ 17-20/

ከሮብአም ዘመን ጀምሮ ከተለያዩ በኋላ ስለእስራኤል ቤትና ስለይሁዳ ቤት የተጻፈውን በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ስንመለከት በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ያለአንዳች ችግር መገንዘብ እንችላለን፡፡ ከኢዮርብዓም እስከ ሆሴዕ ድረስ ያሉት የእስራኤል የነገሥታት ስም ዝርዝር በአጠቃላይ በጌታ ፊት ጨለማና አሳዛኝ የሆነ ክፉ ሥራ በሠሩ ክፉ አድራጊዎች የተሞላ ሆኖ እናገኛለን፤ በእስራኤል ከነገሡት የተለየ ታሪክ ያለውን ለማግኘት መሞከር ከንቱ ድካም ነው፤ በጅማሬው ከፍ ያለ ትጋትንና ኃይልን በማሳየት አምልኮተ ጣኦትን ያስወገደው «ኢዩ» እንኳን በተከታታይ ልቡ በእግዚአብሔር ፊት ቅን አለመሆኑን አረጋግጧል፤ በእርግጥ ከባቢሎን ወዲያ ማዶ እስከተወሰዱና በአሕዛብ መካከል እስከተበተኑበት ጊዜ ድረስ በመላው እስራኤል ላይ የአምልኮተ ጣኦት ጥቁር ደመና ሰፍኖ ነበር፡፡

በይሁዳ ግን እንዲህ አልነበረም፤ እዚህ ደስ የሚያሰኝ ልዩነት እናያለን፤ እነዚህም ጌታ ስለባሪያው ስለዳዊት ሲል በኢየሩሳሌም ካኖረው መብራት የሚፈነጥቁ አስደሳች ጮራዎች ናቸው፤ እንደ ኢዮስያስ፣ አሳ፣ ኢዮአስና ህዝቅያስ የመሳሰሉት ልባቸውን ለቤተመቅደሱ አገልግሎት ያተጉና በጊዜያቸው ላይ የተቀደሰ ተጽዕኖ ያሳደሩ ሰዎችን ታሪክ ማጥናት ለነፍስ ደስታን ይሰጣል፡፡

አሁን ጌታ የሚያስፈልገንንና የሚተርፈንን ትምህርት እንደሚሰጠን በማመን ከእነዚህ ለየት ያለ ታሪክ ካላቸው የተባረኩ ሰዎች በአንዱ ንጉሥ በኢዮሣፍጥ ታሪክ ላይ አጠር ያለ ቆይታ እናደርጋለን፡፡

የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥን የምናገኘው በሁለተኛ ዜና መዋዕል ምዕራፍ 17 ላይ ነው፤ በዚህም ምዕራፍ እግዚአብሔር ለባሪያው መንግሥትን ሲያደራጅለትና የእግዚአብሔር ሕዝብም ለመንግሥቱ እውቅና ሲሰጥ እናገኛለን፤ የኢዮሣፍጥ ቀዳሚ ሥራው ራሱን «በእስራኤል ላይ ማጠንከር» ነበር፤ ይህም በትኵረት ልብ ልንለው የተገባ ነው፤ እስራኤልና የእስራኤል ንጉሥ ምንጊዜም ለኢዮሣፍጥ ልብ ወጥመድ ነበሩ፤ ይሁንና ኢዮሣፍጥ ገና ከአነሳሱማለትም ገና በጅማሬው ወቅት ላይ ከእስራኤል ኃይል ለመጠንቀቅ መንግሥቱን መመሸግ ችሏል፡፡ ይህን የመሰለው ሁኔታዎች በክርስቲያኖች ታሪክ ውስጥም ብዙውን ጊዜ ይታያሉ፡፡ ከጊዜ በኋላ በክርስቲያኖች ሕይወት ላይ ታላቅ ወጥመድ መሆናቸውን ያስመሰከሩ ክፉቶች እነዚያ በመጀመሪያ ላይ እንዳይደርሱ በማሰብ ከበድ ያለ ጥንቃቄ የተደረገባቸው ናቸው፡፡

ከልባችን የዝንባሌና የችሎታ እውቀት መጨመር ጋር ተግቶ መጠንቀቅ ሲታከልበት አስደሳች ነገር ነው፤ ይሁንና የሚያስፈራ ነገር አለ፤ ምክንያቱም ሁልጊዜ ይህ አይሆንምና፤ እንዳውም ክርስቲያኖች ከጊዜ በኋላ አስቀድሞ አእምሮአቸውን ይዘገንናቸው በነበረው ነገር ውስጥ ጠልቀውበት የምናየው ምንኛ ብዙ ጊዜ ነው! እንዲህ ማለታችን ግን ምናልባት ከሕግ አክራሪነት መንፈስ የመነጨ ተደርጎ ሊታይ ይችል ይሆናል፤ ነገር ግን በምትኩ በሩቁ ክፉትን ለይቶ ማወቅ ከሚችል ንቁና ጠንቃቃ ህሊና የመነጨ ተደርጎ መታሰብ አይኖርበትምን? በመሆኑም የአመለካከት መስፋት ውጤቱ ለክፉት ግዴለሽ የሚሆን መንፈስ


*(ወደ ገጽ 10 ይዞራል)*


## በውስጥ ገጾች



| | |
|---|---|
| መልእክተ እውነት | 2 |
| ካህናችን | 2 |
| ዳግመኛ መወለድ | 3 |
| ቤተክርስቲያን በአጥቢያ ገጽታዋ | 5 |
| የጥያቄዎቻችሁ መልሶች | 16 |
| ጸጋው ሲጎድል | 19 |



## ለኢየሱስ ስፍራ አላችሁን?

«በዚያም ሳሉ የመውለጃዋ ወራት ደረሰ፤
የበኩር ልጅዋንም ወለደች፤
በመጠቅለያም ጠቀለለችው በእንግዶችም
ማደሪያ ስፍራ ስላልነበራቸው በግርግም
አስተኛችው»
/ሉቃ.2፤6-7/

ወንጌላዊው ሉቃስ ስለጌታችን ስለኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በጻፈበት ክፍል ይህን ቃል መዝግቦልናል፡፡ ጌታ የተወለደው ዓለሙ ሁሉ እንዲጻፍ ከአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዝ በወጣበት ወራትና ቄሬኔዎስ የተባለው ሰው በሶርያ አገር ገዥ በነበረበት ጊዜ ነው፡፡ የጌታችን እናት ማርያም ትኖር የነበረው በገሊላ ውስጥ በምትገኘው በናዝሬት ከተማ ቢሆንም ለምዝገባ ከዮሴፍ ጋር ቤተልሔም ወደምትባል ከተማ መጥታ ነበር፤ በዚያን ጊዜ የመውለጃዋ ወራት ደረሰና የበኵር ልጅዋን ወለደች፡፡ ሆኖም በቤተልሔም ውስጥ የእንግዶች ማደሪያ ቢኖርም ለሰማያዊው እንግዳ ግን በእንግዶች ማደሪያ ስፍራ አልተገኘለትም፡፡ ለምዝገባ ከተለያዩ ክፍለ ሀገራት የመጡ ሰዎች በእንግዶች ማደሪያ ስፍራ አግኝተዋል፤ ሕፃኑ ኢየሱስ ግን ስፍራ ስላልተገኘለት እናቱ በመጠቅለያ ጠቀለለችውና በግርግም አስተኛችው፡፡

የቤተልሔም ባለሥልጣናትና የምዝገባው ማዕከል ኃላፊዎች ክቡራን ለሚባሉ ምድራውያን እንግዶች ስፍራ ቢኖራቸውም ከሰማይ ለመጣው


*(ወደ ገጽ 7 ይዞራል)*

# እውነት ጋዜጣ

«እውነትም አርነት ያወጣችኋል» በሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ላይ ተመሥርቶ የሚታተም የክርስቲያኖች ጋዜጣ

ዋና አዘጋጅ፡ መዘምር በለጠ

ም/ዋና አዘጋጅ፡ ደጉ ምሕረቴ


## መልእክተ እውነት

# አዲስ በማለቱ ፊተኛውን አስረጅቷል

/ዕብ. 8፡13/

እግዚአብሔር በተለያዩ ዘመናት ከሰው ልጅ ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ሰውን የሚመራበትና የሚያስተዳድርበት የተለያየ መርህ እንዳለው ከመጽሐፍ ቅዱስ እንማራለን፤ በተለያዩ ክፍለ ዘመናት ለሰው የሰጣቸው የተለያዩ ኪዳናትም አሉ፤ በጣም የታወቁት ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን ናቸው። ከላይ በርእስ መልክ የቀረበው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እነዚህ ሁለቱን ኪዳናት «አዲስ» እና «ፊተኛ» በማለት ገልጿቸዋል፤ በዚህ የመልእክተ እውነት ንባብ ትኵረት የምናደርገው በአዲስ ኪዳን ዘመን የብሉይ ኪዳን ሥርዓቶችና መመሪያዎች በፊደላዊ ቅርጻቸው ለክርስቲያኖች መመሪያ ሊሆኑ እንደማይችሉ በመግለጽ ላይ ይሆናል።

በዕብ.8 ውስጥ ከፊተኛው ይልቅ እጅግ ስለሚሻለው ስለ አዲሱ ኪዳን የተመዘገበ ትምህርት እናገኛለን። ጸሐፊው በኤር31፡31-34 ላይ ስለአዲስ ኪዳን የተነገረውን የትንቢት ቃልም ሙሉ ንባቡን በማስፈር በማስረጃነት ይጠቅሳል። ይህም የትንቢት ቃል «እነሆ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል…» የሚል ነው። ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ600 ዓመታት አስቀድሞ በነበረው በኤርምያስ ዘመን ወደፊት ስለሚመጣ አዲስ ስለሆነ ኪዳን እግዚአብሔር ሲናገር በዚያው በኤርምያስ ዘመን የፊተኛውን ኪዳን እንዳስረጀው እንረዳለን፤ ስለሆነም ሐዋርያው ጥቅሱን ከጠቀሰ በኋላ «አዲስ በማለቱ ፊተኛውን አስረጅቷል» ለማለት ተችሎታል፤ በመቀጠል የፊተኛውን ኪዳን መጨረሻ ሲናገር «አሮጌና ውራጅ የሆነውስ ሊጠፋ ቀርቦአል» ይላል/ዕብ8፡13/።

በእውነት ጋዜጣ ባለፉት እትሞች ላይ የአዲስ ኪዳን አገልግሎትን በተለይም የአዲስ ኪዳን አምልኮን በተመለከተ ከፊተኛው ኪዳን ማለትም ከብሉይ ኪዳን ፊደል በፊደል የምንወስደው መመሪያ እንደሌለ ተገልጧል፤ የአምልኮ መሪ፣ የመዘምራን ቡድን፣ ለአገልግሎት የሚለበሱ የተለዩ አልባሳት፣ የሙዚቃ መሣሪያዎች፣ እና በዝማሬ ወቅት የሚታይ ዝላይና ጭፈራ በአዲስ ኪዳን አምልኮ ውስጥ ቦታ እንደሌላቸው በተደጋጋሚ ተብራርቷል፤ ሆኖም ከዚህ ጋር ተያይዞ «እኛ ክርስቲያኖች የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ስለምንቀበል በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተገለጡትን እነዚህን ሥርዓቶች በአምልኮአችንና በጠቅላላ አገልግሎታችን መጠቀሙ ምን ችግር አለው?» የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በአዲስ ኪዳን ዘመንና ወደፊት በሚመጣው ዘመን ስላለው ነገር በምሳሌና በትንቢት ይናገራሉ፤ የያዙአቸው ሕግጋትም በዚያው በኦሪት ዘመን ፊደል በፊደል ተፈጻሚነት ነበራቸው። በአዲስ ኪዳን ግን «በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን፤ ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል» ተብሎ ተነግሯል/2ቆሮ.3፡6/። በመሆኑም የብሉይ ኪዳን አገልግሎት በዘመኑ የከበረ ቢሆንም እንኳን አሁን እንደተሻረ ተጽፎልናል፤ «ያ ይሻር የነበረው በክብር ከሆነ ጸንቶ የሚኖረውማ እጅግ ይልቅ በክብር ሆኖአልና» ይላል/ቁ11/፤ እንዲሁም «ብሉይ ኪዳን ሲነበብ ያ መጋረጃ ሳይወሰድ እስከዛሬ ድረስ ይኖራልና፤ በክርስቶስ ብቻ የተሻረ ነውና»/ቁ.14/ተብሏል። «እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም» ብሎ ጌታ የተናገረው ቃልም ቢሆን/ማቴ5፡17/ የብሉይ ኪዳን አገልግሎት ፊደል በፊደል በአዲስ ኪዳን ሊኖር እንደሚችል የሚያስረዳ አይደለም። ጌታ «ሕግንና ነቢያትን ሊሽር» ባይመጣም «ሊፈጽም» መጥቷል፤ ይህም ማለት በብሉይ ኪዳን ጥላና ምሳሌ የሆኑትን ወደ አማናዊ ፍጻሜ ሊያመጣ፣ እንዲሁም የሚቀሩትን ሊያስቀር የሚተኩትን ሊተካ የሚጨመርባቸውን ሊጨምር ባጠቃላይ በአዲስ ኪዳን ሊሆን በሚገባው መልኩ ሊፈጽም መጥቷል ማለት ነው። ይህን ጥቅስ በተመለከተ ሰፊ ማብራሪያ ለማግኘት እውነት ጋዜጣ ቁ.5 ላይ በአንባብያን ዓምድ በገጽ 16 እና 17 ይመልከቱ።

አምልኮን በተመለከተም በመንፈስና በእውነት የሆነው የአዲስ ኪዳን አምልኮ በኢየሩሳሌም ይፈጸም በነበረው የብሉይ ኪዳን አምልኮ/ስግደት/ የተተካ ወይም የተቀየረ መሆኑን ያስተማረው ራሱ ጌታ ኢየሱስ ነው/ዮሐ4፡21-24/። ስለዚህ የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓቶችንና ልምዶችን በፊደላዊ ቅርጻቸው መውሰድ አይቻልም። የተወሰኑትን ወስዶ የተወሰኑትን ማስቀረትም ትክክል አይደለም፤ የሌዋውያን መዘምራን አገልግሎትንና የዜማ ዕቃዎችን ፊደል በፊደል ወስዶ የእንስሳት መሥዋዕትን፣ የቃልኪዳኑ ታቦትንና የመሳሰሉትን መተው አይቻልም። አዲስ ኪዳን እግዚአብሔር በመንፈስ የሚገለገልበት ዘመን ነው። ብሉይ ኪዳንን በተመለከተ ግን «አዲስ በማለቱ ፊተኛውን አስረጅቷል» ተብሎ የተጻፈውን ቃል ማስተዋል ይገባል።

## ካህናችን

ካህናችን መድኅናችን
ልትቆምልን ከጎናችን
ለደካማ ኀዘንተኞች
አጽናኝ ላጣን ችግረኞች
በጉዟችን ለደከምን
የዓለም ዝለት ለተሰማን
የእግዚአብሔር ልጅ ደረስክልን፤
እንደ መልከ ጼዴቅ
ባለ ሹመት
ልታገለግል በልዑል ፊት
በመሐላ ተሾምክና
ተቀብተህ ሰው ሆንክና
የእኛን በደል ተሸክመህ
እመስቀል ላይ ወጣህና
ስለ እኛ ቃተትክና
በጣር በጭንቅ ማለድክና
አስታረቅኸን ካባትህ ጋር
በነፃነት እንድንኖር።
መኀተትህ መገፋትህ
እንደ በግ መነዳትህ
መሠቃየት መመታትህ
ዓላማህን ልትፈጽም ነው
እኛን ከሞት ልታድን ነው።

የህማም ሰው የመከራ
ደዌን የሚያውቅ የሚራራ
ስለ ሕዝቡ የሚማልድ
ታማኝ ካህን የሚወደድ።
ባለጠጋው ደሀ ሆኖ
ክቡር ሳለ ክብሩን ጥሎ
ለበጎቹ በግ የሆነ
እስከሞት የታመነ
ለሰው ልጆች ፍጹም ሰላም
የሰጣቸው ለዘላለም
ከአንተ በቀር ማን ነበረ?
ጠላቶቹን ያፈቀረ፤
ማን ነበረ ከሰው ወገን?
ሰላም እረፍት የሚሰጠን
ማን ነበረ ከመላእክት?
ስለ እኛ የሚቃትት
ከፍጥረታት የትኛው ነው?
ለ'ኛ መዳን የለመነው
የትኛው ነው የሞተልን
ከእግዚአብሔር ጋር ያስታረቀን
ባይኖር አይደል ከሰው ወገን
የእግዚአብሔር ልጅ የመጣልን
ቢጠፉ አይደል የሚያድነን
ጌታ ኢየሱስ የሞተልን
ያማለደን፤
ቢጠፉ አይደል የሚታደግ?
የታረደው የእግዚአብሔር በግ?

ካህናችን መሥዋዕታችን
ሁል ጊዜም ሊያማልደን
ዛሬም አለ በመቅደሱ
በግርማው ቀኝ በንጉሡ።
ደስታ ሐሴት ሰላም እረፍት
ተስፋ ክብር ጸጋ እውነት
የሆነልን፣ የበዛልን
ጉድለታችን የሞላልን
እርሱ በዚያ ስላለ ነው
እኛ በሕይወት የምንኖረው።

# ዳግመኛ መወለድ

የዮሐ3፡1-11

በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ዜጋ መሆን ይቻል ዘንድ ከእግዚአብሔር የተገኘ አዲስ ሕይወት ያለው ማንነት ያስፈልጋል፤ ይህም ሕይወት የሚገኘው ከሥጋ ልደት ሳይሆን በመንፈስ ከሚሆን ዳግመኛ መወለድ ነው፡፡ በሥጋ ከምድራዊ አባትና እናት እንወለዳለን፤ ዳግመኛ የምንወለደው ግን ከሰማያዊ አባት ከእግዚአብሔር ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ያልተወለደ ሰው በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ስፍራ የለውም፡፡

በዳግመኛ መወለድ የሚገኘው ልጅነት የእግዚአብሔር ልጅነት ነው፡፡ ይህን የእግዚአብሔርን ልጅነት የሚያገኙትም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የተቀበሉና በስሙ ያመኑ ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡ ዮሐንስ በወንጌሉ መጀመሪያ ላይ ስለ ኢየሱስ ሲጽፍ «የእርሱ ወደሆነው መጣ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም፤ <u>ለተቀበሉት</u> ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም» /ዮሐ1፡12/ ብሏል፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን የሚያስችለው ይህ እምነትም አፍአዊ ሳይሆን እውነተኛ የልብ እምነት ነው፤ የአፍ አማኞች ይህ የልጅነት ሥልጣን ሊኖራቸው አይችልም፤ ምክንያቱም ኢየሱስ የሰውን የልብ ሁኔታ ያውቃል፤ እንዲሁም እምነታችን አፍአዊ ይሁን ወይም እውነተኛ እርሱ በሚገባ ያውቃል፡፡

የእግዚአብሔር ልጅነትን ሥልጣን ስለሚያጐናጽፈን ስለዳግመኛ መወለድ ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተማረው ይህንኑ የልጅነት ሥልጣን የሚሰጠው ራሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ያስተማረውም በሌሊት ወደ እርሱ መጥቶ ለነበረው ኒቆዲሞስ ለተባለው አይሁዳዊ ነበር፡፡ በዮሐ3፡1-11 እንደተጻፈው የኒቆዲሞስ ማንነት በሚከተሉት አራት ነገሮች ሊገለጽ ይችላል፡፡

1. ኒቆዲሞስ ከፈሪሳውያን ወገን ነበር/ቁ.1/
2. ኒቆዲሞስ የአይሁድ አለቃ ነበር /ቁ.1/
3. ኒቆዲሞስ የሸመገለ ሰው ነበር /ቁ.4/
4. ኒቆዲሞስ የእስራኤል መምህር ነበር /ቁ.10/

እነዚህ አራቱም ነገሮች ኒቆዲሞስ ወደ ጌታ ከመምጣቱ በፊት በአይሁድ መካከል የነበሩት ስፍራዎች ናቸው፤ አዎን፡- ኒቆዲሞስ ፈሪሳዊ፣ የአይሁድ አለቃ፣ ሽማግሌና የእስራኤል መምህር ቢሆንም የእግዚአብሔር ልጅ ግን አልነበረም፤ እነዚህን አራት ነገሮች የአብርሃም ዘር ከሆኑት አይሁድ በመወለድና ባለው የኦሪት እውቀት አግኝቷቸው ይሆናል፤ እነዚህም ስፍራዎች እርሱን በሥጋ ሊያከብሩት የሚችሉ ስፍራዎች ሊሆኑ ይችላሉ፤ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ግን ስፍራ ሊያሰጡት አይችሉም፤ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ቦታ ለማግኘት ብቸኛው መንገድ ዳግመኛ መወለድ ነው፤ ኒቆዲሞስ ወደ ጌታ ሲመጣ በጌታ ልብ ውስጥ ስለ ኒቆዲሞስ ይታሰብ የነበረው ይህ እውነታ እንደ ነበረ በዚች ሌሊት ጌታ ለእርሱ ካስተማረው ትምህርት መረዳት ይቻላል፡፡

በዘመናት ሁሉ ሰውን የእግዚ አብሔር መንግሥት ዜጋ ሊያደርገው የሚችለው ዳግመኛ መወለድ እንጂ ፈሪሳዊነት እንዳልሆነ ሰዎች ሁሉ ሊረዱ ይገባል፤ «ፈሪሳውያን» ጌታችን በሚያስተምርበት ዘመን በእስራኤል ዘንድ የነበሩ አንድ የኦሪት ሃይማኖት ቡድን ናቸው፤ ከአይሁድ መካከል ተለይተው በሙሴ ሕግና በሽማግሌዎች ወግ አጥባቂ ነን የሚሉ ወገኖች ናቸው፡፡ ሰዱቃውያን ከሚባሉት ወገኖች የሚለዩት «የሙታን ትንሣኤ አለ፣ መልአክም መንፈስም አለ» ስለሚሉ ነው/ሐዋ.ሥ23፡8/፡፡ ሆኖም ይህ የሃይማኖት ቡድን ዳግመኛ ልደት የሌለበት ነው፡፡ በክርስትና ዓለምም የአንድ የሃይማኖት ቡድን ወገን በመሆን የእግዚአብሔር ልጅነት አይገኝም፤ ክርስትና በሥጋ ሐረገ ትውልድ ከወላጆች ወደ ልጆች የሚወረስ ወይም በአንድ የሃይማኖት ቡድን አባል በመሆን የምንኖረው ህይወት አይደለም፤ ክርስትና በዳግመኛ ልደት የእግዚአብሔር ልጅ ሆነን የምንኖረው ሕይወት ነው፡፡ ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት በክርስትና ስም ከሚጠራ ፈሪሳዊነት ወይም ቡድናዊነት ተለይቶ ዳግመኛ መወለድ ያስፈልጋል፡፡

በአሮጌው ተፈጥሮ ማለትም ከሥጋ ልደት ብቻ በተገኘ ባሕርይ ለረጅም ጊዜ እንዲኖሩ አንዳንዶችን አንቆ የያዘው ሌላው ነገር ደግሞ ምድራዊ ሥልጣን ነው፤ ኒቆዲሞስ የአይሁድ አለቃነቱ ወደ ኢየሱስ እንዳይመጣ ሊያዘገዩትና ሊጋርዱት ከሚችሉት ምክንያቶች አንዱ ሊሆን ይችላል፤ ሆኖም ይህንን ግርዶሽ አልፎ ወደ ኢየሱስ ሊመጣ በመቻሉ ምድራዊና ሥጋዊ ሥልጣንን ሳይሆን መንፈሳዊ የሆነውን የልጅነት ሥልጣን እንዴት ሊያገኝ እንደሚችል ተማረ፤ ስለዚህ በሃይማኖተኛውም ሆነ በዚህ በገሃዱ ዓለም የሚገኙ ምድራውያን ባለሥልጣናት ከያዙት ሥልጣን የሚበልጥ የእግዚአብሔር ልጅ የመሆን ሥልጣን እንዳለ አውቀው ወደ ኢየሱስ ሊመጡ ያስፈልጋል፡፡ ወደዚህ ወደ ከበረው የልጅነት ሥልጣን በእግዚአብሔር ጸጋ ይደርሱ ዘንድ የያዙትን ምድራዊ ሥልጣን ሊንቁት ይገባል፤ ወደዚህ ዘላለማዊ የልጅነት ሥልጣን ይገቡ ዘንድ የያዙት ምድራዊ ሥልጣን ጊዜያዊና ኃላፊ እንዲሁም በሰዎች የሚሻር መሆኑን አውቀው ወደ ኢየሱስ ለመምጣት መወሰን ይገባቸዋል፡፡

በዕድሜ ሽምግልና ምክንያትም ከኢየሱስ ጋር ለመቆጠር በማፈራቸው ዳግመኛ ሳይወለዱ ዘመናቸውን የሚጨርሱ ብዙዎች መሆናቸው የክርስቶስ ለሆኑት ሁሉ ልብን የሚነካ አሳዛኝ ነገር ነው፡፡ በዚህች ዓለም ሃይማኖታዊና ባህላዊ ሥርዓት እስኪሸመግሉ ድረስ ከኖሩ በኋላ ለዓመታት ከኖሩበትና ከአባቶቻቸው ከወረሱት ከዚያ የሰው ሥርዓት ተላቅቀው ወደጌታ መምጣት የተሳናቸው ስንቶች ናቸው? የኢየሱስ መሆን አዲስ ልጅነትን ሊያሰጥ እንደሚችል ባለማመናቸው ወደ እነርሱ የመጣውን የጸጋ ወንጌል ያልተቀበሉትስ ስንቶች ናቸው? ኒቆዲሞስ የአይሁድ አለቃነቱ ብቻ ሳይሆን ሽምግልናውም ሳያግደው ወደ ኢየሱስ መምጣቱ ለእንዲህ ያሉ ሰዎች ትምህርት ሊሆናቸው ይገባል፡፡ እነዚህ ሰዎች በሽምግልና ወደ ኢየሱስ ቢመጡና እሱን በመከተል የመጨረሻዋን ውድ ጊዜ ለጌታ ቢሰጡ ባለጠግነቱ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን ልጅነት በጸጋ ሊቀበሉ እንደሚችሉ አሁኑኑ ሊገነዘቡ ይገባል፤ የኢየሱስ መሆን በኅብረተሰብ ዘንድ «በስተርጅና!» እየተባለ እንደ ውርደት የሚቆጠር ቢሆንም በጌታ ዘንድ ግን በአዲስ ልጅነት የአዲስ ሕይወት ባለቤት የሚያደርግ የክብር ኑሮ መሆኑን ሊያውቁ ያስፈልጋል፤ በሌላ በኩል ደግሞ በሽምግልና ወይም በስተርጅና ወደ አንድ የሃይማኖት ጎራ መግባት የእግዚአብሔር ልጅነትን ሊያሰጥ የማይችል መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በስተርጅና ሃይማኖት መቀየር በፊት ከነበሩበት የሃይማኖት ሥርዓት የተለየ ነገርን አያስገኝም፤ በሽምግልና ጊዜ/በስተርጅና/ <u>ከማንኛውም የሃይማኖት ሥርዓት ተለይቶ</u> <u>ከኢየሱስ ጋር መኖር</u> ግን በዳግመኛ ልደት የሚገኘውን የእግዚአብሔር ልጅነትን ያጎናጽፋል፡፡

ስለዳግመኛ መወለድ የተነገረውን ትምህርት ከእውነተኛው መምህር ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ እንዳይማሩ ብዙዎችን የሚያዘናጋው ሌላው የሰው ችግር ደግሞ «ሁሉንም አውቃለሁ፤ እንኳን ለራሴ ለሌላውም አስተምራለሁ» በሚል ትምክህት በጌታ እግር ሥር ዝቅ ብሎ ለመማር ፈቃደኝነትን አለማሳየት ነው፡፡ ኒቆዲሞስ «የእስራኤል መምህር» በሚል

*(ወደ ገጽ 4 ይዞራል)*

## ዳግመኛ .... ከገጽ 3 የዞረ

ቅጽል የተጠራ ሰው ነበር/ቁ.10/:: የእርሱ መምህርነት ለተወሰኑ ደቀመዛሙርት እንደሆነ ተደርጎ አልተገለጸም፤ በጠቅላላው የእስራኤል መምህር ተባለ እንጂ:: ይህ ሰው በመምህርነቱ ብዙ እውቀት ቢኖረውም ዳግመኛ መወለድን በተመለከተ ግን ሊያውቅ አልቻለም:: ስለዚህ ከተለያዩ የትምህርት ተቋማትም ሆነ ከሃይማኖት መምህራን ዘንድ የተማርናቸውና በመምህርነት የተመረቅንባቸው የተለያዩ ትምህርቶች ቢኖሩንም መንፈሳዊ የሆነውን የዳግመኛ መወለድ ምሥጢር ልንማር የምንችለው የራሳችንን መምህርነት ወደ ጐን ትተን ወደጌታ እግር ሥር ስንመጣ ብቻ ነው:: ኒቆዲሞስ ለጊዜው ባይገባው እንኳ በኋላ ከጌታ ጋር እስኪገለጥ ድረስ ሕይወቱ እንደተለወጠ በዚያው በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ እንረዳለን/ዮ7:50፤ 19:39/:: «ማንም አንዳች የሚያውቅ ቢመስለው ሊያውቅ እንደሚገባው ገና አላወቀም» ተብሎ በ1ቆሮ8:2 እንደተጻፈው ገና የማናውቃቸው ብዙ መለኮታዊ ትምህርቶች እንዳሉ ተገንዝበን ከጌታ ለመማር ዝቅ ልንል ያስፈልጋል፤ በተለያየ ሙያና እውቀት በዚህ ዓለም መምህር ብንባልም በጌታ ፊት ግን ደቀመዝሙር ለመሆን መፍቀድ ይገባናል፤ ያን ጊዜ በአዲስ ልደት የእግዚአብሔር ልጅ መሆን እንዴት እንደሚቻል ከእርሱ እንማራለን::

ኒቆዲሞስ ምንም እንኳ ኢየሱስን ከሚቃወሙት ከፈሪሳውያን ወገን ቢሆንም በሌሊት ወደ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ስለ ኢየሱስ የተናገረው ነገር መልካም ምስክርነት ነው፤ ሌሎች ፈሪሳውያን ወደ ኢየሱስ ሲቀርቡ እንደሚናገሩት የፈተናና የተቃውሞ ንግግር አልተናገረም፤ ኢየሱስ ከሚያደርጋቸው ምልክቶች ተነሥቶ ስለ ኢየሱስ የተረዳውን ያህል እንዲህ ሲል መሰከረ፤ «መምህር ሆይ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን እነዚህን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል የለምና መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣህ እናውቃለን» አለ /ምዕ.3:2/::

ጌታ ኢየሱስ ኒቆዲሞስ ከተናገረው በላይ እጅግ የከበረ ማንነት አለው፤ እርሱ ከእግዚአብሔር የተላከ መምህር ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅም ነው፤ እርሱ የመለኮት ሙላት በሰውነት የተገለጠበት እውነተኛ አምላክ ነው:: ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ዘንድም ያለ ወይም በአባቱ እቅፍ የሚገኝ የባሕርይ አምላክም ነው:: እርሱ በኒቆዲሞስ ፊት በምድር በሥጋ እየታየ በሰማይ የሚኖር አምላክ ነው፤ ኒቆዲሞስ ይህን ሁሉ በቃላት ተነግሮ የማያልቀውን የኢየሱስን መለኮታዊ ክብር ሳያውቅ «መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣህ እናውቃለን» ቢለውም ይህን ማለቱ የእግዚአብሔር/የያህዌህ/ ልጅ ለመሆን አያበቃውም::

አንዳንድ ጊዜ ነገሮችን በማቻቻል መናገር የሚወዱ ሰዎች ስለኢየሱስ የተነገረውና የሚባለው ሁሉ ትክክል እንደሆነ ይስማሙና ራሳቸውን ለእርሱ ከመስጠት ግን ሲቆጠቡ እናያለን:: ኒቆዲሞስ ስለኢየሱስ የመሰከረው እጅግ ጥቂቱን ከመሆኑም በላይ የተናገረበት ዓላማ ራሱን የኢየሱስ ደቀመዝሙር አድርጎ ለመስጠት ከማሰብ ሳይሆን እንደተለመደው ለንግግሩ እንደ መግቢያ ይጠቀመኛል ብሎ የተናገረው አዎንታዊ ንግግር ሊሆን እንደሚችል ከንባቡ ይዘት መረዳት ይቻላል፤ በዚህ ዓይነት በተለያየ አጋጣሚ ስለኢየሱስ መልካም ነገርን መናገር ብቻ ሳይሆን ከኒቆዲሞስ በበለጠም የኢየሱስን ጌትነቱንና አምላክነቱንም ጭምር እየተናገሩ ራሳቸውን ግን እርሱን ከመከተል ፈቀቅ የሚያደርጉ ብዙ ወገኖች መኖራቸው የዘመናችን ዋነኛ ገጽታ ነው፤ እንደዚህ ያለው መንፈስ ብዙዎችን በመቆጣጠሩ ዛሬ ስለኢየሱስ የሚነገረውን ወንጌል ሳይቃወሙ በመስማማት ከሚሰሙት መካከል ብዙዎቹ ቀዝቃዛ ምላሽ ሲሰጡ ይታያል፤ «ልክ ነው፣ ጥሩ ነው፣ እውነት ነው፣ ኢየሱስ ጌታ ነው፣ አዳኝ ነው፣ ይህን እናውቃለን» በማለት ብቻ ተወስነው ከተግባራዊ እርምጃዎች የተቆጠቡ ሁሉ ዳግመኛ በመወለድ የሚገኘውን የእግዚአብሔርን ልጅነት ገና አልተቀበሉም::

ጌታ ኢየሱስ ኒቆዲሞስን «መልካም ብለሃል» እያለ ስለተናገረው ነገር በማወደስ ጊዜ አላባከነም፤ ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የመጣበት ዋነኛው ምክንያት ሰውን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ማስገባት ነው:: እንዲህ ሆኖ ሳለ ኒቆዲሞስ ከእግዚአብሔር መንግሥት ውጪ ሆኖ ስለኢየሱስ መልካም ነገር ቢናገር ይህ ለኢየሱስ ምን ይረባዋል? የልቡንስ ደስታ ይህ እንዴት ሊፈጽምለት ይችላል? ኢየሱስ የሚረካውና ደስ የሚለው ኒቆዲሞስ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ ቢሆን ነው:: ለዚህ ደግሞ ዋነኛው መርህ ዳግመኛ መወለድ ነው:: ስለዚህ ኢየሱስ «እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም» አለው/ቁ.3/:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቶቹን አስረግጦ የሚናገርበት ሐረግ «እውነት እውነት እላችኋለሁ» የሚል ቃል ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዚህ ዓይነት አገላለጹ የሚታወቀው እርሱ ብቻ ነው:: በእርግጥም እርሱ ራሱ እኔ «መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ» ለማለት የተቻለው/ዮሐ14:6/ ነው፤ ወደዚህ አለም የመጣውም ለእውነት ሊመሰክር ነው/ዮሐ18:37/:: ስለሆነም ትምህርቶቹን ሁሉ «እውነት እውነት እላችኋለሁ» እያለ ማስረገጡ በእርግጥም አስፈላጊ ነበር:: ለኒቆዲሞስም የዳግመኛ መወለድን እውነት ሲያስተምረው «እውነት እውነት እልሃለሁ» በማለት ይናገረዋል፤ ኒቆዲሞስ ይህን ቃል ከኢየሱስ ሲሰማ ቀጣዩን ወሳኝ ትምህርት ለመስማት ልቡ ምን ያህል ተከፍቶለት ይሆን! ጌታ ኢየሱስ ወደ እርሱ ለመጣ ሰው ሁሉ የሚያስተምረውንና የሚናገረውን ቃል ይሰማና ይቀበል ዘንድ ልቡ የተዘጋጀ እና የተከፈተ እንዲሆን እንዲሁም ለዚያ ቃል ከፍ ያለ ትኩረት እንዲሰጠው «እውነት እውነት እልሃለሁ» በማለት በአጽንኦት ይናገረዋል:: «እውነት እውነት እልሃለሁ» በሚለው በዚህ ቃል ዘንድ የእኛስ ሁኔታ እንዴት ነው? ጌታ ኢየሱስ የሚናገረውን ትምህርት እውነትነት አስረግጠን እንረዳ ዘንድ ልባችን ተከፍቷልን? እርሱ የሚናገረንን በትኩረት፣ በማስተዋልና እጅግ በነቃ ኅሊና እንሰማ ዘንድ በዚህ ቃል ተዘጋጅተናልን?

የዳግመኛ መወለድ ትምህርት ለኒቆዲሞስ ብቻ የተነገረ ትምህርት አይደለም፤ ጌታ ኢየሱስ «እውነት እውነት እልሃለሁ» በማለት አስረግጦ ለኒቆዲሞስ የነገረው ይህ ትምህርት ለሰው ሁሉ የሚሆን አጠቃላይ መርህ ነው:: ጌታ ኒቆዲሞስን «ዳግመኛ ካልተወለድክ የእግዚአብሔርን መንግሥት ልታይ አትችልም» እንዳላለው ማስተዋል ያስፈልጋል:: ነገር ግን «ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔር መንግሥት ሊያይ አይችልም» የሚል መርህን ነግሮታል፤ ስለዚህ ለኒቆዲሞስ ስለዳግመኛ መወለድ የተነገረው ቃል ለሰው ሁሉ የሚሆን አ ጠቃላይ መመሪያ ነው:: ኒቆዲሞስ ወደ ኢየሱስ በመጣበት በዚያች ሌሊት ለሰው ሁሉ የሚሆን መሠረታዊ ትምህርት ተገልጧል:: ይህም ትምህርት ከዚያ በኋላ በየትኛውም ክፍለ ዘመን የሚኖርን ማንኛውንም ሰው የሚመለከት ትምህርት ነው:: ምክንያቱም ሰው ሁሉ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማየት ይችል ዘንድ ዳግመኛ መወለድ አስፈላጊው ነውና::

ዳግመኛ መወለድ ማለት በሥጋ ከምንኖረው ሕይወት የተለየ አዲስና መንፈሳዊ የሆነ ሕይወትን ለመኖር የሚያስችል እውነተኛ ለውጥ ማለት ነው:: «መወለድ» የሚለውን ቃል ስንመለከት «የሚወለደው ፅንስ» አስቀድሞ የነበረበትን የእናት ማኅፀን ትቶ ወደ ሌላ አዲስ ዓለም መውጣቱንና አዲስ ሕይወት ለመኖር መጀመሩን ያሳያል:: ዳግመኛ መወለድ ደግሞ ቀደም ሲል የነበርንበትን አለማዊና ሥጋዊ አኗኗር ሙሉ በሙሉ በመተው ወደ አዲስ መንፈሳዊ ዓለም ውስጥ ሙሉ በሙሉ መግባት ነው፤ ይህም የሚሆነው እውነተኛ የልብ

*(ወደ ገጽ 8 ይዞራል)*

# ቤተክርስቲያን በአጥቢያ ገጽታዋ

## መግቢያ

በክርስቶስ ኢየሱስ ሞት የተመሠረተችው የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን በምድር ላይ እግዚአብሔር ራሱን የሚገልጥባት ማዕከል ናት፤ የምትመራው በሰማያዊና በመንፈሳዊ መርሆዎች ቢሆንም በምንኖርባት በዚህች ዓለም የምትታይ አካልም ናት፤ ይህቺ አካል የምትገለጠውም በወንጌል ቃል በኩል ከዚህች ዓለም ተጠርተው ለእግዚአብሔር የተለዩ ወገኖች በምድር ላይ በጌታ በኢየሱስ ስም ሲሰበሰቡ ነው፡፡

ቤተክርስቲያን በስፍራና በዘመናት የማትወሰን አንዲት የክርስቶስ አካል ናት፤ እንዲሁም ከነገድ ከቋንቋም ሁሉ በክርስቶስ ደም የተዋጁትን ማናቸውንም የሰው ዘር ወገኖች የያዘች የእግዚአብሔር መንግሥት ነች፤ ይህም ቤተክርስቲያን ዓለም አቀፍ እና ዘመን አቀፍ ባሕርይ እንዳላት ያመለክታል፡፡ በምድር ላይ በጌታ በኢየሱስ ስም የሚሰበሰቡትን ሁሉንም አባሎቿን ግን ስፍራና ዘመን ሊያገናኛቸው አይችልም፤ ስለሆነም ቤተክርስቲያን በየዘመናቱ በተለያዩ ስፍራዎች የተሰበሰቡ አጥቢያ ጉባዔያት አሏት፤ እኛም በዚህ ጽሑፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቤተክርስቲያን በአጥቢያ ገጽታዋ እንዴት እንደተገለጠች የሚያስረዳ እውነትን እናቀርባለን፡፡

## አብያተ ክርስቲያናት

መጽሐፍ ቅዱስ «የእግዚአብሔር አብያተክርስቲያናት»/1ቆሮ11፡16/ ወይም «የክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናት»/ሮሜ16፡16/ በሚልባቸው ንባቦች አብያተ ክርስቲያናት ብሎ በብዙ ቁጥር ሲናገር በአንዲቷ ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙትን አጥቢያ ጉባዔያት ያመለክታል እንጂ በእምነትና በትምህርት የተለያዩና ምንም አንድነት የሌላቸውን ነገር ግን ራሳቸውን «አብያተ ክርስቲያናት» እያሉ የሚጠሩትን የሚያመለክት አይደለም፡፡ በአንድ ከተማ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በአንድ ሠፈር ውስጥ እንኳ ሆነው ቅርብ ለቅርብ በተሠሩ አዳራሾች ለአምልኮ የሚሰበሰቡትን፣ በተለያየ ስም የሚጠሩትንና የተለያየ እምነትና ሥርዓት ያላቸውን የዘመናችንን የተከፋፈሉ «አብያተ ክርስቲያናት» የሚያሳይ አይደለም፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አብያተ ክርስቲያናት ተብሎ የተነገረውን ቃል የተለያዩ የክርስትና የእምነት ድርጅቶችን ለማመልከት መጠቀም ቃሉ የማያመለክተውን ሐሳብ መናገር ነው፡፡ በዓለም አቀፍና በአገር አቀፍ ደረጃ ግዙፍ የሆነ የእምነት ድርጅት ሆኖ፣ ከሌላው የሚለዩበትን አቋም የሚገልጽ መጠሪያ ስም አውጥቶ «ቤተክርስቲያን» በማለት በድፍረት ከሰየሙ በኋላ በልዩነት ላይ የተመሠረተ አንድነት(unity in diversity) ፈጥሮ የተለያዩ የእምነት ድርጅቶችን «አብያተ ክርስቲያናት» ብሎ መጥራት የእግዚአብሔር ቃል የሚናገረውን እውነት ካለማስተዋል የመጣ የዘመናችን ስህተት ነው፡፡

ሆኖም ምን ጊዜም ቢሆን እውነትን ሳይስት ቃሉን በቀጥታ ለመረዳት የሚታዘዝ ቅን ልብ አብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ትክክለኛ ትርጉሙ ምን እንደሆነ ለመረዳት ይችላል፤ በአንዲቷ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ውስጥ በየስፍራው የሚገኙትን አጥቢያ ቤተክርስቲያናት ማለት እንደሆነም ይረዳል፡፡ ከዓለማዊ አሠራር ተቀድቶ ከዋና ከተማ ጀምሮ እስከ ገጠር መንደሮች ድረስ በየደረጃው የተዋቀሩትንና በተለያየ ስም የሚጠሩትን የክርስትና እምነት ድርጅቶችን ፈጽሞ ሊያመለክት እንደማይችልም በቀላሉ ያውቃል፤ የእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት ከዓለም ተለይተው ለእግዚአብሔር የተቀደሱ ወይም የተለዩ የአማኞች ማኅበራት ከመሆናቸው አንፃር «ቅዱሳን አብያተ ክርስቲያናት»/1ቆሮ14፡33/ ተብለው ተጠርተዋል፤ ከአሕዛብ ተጠርተው የተሰበሰቡ አማኞችን ለማመልከት ደግሞ «የአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት» የሚል አገላለጥ እናገኛለን /ሮሜ16፡4/፡፡ እንደዚሁም በአንድ አገር ወይም ክፍለ ሀገር የሚገኙ የተለያዩ ጉባዔያት ከዚያ አገር ወይም ክፍለ ሀገር ጋር አብረው ተጠርተዋል፤ ለምሣሌ «የገላትያ አብያተ ክርስቲያናት»/ገላ1፡2/፤ «የእስያ አብያተ ክርስቲያናት»/1ቆሮ16፡19፤ ራእ1፡5/፤ የሚሉ ንባቦችን እናገኛለን፡፡ ገላትያና እስያ ትላልቅ ክፍለ ሀገሮች እንደመሆናቸው መጠን በየስፍራው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ይገኙባቸው ነበር፡፡ ለምሳሌ በእስያ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ሰባት እንደነበሩ ተገልጧል /ራእ1፡5፣11፣20/፤ እነርሱም የኤፌሶን ቤ.ክ፣ የሰምርኔስ ቤ.ክ፣ የጴርጋሞን ቤ.ክ፣ የትያጥሮን ቤ.ክ፣ የሰርዴስ ቤ.ክ፣ የፊልድልፍያ ቤ.ክ እና የሎዶቅያ ቤ.ክ ናቸው፡፡ እነዚህ በእስያ ውስጥ በየከተሞቹ የሚገኙት አጥቢያ ጉባዔያት ባንድ ላይ ሲጠሩ የእስያ አብያተ ክርስቲያናት ተብለዋል፤ እዚህ ላይ ገላትያም ሆነ እስያ እንዲሁም ኤፌሶን፣ ሰምርኔስ፣ ጴርጋሞን፣ ትያጥሮን፣ ሰርዴስ፣ ፊልድልፍያ እና ሎዶቅያ የሚሉት ቃላት የክፍለ ሀገሮችና የከተሞች ስሞች ናቸው እንጂ በብሔራዊ ደረጃ የተዋቀሩ የተለያዩ የድርጅታዊ ቤተክርስቲያናት ስሞች አይደሉም፡፡

በዘመናችን በተለያዩ የእምነት ትምህርቶችና በሰው ሥርዓቶች ተከፋፍለው በተፈጠሩ የክርስትና እምነት ድርጅቶች ዘንድ እያንዳንዱን ድርጅታዊ ቤተክርስቲያን አጥቢያ ቤተክርስቲያን በማለት እንደ ኤፌሶን ወይም እንደ ሰርዴስ ቤተክርስቲያን አድርጎ ለማቅረብ ሲሞከርና እውነተኛውን የቃሉን ሐሳብ አቅጣጫ ለማሳት ጥረት ሲደረግ ይታያል፤ ነገር ግን ሰዎች በመረጧቸው ውብ በሆኑ ስሞች ለምሳሌ «ብርሃነ-ጽድቅ ቤተክርስቲያን፣ ፍኖተ-ወንጌል ቤተክርስቲያን፣ ማዕከለ-ሕይወት ቤተክርስቲያን … ወዘተ» እየተባሉ የሚጠሩትና በሚመሩባቸው የእምነት መርሆዎች የተከፋፈሉት የእምነት ድርጅቶች አጥቢያ ቤተክርስቲያናት እንዳልሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ «አጥቢያ (Locality)» የሚለው ቃል የሚያመለክተው ቦታን ወይም ስፍራን በሌላ አባባል አካባቢን ነው እንጂ የእምነት ድርጅትን አይደለም፤ ቦታውም የአንድ አካባቢ አማኞች የሚሰበሰቡባት ጉባዔ የምትገኝበት ከተማ ወይም መንደር ሊሆን ይችላል፡፡ አጥቢያ ቤተክርስቲያን(Local Church) ማለትም ባንዲት ከተማ ወይም መንደር የምትገኝ የክርስቲያኖች ጉባዔ ማለት ነው፡፡ እንደዚህ ያሉት በተለያዩ ከተሞችና መንደሮች የሚገኙ አጥቢያ ጉባዔያትም በዓለም ሁሉ ባለችው ባንዲቱ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ናቸው እንጂ ከዚያ የተለዩ አይደሉም፤ በእምነትም ሆነ በሥርዓተ አምልኮ እንዲሁም በአስተምህሮአቸው የጌታ የኢየሱስን ትምህርትና የሐዋርያትን ትምህርት የሚከተሉ ናቸው እንጂ የየራሳቸው የእምነት መግለጫ ያላቸው አይደሉም፡፡ አንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን እና ሌላው አጥቢያ ቤተክርስቲያን በአንድ ቤት ውስጥ የሚገኙ የአንድ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ናቸው፡፡ ስለሆነም በአንዱ አጥቢያ ያለው እምነትና ትምህርት በሁሉም አጥቢያ ይገኛል፤ ከዚህም የተነሣ በየአጥቢያው ያሉ አማኞች በተለያየ ምክንያት የሚኖሩበትን ከተማ ወይም መንደር ለቅቀው ወደ ሌላ ከተማ ወይም መንደር ቢሄዱ በሄዱበት ቦታ ባለች አጥቢያ ቤተክርስቲያን በጌታ እራትና በአምልኮ እንዲሁም በቃል አገልግሎትና በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጉባዔያት የመካፈል ሙሉ መብት አላቸው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ አብያተ ክርስቲያናት የሚለው ቃል

(ወደ ገጽ 6 ይዞራል)

*የአጥቢያ ... ከገጽ 5 የዞረ*

*የሚያመለከተው በዚህ መልክ እውነተኛ የመንፈስ አንድነት ያላቸውን የክርስቲያኖች ጉባኤያትን ነው::*

## የአጥቢያ ቤተክርስቲያን መጠሪያ

አጥቢያ ቤተክርስቲያን በአንድ ስፍራ የምትገኝ አንዲት ጉባዔ እንደመሆኗ መጠን በዚያው በምትገኝበት ቦታ ከመጠራት በቀር እኛ የምናወጣላት ስም ሊኖራት አይገባም፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አጥቢያ ቤተክርስቲያናት በተለያየ አገላለጽ ተጠርተዋል፤ «በኢየሩሳሌም ያለች ቤተክርስቲያን» /የሐዋ.ሥ8፡1/፣ «በአንጾኪያ ያለች ቤተክርስቲያን»/የሐዋ.ሥ13፡1/፣ «በክንክራኦስ ያለች ቤተክርስቲያን» /ሮሜ16፡1/ «በቆሮንቶስ ያለች የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን»/1ቆሮ1፡2፣2፡1/፣ «የተሰሎንቄ ሰዎች ቤተክርስቲያን» /1ተሰ1፡1፤ 2ተሰ1፡1/፣ ..... እየተባሉ ተገልጸዋል:: እዚህ ላይ አንባቢው እንዲያስተውል የሚያስፈልገው አጠራሩ በቦታ የተገለጸም ሆኖ የቃላት አቀማመጡ ግን የተለያየ መሆኑን ነው፤ ለምሳሌ «በኢየሩሳሌም ያለች ቤተክርስቲያን፣ በቆሮንቶስ ያለች የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን እና የተሰሎንቄ ሰዎች ቤተክርስቲያን» የሚሉትን አጠራሮች ስንመለከት ሦስቱም በቃላት አቀማመጥና ባገላለጻቸው እንደሚለያዩ እናያለን፤ እንዲሁም እነዚህ አገላለጾች አንድን አጥቢያ በአንድ ወቅት ለመግለፅ ጸሐፊዎቹ የተጠቀሙባቸው ሐረጐች /ቃላት/ ናቸው እንጂ የዚያች አጥቢያ ቋሚ የመጠሪያ ስሞች አለመሆናቸው ሊስተዋል ይገባል፤ በሌላ በኩል ደግሞ አጥቢያ ቤተክርስቲያን በምትገኝበት ከተማ ብቻ ሳይሆን በምትሰበሰብበት የአማኞች ቤትም የተጠራችበትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እናነባለን፤ ለምሳሌ በኤፌሶንና በሮሜ ውስጥ በአቂላና በጵርስቅላ ቤት የነበረች ቤተክርስቲያን «በቤታቸው ያለች ቤተክርስቲያን» ተብላ ተጠርታለች /1ቆሮ16፡19፤ ሮሜ16፡15/፤ በቈላስይስ ውስጥ በፊልሞና ቤት ያለች ቤተክርስቲያን «በቤትህ ላለች ቤተክርስቲያን» ተብላ ተጠርታለች /ቈላ4፡15፤ ፊልሞ.2/::

ይህ ሁሉ በአንድ ቦታ የምትገኝ አጥቢያ ቤተክርስቲያንን ለመግለፅ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚታይ የተለያየ አጠራር ነው:: መደበኛ ወይም ቋሚ የሆነ የመጠሪያ ስም ግን ለአጥቢያ ቤተክርስቲያናት አልተሰጠም:: አማኞች ለአምልኮና ለቃል እንደዚሁም ለጸሎት የሚሰበሰቡበትን አድራሻ ለመጠቆም ሲፈለግ ግን የቦታውን ስም ወይም የሚሰበሰቡበትን ቤት አድራሻ መጠቀም የሚቻል መሆኑን መዘንጋት የለብንም::

## የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ተጠሪነት

በዓለም ሁሉ በተለያዩ አገሮች ውስጥ በተለያዩ ከተሞችና መንደሮች የሚገኙትን አጥቢያ ቤተክርስቲያናት የሚመራቸው የቤተክርስቲያን ራስ የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው/ኤፌ1፡22፤ ቈላ1፡18/:: ስለዚህ በዓለምም ይሁን በአንድ አገር የሚገኙ በጌታ በኢየሱስ ስም ብቻ የተሰበሰቡ ጉባዔያት /አጥቢያ ቤተክርስቲያናት/ በምድር ላይ ራስ የሚሆናቸው ቢሮ (Head Office) ሊኖራቸው አይገባም፤ በዋና ከተማ ላይ የምትገኝ የተጠናከረ የገንዘብ አቅም እንዲሁም የሰው ብዛት ያላት ቤተክርስቲያን በሌሎች አነስተኛ ከተሞችና የገጠር መንደሮች የሚገኙትን አጥቢያ ቤተክርስቲያናት በበላይነት መምራት አትችልም:: እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ተጠሪነቷ ለክርስቶስ እንጂ ለሌላ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ወይም በማዕከላዊ ከተማ ለሚገኝ ራስ-ቢሮ (Head Office) መሆን የለበትም:: በቤተክርስቲያን ውስጥ ከአንድ ከክርስቶስ በቀር ሌላ ራስ የለም፤ ሆኖም ይህንን እውነት በመጣስ በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ በበላይነት መሪ በሆኑ ቢሮዎች በተሾሙ «ፓፓዎች፣ ፓትሪያርኮች፣ ሊቃነጳጳሳት፤ ፕሬዝዳንቶች፣ ፓስተሮችና ርእሰ ርኡሳኖች፣ አሁን አሁን ሐዋርያት ወዘተ» ቤተክርስቲያን እንድትመራ ማድረግ በዚህ ዘመን ጐልቶ የተለመደ የሰው ሥርዓት ነው:: በዚህ ዓይነት ተጠሪነታቸውን ለምድራውያን ራሶች ያደረጉ ጉባዔያት ሁሉ የክርስቶስን አካል ሊገልጡ በፍጹም አይችሉም፤ ስለሆነም አጥቢያ ቤተክርስቲያን በምድር ላይ የበላይ አካል ሳይኖራት በቀጥታ በሰማይ ባለውና በስሙ ስትሰበሰብ በመካከሏ በሚገኘው ራስ በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ልትመራ ይገባታል::

## የአጥቢያ ቤተክርስቲያናት የእርስ በእርስ ግንኙነት

በአንዲቷና በመላዋ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙት አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በድርጅታዊ ጠባይ የሚዋቀሩበት ገጽታ የላቸውም ማለት እርስ በእርሳቸው ምንም ዓይነት ግንኙነት የላቸውም ማለት አይደለም:: አንዲት አጥቢያ ቤተክርስቲያን ለሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ስላሉበት አጠቃላይ ሁኔታ ለመስማትና ለማወቅ የዘወትር መሻቷ ሊሆን ይገባል:: እርስ በእርስ መተሳሰብና መተዋወቅ ካለ ደግሞ እርስ በእርስ መደጋገፍም ይኖራል:: ለምሣሌ አንዲት አጥቢያ ቤተክርስቲያን በአንድ ከተማ ውስጥ ገና መሰብሰብ እንደጀመረች የወንጌል አገልጋይ ባይኖራት ከእርሷ ቀደም ብላ በተሰበሰበች አጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ የወንጌል አገልጋዮች ሊያገለግሏት ይችላሉ፤ የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን መሰብሰብ ስትጀምር የሆነው ልክ እንደዚህ ነበር:: በአንጾኪያ ውስጥ ሰዎች ወደ ጌታ ዘወር ያሉት በእስጢፋኖስ መገደል የተበተኑት አማኞች በሰበኩት ወንጌል ነው፤ ታዲያ ቁጥራቸው እጅግ ብዙ የሚሆኑ ሰዎች ማመናቸው በኢየሩሳሌም ባለችው ቤተክርስቲያን ሲሰማ «በርናባስን» ወደ አንጾኪያ ላኩት:: እርሱም ሳውልን ከጠርሴስ አምጥቶ በአንጾኪያ በቤተክርስቲያን ህዝብን እያስተማሩ ያገለግሉ እንደነበር እናነባለን/የሐ.ሥ.11፡19-26/:: በዚህ ዓይነት የወንጌላውያንና የአስተማሪዎች እጥረት ባሉባቸው ጉባዔያት /ቤተክርስቲያናት/ ከሌላ አጥቢያ ቤተክርስቲያን በነዚህ ጸጋዎች የተገለጡ አማኞች ሊያገለግሉ ይችላሉ:: ይህም በድርጅታዊ አሠራር በምደባ የሚከናወን ሳይሆን አጥቢያ ቤተክርስቲያናት ባላቸው ወንድማማችነት የሚከናወን ነው፤ ከሌላ አጥቢያ ቤተክርስቲያን በመጡ የወንጌል አገልጋዮች የምትገለገለው ቤተክርስቲያንም አገልጋዮቹን የምትቀበለው በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው ኢየሱስ በሌላ ቦታ ባለች ቤተክርስቲያን የገለጣቸው የእርሱ አገልጋዮች ናቸው በሚል እምነት ነው:: በዚህ ዓይነት የወንጌል አገልጋዮችን እጥረት ለመሸፈን አጥቢያ ጉባዔያት ድርጅታዊ ባልሆነ መልኩ በፍቅር ላይ ብቻ የተመሠረተ ግንኙነት ያደርጋሉ::

አብያተ ክርስቲያናት ለአማኞች ሁሉ የሚሆኑ መንፈሳዊ መልእክቶችን ለመካፈል የሚያስችላቸውን ግንኙነት ሊያደርጉ ይችላሉ:: በአንዲት አጥቢያ ቤተክርስቲያን የተሰበኩ ስብከቶች በጽሑፍና በካሤት ተባዝተው ሌሎች አጥቢያዎችም ከመልእክቱ ተካፋይ ቢሆኑ መልካም ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ ለቈላስይስ ሰዎች ሲጽፍላቸው «ይህችም መልእክት በእናንተ ዘንድ ከተነበበች በኋላ በሎዶቅያ ሰዎች ማኅበር ደግሞ እንድትነበብ አድርጉ፤ ከሎዶቅያ የምትገኘውን መልእክት እናንተ ደግሞ አንብቡ» ብሎአቸዋል /ቈላ4፡16/:: ከዚህም የምንረዳው የቈላስይስ ቤተክርስቲያንና የሎዶቅያ ቤተክርስቲያን የተላኩላቸውን መልእክታት እርስ በእርስ እንዲለዋወጡ ከሐዋርያው መታዘዛቸውን ነው:: ይህም ለአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ምክር ሌላ አጥቢያ ቤተክርስቲያን እንዲደርሳት ለማድረግ የሚያስችል የእርስ በእርስ ግንኙነት ሊኖር እንደሚችል ያስረዳል:: ይህም ድርጅታዊ በሆነ መንገድ ሳይሆን

*(ወደ ገጽ 12 ይዞራል)*

## *ለኢየሱስ ስፍራ*...*ከገጽ 1 የዞረ*

ለኢየሱስ ግን ስፍራ አልነበራቸውም:: የምድር ኃያላንና ባላባቶች እንደምንም ቦታ ሊፈለግላቸው ችሏል፤ ሰማይና ምድርን የዘረጋ እርሱ ግን የእንግድነት ስፍራ አላገኘም፤ ዛሬም ጌታ ኢየሱስ በወንጌል ቃል በኩል ወደ ሰው ልጆች ይመጣል፤ ወንጌልን እየሰማ ባለው በእያንዳንዱ ሰው ልብ በራፍ ላይ ኢየሱስ ይገኛል፤ እራሱም እንዲህ ይላል፤ «እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ ማንም ድምጼን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ እገባለሁ» ይላል፤ ታዲያ ይህን ጽሑፍ የምታነቡ ወገኖች እናንተስ በልባችሁ ለጌታ ኢየሱስ ስፍራ አላችሁን?

ጌታ ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ በሰዎች ዘንድ ስፍራ ያልተገኘለት ለምን ይሆን? የእርሱን ማንነት ካለማወቅ ይሆንን? እስራኤል አልተረዳችውም እንጂ በቤተልሔም ስለሚወለደው መሢሕ እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፤ «አንቺ ቤተልሔም ኤፍራታ ሆይ:- አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ በእስራኤልም ላይ ገዢ የሚሆን ይወጣልኛል»/ሚክ5:2/::

በነቢዩ ሚክያስ በተነገረው በዚህ ትንቢት ውስጥ በቤተልሔም የተወለደው መሢሕ ማንነቱ በሁለት መንገድ ተገልጧል::

1. አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ

ይህ አባባል ጌታ ኢየሱስ በሥጋ ከመገለጡ በፊት ያለውን ዘመን በሙሉ ያጠቃልላል:: የእርሱ ህልውና በሥጋ ከተገለጠ ጀምሮ አይደለም፤ እርሱ ከዘመናት በፊት ከዘላለም የነበረ ነው:: በማስተማር ዘመኑ ራሱ ጌታ ኢየሱስ ስለቀዳማዊነቱና ዘላለማዊነቱ ሲናገር «እውነት እውነት እላችኋለሁ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ» ብሏል/ዮሐ5:58/::

በቤተልሔም የተወለደው ህፃን አወጣጡ ከዘላለም የሆነ ጅማሬ የሌለው አምላክ ነው፤ ለዚህ ዘላለማዊነቱ ክብር አለመስጠትስ እንዴት አሳዛኝ ነው! ጅማሬያቸውና ፍጻሜያቸው ለሚታወቅ የክብር እንግዶች ስፍራ ለማዘጋጀት ሽርጉድ የሚሉ ሰዎች አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም ለሆነው ትኩረት መንፈጋቸው እንዴት ያለ እውቀት ማጣት ነው! በዚህ ዘመንስ እየሆነ ያለው ይህ አይደለምን? ከዘላለም ለሆነው ለዚህ ጌታ ልባችን ክፍት ነውን? ለእርሱ የሚሆን ስፍራ በልባችን ይኖራልን?

2. በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን

በጊዜው እስራኤል ትገዛ የነበረው በሮማውያን ሹማምንት ተከፋፍላ ስለነበር በይሁዳ ላይም የተሾመ ገዥ ነበር:: እግዚአብሔር ግን እስራኤልን አንድ አድርጎ የሚገዛ ንጉሥ ወይም ገዢ አድርጎ መሢሕን /ክርስቶስን/ ሾሞአል፤ ይህም መሢሕ በቤተልሔም ከማርያም የተወለደው ህፃኑ ኢየሱስ ነው:: እስራኤል ለዚህ እግዚአብሔር ለሾመላት ገዥ ቦታ አልነበራትም፤ ከተወለደ ጀምሮ በምድር እስከኖረበት ዘመን ሁሉ እሱን በመሢሕነት አልተቀበለችውም፤ የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፤ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም ተብሎ እንደተጻፈው ነው/ዮሐ.1:11/፤ ዛሬስ በሕይወታችን የገዢነትን ስፍራ የያዘው ማነው? በልባችን እንዲገዛን ስፍራ የሰጠነው ለማነው? እግዚአብሔር ለሾመው ገዢ ለጌታ ኢየሱስ ስፍራ ሰጥተናልን? በእስራኤል ዘንድ በጥቅሉ ለጌታ ኢየሱስ ስፍራ ባይኖርም በእንስሶች ማደሪያ በግርግም ውስጥ ስፍራ ተግኝቶለታል፤ በአብ እቅፍ ያለው እርሱ በግርግም ውስጥ መተኛቱን ስናይ እኛን ለማክበር ራሱን ምን ያህል ባዶ እንዳደረገ እንረዳለን፤ በዚያን ጊዜ በነበሩ በእስራኤል ታላላቆች ዘንድ የእርሱ መወለድ ትኩረት ባይሰጠውም በሜዳ ባደሩት እረኞች ዘንድ ግን እጅግ ታላቅ ደስታን ያስገኘ ነበር/ሉቃ2:8-14/:: በዚያ ለነበሩ ነገሥታት የእርሱ መወለድ አስደንጋጭ ቢሆንም ከምሥራቅ ለመጡት የአሕዛብ ነገሥታት ግን እጅግ የሚያስደስት ነበር /ማቴ2:1-10/:: ጌታ ብሔራዊ ተቀባይነት ባያገኝም በጥቂት ቅንነት ባላቸው ሰዎች ዘንድ ግን ስፍራ አግኝቷል:: ዛሬም እንዲሁ ነው፤ በምድር ላይ ባሉ ታላላቆች ስፍራ ባይሰጠው ምስኪን በሆኑ ቅኖች ዘንድ ግን ለእርሱ የሚሆን ስፍራ ይገኛል::

ጌታ አየሱስ በከብቶች በረት በተወለደ ጊዜ በሰማይ ሠራዊት ዘንድ ታላቅ የሆነ ምስጋና ቀርቦ ነበር:: መንፈስ ቅዱስ ይህ የምስጋና ቃል እንዲጻፍልን ስላደረገ የምስጋናው ይዘት ምን እንደነበር ለማወቅ ችለናል/ሉቃ2:13-14/:: ጌታ ኢየሱስ በሰዎች ሕይወት ውስጥ ትክክለኛውን ስፍራ ሲይዝ የሚሆነውን ነገር እንድናስተውል የምስጋናውን ቃል አ ጠር አጠር አድርገን እስኪ እንመልከት::

1. ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን

**አርያም** ማለት ሰማይ ማለት ነው:: በመላእክት ሠራዊት ዘንድ ሁል ጊዜም ምስጋና ይቀርባል:: ጌታ በተወለደ ጊዜና ለሕዝብ ሁሉ የሚሆን የምሥራች በተነገረ ጊዜ ደግሞ በተለይ ለሰዎች ከተደረገው የጌታ ሥራ አንጻር ምስጋና አቅርበዋል:: ጌታ ኢየሱስ ስለሰዎች መዳን ራሱን ዝቅ አድርጎ በግርግም ውስጥ ቢተኛም እነርሱ ግን «ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን» በማለት እግዚአብሔርን አመስግነዋል፤ ዛሬም አንድ ኃጢአተኛ ንስሐ ሲገባ ልቡ ለኢየሱስ ወደሚሆን ስፍራ ስለሚለወጥ በሰማይ ሠራዊት ዘንድ ታላቅ ደስታን ያስገኛል፤ የዚህም ውጤቱ «ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን» የሚል ምስጋና ይሆናል::

2. ሰላምም በምድር

ስለ ጌታ ኢየሱስ «ህጻን» ተብሎ በተ ጠራበት ስፍራ ላይ የሰላም አለቃ እንደሆነ አስቀድሞ በነቢያት ተነግሮ ነበር/ኢሳ9:6/፤ አሁን ደግሞ በእርሱ መወለድ ሰላም በምድር እንደሚሆን በሰማይ ሠራዊት ተዘመረ:: ሰዎች ልባቸውን ለኢየሱስ የሚሆን ስፍራ አድርገው ሲሰጡ ለእነርሱም ሆነ ከእነርሱ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች የሚሆን ሰላም ከእርሱ ከጌታ ዘንድ ይገኛል::

3. ለሰውም በጎ ፈቃድ

ከመላእክቱ ምስጋና የምናስተውለው የመጨረሻው ነገር በጌታ መወለድ በሰዎች ዘንድ ወይም በሰዎች ውስጥ በጎ ፈቃድ እንደሚሆን ነው:: በሕይወታቸው ለኢየሱስ ስፍራ የሰጡ ሰዎች ፈቃዳቸው ሁሉ በጎ ይሆናል፤ ለእርሱ ስፍራ ያላቸው ሰዎች ለእነርሱና ለሌሎች ሁሉ የሚሆን በጎ ፈቃድ ይኖራቸዋል፤ ኢየሱስ በሚኖርበት ልብ ውስጥ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የሚስማማ በጎ ፈቃድ ይኖራል፤ እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ በጎ ፈቃዱ እንደሆነ ሁሉ/1ቆሮ1:21/ ለአየሱስ ስፍራ የሰጡ ሰዎችም በበጎ ፈቃድ ስለ ሰዎች ያስባሉ:: በማናቸውም ጉዳይ የሚያስቡትና የሚያደርጉት ሁሉ በበጎ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ይሆናል::

የተወደዳችሁ አንባብያን እናንተስ ለኢየሱስ ስፍራ አላችሁን? አንድ ኃጢአተኛ ለኢየሱስ ስፍራ የሚኖረው ልቡን በንስሐ ሲያዘጋጅ ነው:: ንስሐ በሚገባ አንድ ኃጢአተኛ ምክንያት ደግሞ በሰማይ መላእክት ዘንድ ደስታ እንደሚሆን ተነግሮናል/ሉቃ15:7ና10/:: ስለዚህ በኑሮአችሁ ሁሉ ለኢየሱስ ስፍራ ያልሰጣችሁ ሰዎች ለእርሱ ስፍራ ትሰጡት ዘንድ በንስሐ ልባችሁን አዘጋጁ ለት:: እናንተ ራሳችሁን ልትንቁ ትችሉ ይሆናል፤ በዚህ ዓለምም ያላችሁ ስፍራ የተናቀ ሊሆን ይችላል፤ ሆኖም የልባችሁን በር ከከፈታችሁለትና በውስጣችሁ ስፍራ ከሰጣችሁት እርሱ አይንቃችሁም፤ እርሱ የሚፈልገው የተዘጋጀ የውስጥ ማንነትን እንጂ ያሸበረቀ የውጭ ሽልማትን አይደለም::

ምናልባት በውስጣችን ስፍራ የያዘው የዚህ ዓለም ጊዜያዊ ጥቅምና ደስታ ከሆነም እንደ እንፏዋለት ጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ የሚጠፋ መሆኑን አውቀን ከልባችን እናስወጣው:: በምትኩም ለኢየሱስ ስፍራ እንስጠው፤ ይህንንም ለማድረግ ዛሬ ነገ ሳንል በቁርጠኝነት እንወስን:: ለዚህም ጸጋው አይለየን::

## *ዳግመኛ ...* *ከገጽ 4 የዞረ*

መለወጥ ሲኖር ነው፤ በእርግጥ ዳግመኛ መወለድ በቀላሉ በሥነ ምግባር የሚታይ የጠባይ ለውጥ ብቻ አይደለም፤ የሥጋን ፈቃድ የሚቃወምና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም የሚያስችል አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት በውስጣችን የሚገባበት ክስተት ነው:: የሥጋ አእምሮ ይህን መረዳት ሊከብደው ይችል ይሆናል፤ ምድራዊና ፊደላዊ በሆነ መንገድ በሥጋ ሥርዓቶች ብቻ የሚመራ አንድ የኦሪት እምነት ተከታይም ይህ ሊገባው አይችልም፤ ምክንያቱም እርሱ ስለመወለድ የሚያውቀው ከአብርሃም ዘር በሥጋ ስለመወለድ ብቻ ነው:: ይህ ብቻውን ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር እንድቆጠር ያስችለኛል ብሎ ያምናል፤ ስለዚህም ኒቆዲሞስ ጌታ ኢየሱስ ስለ ዳግመኛ መወለድ የሚያስተምረው ነገር ጥያቄ ፈጠረበት፤ ሰው ዳግመኛ የሚወለደው በተለመደው መንገድ በሥጋ መስሎት «ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን?» የሚል ጥያቄ ለጌታ አቀረበ:: አዎን ኦሪት ለኒቆዲሞስ ሰው በዕድሜም ከሸመገለ በኋላ እንኳ ሊያገኘው ስለሚችለው አዲስ ልደት አላስተማረችውም፤ እሱን ያስተማሩት ታላላቅ የሕግ መምህራን ይህን ሊያስተምሩት የሚችሉበት መንገድ የላቸውም፤ እርሱ የእስራኤል መምህር እስኪሆን ድረስ ስለዳግመኛ መወለድ ሰምቶም አያውቅም፤ አሁን ግን የሸመገለ ሰው እንኳ ሊጐናጸፈው ስለሚችለው በዳግመኛ ልደት ስለሚገኘው አዲስ ልጅነት በሚያስተምረው መምህር ፊት ቀርቧል:: ከአያት ከቅድመ አያት ሲወርድ ሲዋረድ በመጣ ሥርዓተ ሃይማኖት ውስጥ ወይም ከቤተሰብ በተወረሰ ቤተ-እምነት ውስጥ በመወለድና በማደግ የዳግመኛ መወለድን ነገር ማወቅ አይቻልም፤ ይህን መንፈሳዊ እውቀት ለማግኘት ወደ እውነተኛው መምህር ወደ ኢየሱስ መቅረብ ያስፈልጋል::

አሮጌው ሰው ሊያቀርበው ለሚችለው ለማናቸውም ጥያቄ በኢየሱስ ዘንድ የተሟላ መልስ ይገኛል:: በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ለእግዚአብሔር ልጆች የተዘጋጀውን ባለጠግነት ለመውረስ ለአዲስ ልደት ራስን ከማዘጋጀት ይልቅ የአፈጻጸም ጥያቄዎችን በማቅረብ ወደ ጌታ ዘወር ለማለት መዘግየቱ ጠቃሚ ባይሆንም ኢየሱስ ግን ለጥያቄዎቻችን የሚሆን መልስ ለመስጠት የሚቸገር መምህር አይደለም:: ከመንፈሳዊና ከመለኮታዊ አሠራር ጋር ያልተለማመደው የኒቆዲሞስ አእምሮ ላቀረበው ጥያቄ ኢየሱስ የሰጠው መልስ «እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም» የሚል ነበር/ቁ.5/:: በዚህም ምላሹ ላይ መምህራችን ኢየሱስ «እውነት እውነት እልሃለሁ» በማለት ትምህርቱን በድጋሚ አስረግጦ ይናገራል:: የወላዋይነት እና እርግጠኛ ያለመሆን ስሜት በውስጣችን በተፈጠረ ጊዜ «እውነት እውነት እልሃለሁ» የሚለውን የኢየሱስን ውብና ግልጽ የሆነ ቃል መስማት ነፍሳችንን ምንኛ ያረጋጋል! ምንኛስ ያሳርፋል! በኒቆዲሞስ ፍጥረታዊ አእምሮ በሽምግልና ዳግመኛ መወለድ የማይታመን ቢሆንም በእርግጥ እውነት ነው:: ለነገሩማ እሱ እንዳሰበው ዳግመኛ መወለድ ሁለተኛ ወደ እናት ማኅፀን በመግባት የሚከናወን ቢሆን ኖሮ ሰው እንኳን በሽምግልና በሕፃንነቱስ ቢሆን አንዴ ከተወለደ በኋላ በድጋሚ ከእናቱ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ኒቆዲሞስ ይህንንም የዘነጋው ይመስላል፤ ያልገባው ነገር ቢኖር ጌታ ኢየሱስ እያስተማረው ያለው «ዳግመኛ መወለድ» ከሥጋዊ ልደት በተለየ መልኩ በመንፈሳዊ መንገድ የሚከናወን መሆኑን ነው:: ሰው ዳግመኛ የሚወለደው ከሥጋ እናቱ ሳይሆን ጌታ እንዳስተማረው «ከውኃና ከመንፈስ» ነው::

በተጨማሪም የጌታ ትምህርት ግልጽ ባልሆነለት ኒቆዲሞሳዊ አእምሮ በሚመሩ ወገኖች ዘንድ ከውኃና ከመንፈስ የመወለድ ትርጉም አቅጣጫውን መሳቱ አሳዛኝ ነው፤ በፊደላዊ ትርጉም መመራት የለመደ አእምሮ በዚህ ስፍራ «ውኃ» የሚል ቃል ሲያገኝ ስለውኃ ጥምቀት ወደማሰብ ይሄዳል፤ ይህ ግን ያ ፊደላዊ ሥርዓትና ፊደላዊ አእምሮ የፈጠረው ትርጉም እንጂ ጌታ የተናገረው እውነተኛው ሐሳብ አይደለም፤ «ከውኃ መወለድ» ማለት «በውኃ መጠመቅ» ማለት አይደለምና:: መወለድና መጠመቅ በቃላት ብቻ ሳይሆን በትርጉምም የተለያዩ ናቸው፤ መወለድ በአዲስ ሕይወትና በአዲስ ስፍራ ለመኖር ከነበሩበት ማኅፀን መውጣት ነው፤ እንደዚሁም ከአንድ ዘር መገኘት ማለትም ነው:: መጠመቅ ግን ወደ ውኃ ሙሉ በሙሉ ራስን ማስገባት ወይም ተዘፍቆ መውጣት ነው:: ጌታ ኢየሱስ ከዳግመኛ መወለድ ጋር አያይዞ የተናገረው ከውኃ መወለድን እንጂ በውኃ መጠመቅን አለመሆኑን አንባቢው ሊያስተውል ይገባል:: በመሠረቱ ኒቆዲሞስ ወደ ጌታ በመጣ ወቅት የክርስቲያን ጥምቀት ገና አልተጀመረም ነበር፤ በዮሐ4:2 ላይ የጌታ ደቀመዛሙርት ሰዎችን እንዳጠመቁ ቢገለጥም ይህ እንደመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት ዓይነት ነው እንጂ የክርስትና ጥምቀት አለመሆኑ ሊታወቅ ይገባል:: ጌታ ለሐዋርያት ሰዎችን እያጠመቁ የእርሱ ደቀመዛሙርት እንዲያደርጉ ትእዛዝ የሰጠው ከእነርሱ ተለይቶ ሊያርግ ሲል በመጨረሻው ሰዓት እንደነበር እንረዳለን/ማቴ28:19፤ ማር16:16/:: ጌታ ከኒቆዲሞስ ጋር የተነጋገረው ግን ገና ማስተማር በጀመረ በመጀመሪያው ዓመት ነው:: ያን ጊዜ ደግሞ ኢየሱስ ገና ወንጌል እያስተማረ መሠረታዊ ነገሮችን እየገለጠ ነበር እንጂ እንደ ውኃ ጥምቀት ያሉትንና ሌሎችንም ተግባራዊ ሥርዓቶች የሚያስተምርበትና የጀመረበት ጊዜ አልነበረም፤ ሆኖም የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጐች የሚሆኑት ሰዎች እንዴት ያሉ እንደሆኑ ለይቶ የሚገልጽ ትምህርትን እየተናገረ ነበር፤ ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚያበቃው ጅማሬ ደግሞ ከውኃ መወለድ እንጂ በውኃ መጠመቅ አይደለም፤ ኒቆዲሞስም በውኃ ስለመወለድ ሲነገረው ስለውኃ ጥምቀት አላሰበም፤ ሊያስብ የሚችልበት ሁኔታም በዙሪያው አልነበረም፤ ምክንያቱም ኢየሱስም ሆነ ሐዋርያት በመደበኛ መልኩ ያመኑ ክርስቲያኖችን በውኃ እያጠመቁ ደቀመዛሙርት ማድረግ አልጀመሩም ነበርና፤ ይህ በይፋ የተጀመረው ከበዓለ ሃምሳው የመንፈስ ቅዱስ መውረድ በኋላ ነው::

ታዲያ «ከውኃ መወለድ» ምንድር ነው? ለመማር በሚፈልግ ልብ ሆነን በጌታ ትምህርት ውስጥ «ውኃ» የሚለው ቃል «መወለድ» ከሚለው ቃል ጋር መያያዙን በትኩረት ካስተዋልን ትርጉሙን ለመረዳት ቀላል ይሆንልናል:: በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ «ውኃ» የሚለው ቃል ከምናውቀው ፈሳሽ ውኃ ውጭ የሚያመለክተው ሌላ መንፈሳዊ ነገር እንዳለ እንረዳለን፤ ለምሳሌ በትንቢተ ሕዝቅኤል ምዕራፍ 36 ቁ.25 ላይ «ጥሩ ውኃንም እረጭባችኋለሁ፤ እናንተም ትጠራላችሁ፤ ከርኵሰታችሁም ሁሉ ከጣዖቶቻችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ» ተብሎ ስለ እስራኤላውያን የተነገረውን ቃል ስንመለከት በዚህ ክፍል የተገለጠው ውኃ በቁሙ ፈሳሽ ውኃ ማለት እንዳልሆነ እንረዳለን:: ምክንያቱም ፈሳሽ ውኃ ሰውን ከሰውነት እድፍ/ቆሻሻ/ እንጂ ከርኩሰትና ከጣኦት ሊያጠራ አይችልምና፤ ስለሆነም በዚህ ክፍል የተነገረው እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ የሚረጨው ጥሩ ውኃ ፊደል በፊደል የሚታወቀው የኵሬ ወይም የምንጭ ውኃ ሳይሆን የሕዝቡን ርኵሰት ሊያጠራ የሚችል ሌላ መንፈሳዊ ውኃ እንደሆነ መረዳት ይቻላል:: በትንቢተ አሞጽ ውስጥ ደግሞ እግዚአብሔር በምድር ላይ ስለሚልከው ረሀብ ስናነብ «እንጀራና ውኃ» የእግዚአብሔርን ቃል ሊያመለክቱ እንደሚችሉ እንገነዘባለን፤ ቃሉም ሲነበብ «እነሆ በምድር ላይ ራብን የምሰድበት ዘመን ይመጣል ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ እርሱም

*(ወደ ገጽ 9 ይዞራል)*

## ዳግመኛ ... *ከገጽ 8 የዞረ*

ከገጽ 8 የዞረ

የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት እንጂ እንጀራን ከመራብና ውኃን ከመጠማት አይደለም» ይላል/አሞ.8፡11/፡፡ ስለዚህ ጌታ የኦሪት መጻሕፍትን ለሚቀበለውና የኦሪት አማኝ ለነበረው ለኒቆዲሞስ ከውኃ ስለመወለድ ሲያስተምረው ከእግዚአብሔር ቃል መወለድ ማለቱ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ በአዲስ ኪዳንም ውኃ የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚያመለክት እናነባለን፤ ለምሳሌ በኤፌ.5፡26 ላይ ቤተክርስቲያንን በተመለከተ የተጻፈው ቃል «....<u>በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር</u> <u>አንጽቶ</u> እንዲቀድሳት ስለእርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ» ይላል፡፡ በዚህ ንባብ ውስጥ ቃሉ እንደ ውኃ የሚያነጻ እንደሆነ ተገልጧል፤ በዮሐ15፡3 ላይም «እናንተ <u>ስለነገርኳችሁ ቃል</u> አሁን ንጹሐን ናችሁ» ይላል፤ ውኃ ቆሻሻን እንደሚያነጻ ሁሉ የእግዚአብሔር ቃልም ከርኵሰት የማንጻት ሥራን ይሠራል፡፡ ከመታጠብና ከመንጻት ጋር የተገለጠው ይህ የእግዚአብሔር ቃል ባሕርይ ከዳግመኛ መወለድ ወይም ከአዲስ ልደት ጋር ተያይዞም ተገልጧል፤ በቲቶ3፡5 «...እንደ ምሕረቱ መጠን <u>ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታ ጠብ</u>ና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን......» የሚል ቃልን እናገኛለን፡፡ በዚህ ንባብ «መታጠብ» ከአዲስ ልደት ጋር ተያይዞ ተነግሯል፤ በሌላ አባባል በዚህ ንባብ የተገለጠው «መታጠብ» «ለአዲስ ልደት» የሚሆን ወይም የሚያበቃ መታጠብ ነው፡፡

መታጠብና መንጻት በእግዚአብሔር ቃል አማካኝነት ሊከናወን እንደሚችልና መታጠቡም አዲስ ልደትን ሊያስገኝ እንደሚችል ከላይ ባየናቸው ጥቅሶች ተረድተናል፤ ሐዋርያው ጴጥሮስ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል «የማይጠፋ ዘር» አድርጎ በተናገረበት ክፍል «ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፤ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ» ይላል/1ጴጥ1፡23/፡፡ በዚህ ንባብ ውስጥ ዳግመኛ መወለድ በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር እንደሆነ በማያሻማ መልኩ ተገልጧል፤ ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ ከውኃ ስለመወለድ ያስተማረው ትምህርት ከማይጠፋው ዘር ማለትም ከእግዚአብሔር ቃል መወለድ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ሐዋርያው ያዕቆብም «ከእግዚአብሔር መወለድ» በቃል አማካኝነት እንደሆነ ሲናገር «ለፍጥረቱ የበኵራት ዓይነት እንድንሆን <u>በእውነት ቃል</u> አስቦ ወለደን» ይላል/ያዕ1፡18/፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ውኃ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያመለከት መሆኑን ከተረዳንና ከእግዚአብሔር መወለድም በቃሉ አማካኝነት መሆኑን ካየን «ከውኃ መወለድ» ማለት «ከእግዚአብሔር ቃል» መወለድ ማለት መሆኑን በቀላሉ እንገነዘባለን፡፡ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ ዳግመኛ ሊወለድ የሚችለው ግን የሰማው ቃል በእምነት ሲዋሐደውና ሲቀበለው ብቻ ነው፤ የሰማው የእግዚአብሔር ቃል ከሰሚው ጋር በእምነት ካልተዋሐደ ግን ምንም አይጠቅመውም /ዕብ4፡2/፡፡ እንዲህ አይነት ሰው ዘሪው የዘራውን ዘር እንደማያበቅል እንደ መንገድ ዳር ወይም እንደ ጭንጫ መሬት ወይም እንደ እሾካማ መሬት ነው/ማቴ13፡3-8/፡፡ በዘመናችን በዓለም ዙሪያ ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል እየተሰበከ ነው፤ ብዙዎች የእግዚአብሔርን ቃል እየሰሙና እያነበቡ ነው፤ ሆኖም የምንኖርባት ምድር በአብዛኛው ዳግም ባልተወለዱ የአሮጌው ሰው ልጆች የተሞላች ናት፤ ለእግዚአብሔር ቃል የእምነት ምላሽ ላለመስጠት የሰው ልጅ ልብ ምንኛ ደንድኗል!

ጌታ ኢየሱስ ሰው ዳግመኛ የሚወለደው ከውኃና ከመንፈስ እንደሆነ የተናገረውን መሠረት በማድረግ ከውኃ መወለድ ምን ማለት እንደሆነ ከላይ አይተናል፤ በመቀጠል ደግሞ ከመንፈስ መወለድ ምን እንደሆነ እንማራለን፡፡ በዚህ ክፍል «መንፈስ» የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን መንፈስ ነው፡፡ በዮሐ4፡24 «እግዚአ ብሔር መንፈስ ነው» የሚል ቃል እናነባለን፤ በዮሐ1፡12 ላይ ደግሞ ኢየሱስን ያመኑ የእግዚአብሔር ልጆች ከእግዚአብሔር እንደተወለዱ እንጂ ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ እንዳልተወለዱ ተምረናል፤ በዚህ ክፍልም እግዚአብሔር የሚለው ቃል «ሥጋ» ለሚለው ቃል በተቃራኒ መልክ ቀርቧል፤ «ሥጋ» የሚታይ የሚዳሰስ ነገር ሲሆን እግዚአብሔር ግን «መንፈስ» ነው፡፡ ስለዚህ ከመንፈስ መወለድ ማለት ከእግዚአብሔር መወለድ ማለት ነው፤ አማኞች ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች የሚሆኑበት ብቸኛ መንገድም ይኸው ከመንፈስ መወለድ ነው፡፡ እዚህ ላይ ከውኃ መወለድና ከመንፈስ መወለድ ሁለት የተለያዩ ልደቶች እንዳልሆኑ ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡ ሁለቱም የሚናገሩት ስለአንዱ ዳግመኛ መወለድ ነው፡፡ «ከውኃና ከመንፈስ መወለድ» ተብሎ በአንድነት መነገሩም ልደቱ ከእግዚአብሔር መወለድን የሚያመለክት የአንድ ጊዜ መንፈሳዊ ክስተት መሆኑን ያሳያል፡፡ ለዳግመኛ ልደት የሚያበቁን ቃሉም ሆነ መንፈሱ የእግዚአብሔር ናቸው፡፡ «መንፈስ» የሚለው ቃል እግዚአብሔር በምድር ላይ ሥራ እየሠራበት ያለውን መንፈስ ቅዱስን ያሳያል፡፡ ይህም የራሱ መንፈስ ነው፤ ይህም መንፈስ ሰዎችን በእምነት ለመለወጥና አዲስ ዘላለማዊ ሕይወትን በውስጣቸው ለማስገባት በዚህም የእግዚ አብሔር ልጆች ሆነው ዳግመኛ እንዲወለዱ ለማድረግ የእግዚአብሔርን ቃል ይጠቀማል፡፡

ከውኃና ከመንፈስ ያልተወለዱ ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት «ሊያዩም» ሆነ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት «ሊገቡ» እንደማይችሉ በግልጽ ተነግሮናል፡፡ የዚህ ዓለም መንግሥታት በአገራቸው ወይም በመንግሥታቸው ግዛት ውስጥ ያልተወለደውን ሰው በቤተ መንግሥት ውስጥ ስፍራ ባይሰጡትም ባላቸው አለማዊ ሕግ መሠረት በበቂ ምክንያት ከሆነ ያን ሰው ቤተመንግሥታቸውን ሊያሳዩትም ሆነ ሊያስገቡት ይችሉ ይሆናል፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማየትም ሆነ ወደዚያ ለመግባት ግን ከእግዚአብሔር መወለድ አስፈላጊ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ያልሆነ በመንግሥቱ ውስጥ ስፍራ የለውም፤ ኢየሱስን ባመንን ጊዜ ከውኃና ከመንፈስ በምናገኘው ዳግመኛ ልደት ግን መንግሥቱን ማየትና ወደመንግሥቱ መግባት በሙላት ይሰ ጠናል/2ጴጥ1፡11/፡፡ የመንግሥቱ ካህናት የምንሆነውና ከእርሱ ከክርስቶስ ጋር የምንነግሠው በዳግመኛ ልደት ባገኘነው ሥልጣን ነው፡፡ ይህ ሁሉ ከፍ ያለ ክብር የሚገኝበትን ይህን መንፈሳዊ ልደት ቸል ያሉ ሁሉ ወደ ልባቸው ሊመለሱና የክብሩን ከፍታ ሊመለከቱ ያስፈልጋል፡፡

በዳግመኛ መወለድ የእግዚአ ብሔርን መንግሥት ማየትና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት በዚያም ያለውን ከፍ ያለ የእግዚአ ብሔርን ባለጠግነት መውረስ እንደሚቻል ከጌታ ተምረናል፤ ሆኖም ይህ ዳግመኛ መወለዳችን የሚታወቅበት በሥጋ ዓይን የሚታይ ምን ማስረጃ ይኖራል? የዚህ የዳግመኛ ልደት ክንዋኔስ እንዴት ዓይነት ነው? የሚሉ ጥያቄዎች ከፍጥረታዊው ሰው አእምሮ ተነሥተው ብዙ ጊዜ ሊጠየቁ ይችላሉ፤ የኒቆዲሞስም ችግር ይህንን መረዳት አለመቻል ነበር፡፡ ጌታ ኢየሱስ ይህን ጥያቄ የሚመልስ ቃል ሲናገር «ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው፤ ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል ስላልሁህ አታድንቅ፤ ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል ድምፁንም ትሰማለህ ነገር ግን ከወዴት እንደመጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም፤ ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው» ብሏል/ዮሐ.3፡6-8/፡፡ ከዚህም አባባል የምንረዳው በዳግመኛ ልደት የሚገኘው ልጅነት በባሕርዩ ሥጋዊ የሚታይ/የሚዳሰስ/ ሳይሆን መንፈሳዊ/መንፈስ ከሆነው ከእግዚ አብሔር የተገኘ/ መሆኑን ነው፤ ይህም አዲስ ሕይወት ነው፡፡ ይህም ሕይወት የሥጋ ፈቃድ የሚስማማው አይደለም፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚከተል ነው እንጂ፤ የፍጥረታዊ ሰው አእምሮ ይህን ባይረዳው የሚያስደንቅ አይደለም፤ እንዲህ ያለ አእምሮ የሚረዳው የሚታይና የሚዳሰስ ቁሳዊና

*(ወደ ገጽ 11 ይዞራል)*

## ኢዮሣፍጥና *....ከገጽ 1 የዞረ*

ማስገኘት ወይም በቃጠሎ ምክንያት ጠባሳ ሆኖ የደነደነ ህሊና ማትረፍ ከሆነ ወይም ወደላቀ እውነት መድረስ አስቀድሞ ራሳቸውን በመካድ ከክፉ ተለይተው ይኖሩ የነበሩትን ሰዎች ተመልሰው ይጠሉት ወደነበረው ነገር ውስጥ ራሳቸውን እንዲዘፍቁና ግዴለሾችና ዓለማዊያን እንዲሆኑ ምክንያት የሚሆናቸው ከሆነ አሳዛኝ ነው:: ሐቁ ግን እንዲህ አይደለም፤ ምክንያቱም እውነትን በማወቅ ማደግ እግዚአብሔርን በማወቅ ማደግ ነውና፤ እግዚአብሔርን በማወቅ ማደግ ካለ ደግሞ በተግባራዊ የቅድስና ሕይወት ማደግ አለ፤ ስለሆነም አስቀድሞ የሚጸየፈውን ነገር ሳይገቅ የሚያልፍ ህሊና በእጅጉ ሊፈራ ይገባል፤ ምክንያቱም በእግዚአብሔር እውነት ተጽዕኖ ሥር በመሆን ፈንታ በሚያደነድን በኃጢአት የማታለል ተጽዕኖ ሥር ወድቋልና::

በምዕራፍ 17 የቀረበልን ነገር በሁለንተናው አስደናቂ ነው፤ ኢዮሣፍጥ አባቱ የማረከውን ግዛት አጽንቶ የያዘ ብቻ ሳይሆን በራሱም ግዛትን በማስፋት የመንግሥቱን ጥቅም ያስጠበቀ ሰው ነው:: ሁሉም ነገር በአግባቡ ነበር፤ «እግዚአብሔርም ከኢዮሣፍጥ ጋር ነበረ፤ በፊተኛይቱ በአባቱ በዳዊት መንገድ ሄዷልና፤ በኣሊምንም አልፈለገምና፤ ነገር ግን የአባቱን አምላክ ፈለገ፤ በትእዛዙም ሄደ፤ የእስራኤልንም ሥራ አልሠራም:: እግዚአብሔርም መንግሥቱን በእጁ አጸና፤ ይሁዳም ሁሉ እጅ መንሻ ለኢዮሣፍጥ አመጣ፤ እጅግም ብዙ ብልጥግናና ክብር ሆነለት፤ ልቡም በእግዚአብሔር መንገድ ከፍ ከፍ አለ፤ የኮረብታውን መስገጃዎችና የማምለኪያ ዐፀዱንም ከይሁዳ አስወገደ /ቁ.3-6/:: የኢዮሣፍጥ የብልጥግናው ምስጢር «ልቡን በእግዚአብሔር መንገድ ከፍ ከፍ ከማድረጉ» ላይ ነው፤ ልብ እንዲህ ባለ መንገድ በጌታ ነገር ከፍ ስትል ሁሉም ነገር በተገቢው መንገድ ይቀጥላል:: በምዕራፍ 18 ላይ ግን ነገሮች ሌላ መልክ ይዘው እናገኛለን፤ የኢዮሣፍጥ ብልጥግና ለገዛ ራሱ ወጥመድ ይሆንበት ዘንድ ለሰይጣን አገለገለ፤ «ለኢዮሣፍጥም ብዙ ብልጥግናና ክብር ነበረው፤ ለአክአብም ጋብቻ ሆነ»/18:1/፤ አስቀድመን ኢዮሣፍጥ መንግሥቱን እንዴት እንደመሸገ አይጠተናል፤ ነገር ግን ጠላት ኢዮሣፍጥ ራሱን ያዘጋጀ በማይመስልበት መንገድ መጣበት፤ ጠላት የተመሸገ መንግሥቱን አላጠቃበትም፤ በምትኩ ግን ልቡን አጠቃበት፤ እንደአንበሣም ሳይሆን እንደእባብ መጣበት፤ የአክአብ «በሬዎችና በጎች» እርሱን ለማጥቃት ከአክአብ ጦረኞች ሰዎች ይልቅ ውጤታማ ነበሩ፤ አክአብ በኢዮሣፍጥ ላይ ጦርነትን አውጆ ቢሆን ኖሮ ውጤቱ ኢዮሣፍጥን በእግዚአብሔር ላይ እንዲወድቅ ማድረግ ነበር፤ ይሁንና ግን ይህን አላደረገም:: የኢዮሣፍጥ መንግሥት በአክአብ ጠላትነት ላይ ተመሽጓል፤ የኢዮሣፍጥ ልብ ግን ለአክአብ ማታለል ክፍት ነበረ:: ይህ በእርግጥ አሳዛኝ ነው፤ ብዙውን ጊዜ በአንድ መልኩ ክፋትን ለመከላከል እጅግ ታላቅ የሆነ ጥረት እያደረግን በሌላ በኩል ደግሞ ክፋትን ወደውስጣችን እንዲገባ በር እንከፍትለታለን::

ኢዮሣፍጥ መጀመሪያ በእስራኤል ላይ ልቡን አጠንክሮ ነበር፤ ነገር ግን አሁን ደግሞ ከእስራኤል ንጉሥ ጋር ወዳጅነት ገጥሞ እናገኘዋለን፤ እና ለምን? የተለወጠና የተሻለ ነገር ተገኝቶ ነውን? የአክአብ ልብ ከፊት ይልቅ ለእግዚአብሔር የሚታዘዝ ሆኖ ነውን? በማናቸውም መንገድ አልነጠበረም:: አክአብ እንደቀድሞው ነበር፤ የኢዮሣፍጥ ህሊና ግን አስቀድሞ የነጠበረውን የመታዘዝና የጠንቃቃነት መንፈስ አጣ፤ ወደ ክፋትም አብዝቶ ቀረበ፤ አብሮም ተሳተፈ፤ በከፍተኛ ደረጃም ራሱን አዛመደና ራሱን አረከሰበት፤ «ለአክአብም ጋብቻ ሆነ»፤ አሠራሩ ዝግተኛ ቢሆንም ቀይቶም ሆነ በቶሎ የራሱን ፍሬ ሊያፈራለት ያለ ክፋት እዚህ ላይ አለ፤ «በገዛ ሥጋው የሚዘራ ከገዛ ሥጋው መበስበስን ያጭዳልና»/ገላ6:8/፤ የዚህ ነገር እውነታም የግድ ራሱን መግለጡ አይቀርም፤ ጸጋ የኃጢአትን ይቅርታ በመስጠት አሸናፊነቷን ልታሳይ ብትችልም የተዘራው ዘር ግን በጊዜው ፍሬ ማፍራቱ አይቀርም፤ ኦርዮንን በተመለከተ ያለውን የዳዊትን ኃጢአት እግዚአብሔር አስወግዷል፤ ነገር ግን ቤርሳቤህ የወለደችው ሕጻን ከመሞት አላመለጠም፤ አቤሴሎምም በዓመፅ ከመነሣት አልቀረም፤ ለሁል ጊዜም የሚሆነው ይኸው ነው፤ በሥጋ የምንዘራ ከሆነ መበስበስን ማጨድ አለብን፤ ሥጋ ሌላ ሊያፈራ አይችልምና::

ኢዮሣፍጥን በተመለከተ የተሳሳተ እርምጃው ያስከተላቸው ውጤቶች ራሳቸውን መግለጥ የጀመሩት ከበርካታ ዓመታት ቆይታ በኋላ አይደለም፤ ኢዮሣፍጥ «ከጥቂት አመት በኋላም ወደ አክአብ ወደ ሰማርያ ወረደ፤ አክአብም ለእርሱና ከእርሱ ጋር ለነበሩት ሕዝብ ብዙ በሬዎችና በጎችን አረደ፤ ከእርሱም ጋር ወደሬማት ዘገለአድ ይሄድ ዘንድ አባበለው»/18:2/፤ ሰይጣን የሚበጀውን የራሱን ስፍራ በደንብ ያውቃል፤ የክፋት ዘርም ከምን ጋ እንደበቀለ ያውቃል፤ ለእርሱ ማባበያም በጎ ምላሽ ለመስጠት የተዘጋጀ ልብንም ያውቃል፤ የይሁዳ ንጉሥ ከእሥራኤል ንጉሥ ጋር የገባበቱ ወዳጅነት የይሁዳን ንጉሥ ለበለጠ ውድቀት እንዳዘጋጀው ሰይጣን ያውቃል:: ክርስቲያንም ከዓለም ጋር የሚያያይዘው ነገር ውስጥ ከገባ ክርስቲያናዊ ወዳልሆነ የድርጊት መንገድ ለሚያስገባ የዓለም ማባበል ራሱን ክፍት ያደርጋል:: ዳዊት ጺግላግን ከባእድ እጅ ከአንኩስ በስጦታ ተቀበለ/1ሳሙ27:6/፤ ቀጣዩ እርምጃ ግን እስራኤልን ለመውጋት አንኩስን መተባበር ነበር/1ሳሙ28.1/::

ዓለም በምትኩ ታላቅ የሆነ ውለታ ወይም ምላሽ ከእጃቸው ሳትጠይቅ ለእግዚአብሔር ልጆች አንዳች ነገርን አትሰጣቸውም:: የይሁዳ ንጉሥ አክአብ በሬዎችንና በጎችን እንዲያርድለት በመፍቀዱ ሬማት ዘገለዓድን በተመለከተ አክአብ የሚያቀርብለትን ሐሳብ አልቀበልም ለማለት ይቸግረዋል:: ስለሆነም አማራጩና ደህንነት ያለው መንገድ ለዓለም ባለዕዳ አለመሆን ነው፤ ኢዮሣፍጥ ከአክአብ ጋር አንዳች የሚሠራው ነገር የለውም፤ ራሱንም በንጽሕና መጠበቅ ይችል ነበር፤ ከመማፀኛ ከተሞች አንዷ የነበረችውን ሬማት ዘገለአድን ከጠላት እጅ ማስመለሱ አስፈላጊ መስሎ ቢታይም ጌታ ከአክአብ ጋር አይደለምና መተባበሩ አግባብነት የለውም፤ እንደዚሁም ደግሞ ይህን መልካም ሥራ ይሠራ ዘንድ ኢዮሣፍጥ ከክፉ ጋር መተባበር የለበትም፤ ከዓለም ጋር በእቅዷ ከተባበርን ታላቅ ከሆነው ውድቀቷ ጋርም መገለጣችን አይቀርም::

ሬማት ዘገለዓድ ጥንት ነፍሰገዳይ ይሸሽባት ዘንድ የተሰጠች ከተማ ነበረች/ዘዳ4:43/፤ ይህችንም ከተማ ከሶርያ ንጉሥ እጅ ማስመለሱ ደግሞ የአክአብ ዘመቻ ዓላማ ነው፤ ይሁን እንጂ ከዚህ በስተጀርባ የእግዚአብሔርን ሰው ከንጽሕናና ለእግዚአብሔር ተለይቶ ከመኖር ጎዳና አታሎ ለማውጣት እስከተገለገለባት ድረስ ለከተማዋ መወሰድ ደንታ የሌለውን ጠላት ሤራውን እንመለከታለን፤ ዲያብሎስ ሁልጊዜም በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ውጤታማ ተጽዕኖ የሚያመጡለትን ሃይማኖታዊና በጎሥራ የሆኑ አላማዎችን አጥቶ አያውቅም፤ ከመጀመሪያው ርኩስ የሆኑ አላማዎችን በግልጽ ይዞ አይቀርብም፤ ክርስቲያኑን ለአንዳች ላልተቀደሰ አላማ ከዓለም ጋር እንዲያብር አይደልለውም፤ ምክንያቱም ጠንቃቃ ህሊናው ከወዲሁ ተገንዝቦ እንዲህ ካለው ነገር እንደሚርቅ ያውቃልና፤ በምትኩ የእርሱ መንገድ በሩቁ አንዳች ተፈላጊነት ያለውን ዓላማ ማሳየት ማለትም ዕቅዶቹን በሃይማኖታዊና በበጎ ሥራ ካባ ሸፍኖ ማጥመድ ነው::

ሆኖም በሥራ ላይ እንዲውል ከተደረገ ክርስቲያኖችን ከዚህ ዓለም ሰዎች ማናቸውም ግንኙነት በእርግጠኝነት የሚያድን እውነት አለ፤ ሐዋርያው በመንፈስ ቅዱስ ኢአማንያን «ለበጎ ሥራ የማይበቁ» /ቲቶ1:16/ እንደሆኑ ያስተምረናል፤ ለምትታዘዝ ነፍስ ይህ በቂዋ ነው፤ እንዲህ ከተባሉት ጋር መግጠም አይኖርብንም፤ አብረን እንሥራ ብለው የሚያቀርቡልን ነገር በጎሥራም ይሁን

*(ወደ ገጽ 11 ይዞራል)*

## ዳግመኛ ... ከገጽ 9 የዞረ

በሥጋ የሆነ ነገርን ነው። ሆኖም በማስተዋል ከተመለከትን ሳናያቸውና ሳንዳስሳቸው፣ መኖራቸውን የምናምነው ብዙ ነገሮች አሉ። ከእነዚህም አንዱ ጌታችን ለኒቆዲሞስ በምሳሌነት ያቀረበው ነፋስ ነው። ነፋስ ከወዴት እንደመጣ ወዴትም እንዲሄድ አይታወቅም፤ መኖሩን የምናውቀው ድምፁን በመስማት ነው፤ ከመንፈስ መወለድም በዚህ ዓይነት በማይታይ እና በማይዳሰስ መንገድ የሚከናወንና እኛ በእምነት የምንረዳው ነገር ነው፤ ሆኖም ዳግም በተወለደው ሰው ኑሮ ላይ የዚያ የአዲሱ ሕይወት ባሕርያት በንግግሩና በተግባሩ ላይ ስለሚታዩ ያ ሰው ዳግም መወለዱን በሕይወቱ በሚታዩ ተግባራዊ ምስክርነቶች ማወቅ ይቻላል። ሆኖም «ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም በመንፈስም የሚመረመር ስለሆነ ሊያውቀው አይችልም» ተብሎ እንደተጻፈ/1ቆሮ2:14/ እንደ ኒቆዲሞስ ፊደላዊና በሥጋ የሆነ ነገርን ብቻ የሚያውቅ ዳግም ያልተወለደ ሰው ይህ አይገባውም፤ ሊቀበለውም አይፈልግም፤ ስለዚህም ኒቆዲሞስ «ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?» በማለት ክርክር አዘል ጥያቄውን «መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣህ እናውቃለን» ብሎ ለተናገረለት ለእርሱ ሲያቀርብ እንመለከታለን። ኒቆዲሞስ ትምህርቱ ባይገባው እንኳ ከሰማይ ለመጣው መምህር እንዲህ ያለ ክርክር አዘል ጥያቄ ሊያቀርብ ይገባዋልን? ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ መምህር ሊሆን የማይችል ነገር ይናገራልን? «ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?» ተብሎ የሚ ጠየቅ መምህር እርሱ ነውን? ኒ ቆዲሞስ በማን ፊት እንዳለ ከምን ጊ ዜው ዘነጋው? ነገሩን መረዳት ቢ ያቅተው እንኳ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣው መምህር እርሱ ሁሉን ያውቃል ብሎ በእምነት ለመቀበል ለምን ከበደው? በትንሽ እውቀታችን ሁሉን ከሚያውቀው ከእርሱ ጋር ስንሟገት ብዙ ጊዜ ያባከንን ስንቶች እንሆን!

ከሰማይ የመጣው እርሱ ግን ኒቆዲሞስን እንዲህ ለማለት ተችሎታል። «አንተ የእስራኤል መምህር ስትሆን ይህን አታውቅምን? እውነት እውነት እልሃለሁ የምናውቀውን እንናገራለን ያየነውንም እንመሰክራለን ምስክርነታችንንም አትቀበሉትም። ስለምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ ካላመናችሁ ስለሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ? ከሰማይ ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው»። ይህንን የጌታ ንግግር ማስተዋል ከፍጥረታዊ

(ወደ ገጽ 18 ይዞራል)

## ኢዮሣፍጥና... ከገጽ 10 የዞረ

ሃይማኖታዊ ለውጥ የለውም፤ መጽሐፍ ቅዱስ የማይበቁ ናቸው ካለን ምንም እንኳን እነርሱ እግዚአብሔርን እናውቀዋለን እያሉ ቢናገሩም አዎን «የማይበቁ» ናቸው። ይህ በቂ ሊሆን ይገባል፤ እግዚአብሔር ልባቸው ከእርሱ ለራቀ ሰዎች ሥራ ወይም ለሚያቀርቡት መሥዋዕት እውቅና አይሰጥም፤ መልካም ፍጻሜ ያለውን ለመተግበርም ቢሆን ቤተክርስቲያንም እንደእነዚህ ካሉት ጋር መቀየጥ የለባትም፤ «ራስህን በንጽሕና ጠብቅ» የሚለው ለሁላችንም ጠቀሜታ ያለው ምክር ነው፤ «መታዘዝ ከመሥዋዕት ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል»/1ሳሙ15:22/፤ ሬማትን ከሶርያ እጅ ማስመለስ የሚሳካለት ቢሆን ኖሮ እንኳን ለኢዮሣፍጥ ከዚህ ይልቅ ከማናቸውም የአክአብ ርኵሰት ጋር ከመነካካት ራሱን በንጽሕና መ ጠበቅ ይበልጥ የሚሻልና ተቀባይነት ያለው ሥራ ይሆንለት ነበር።

ይሁን እንጂ ኢዮሣፍጥ ይህን አሳማሚ በሆነ ልምምድ ሊማር ይገባው ነበር፤ ብዙዎቻችንም የምንማረው በዚህ ዓይነት ነው፤ ስለአንድ እውነት የተወሰኑ ነጥቦች ብዙ እንናገራለን፤ ነገር ግን በተግባራዊ ልምምድ እንደተማርናቸው የምናውቀው ግን ጥቂቱን ነው፤ ኢዮሣፍጥ በሥራው ጅማሬ ላይ ራሱን በእስራኤል ላይ ሲያጠነክር ከእስራኤል በከፋው ወጥመድ ስለሚያዝበት መንገድ የሚያውቀው አልነበረም። ከክፉ ለመጠበቅ የሚያስችለው የታመነው መንገድ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ማድረግ ነው፤ ክፉ የሆነውን ነገር በእግዚአብሔር የቅድስና ብርሃን ስንመለከተው የምናየው የምናደርገውን ነገር ብቻ ሳይሆን መርሆውንም ጭምር ነው፤ መርሆው ተገቢ ካልሆነ ደግሞ ውጤቱ ምንም ይሁን ምን ከዚያ ነገር ጋር ምንም ህብረት አይኖረንም፤ ሆኖም ክፉን በዚህ ዓይነት ከራስ ለማራቅ ነፍስ በእግዚአብሔር ፊት ብዙ ቆይታ ማድረግ ይኖርባታል፤ ይህም ብዙ መንፈሳዊነት፣ የበዛ ራስን መግዛት፣ የበዛ ጸሎትና ንቃትን ይጠይቃል፤ ጌታም እነዚህን ሁሉ፣ እንደዚሁም ንቁ ስሜት ያለውና በክፉት ላይ ከሩቁ የሚነቃ ህሊናን ይሰ ጠናል።

የሚፈጸመው ስህተት በእግዚ አብሔር ልጆች ላይ የሚያስከትለው አሳዛኝ ውጤት ምን እንደሚሆን መጀመሪያ ላይ ግምቱ አይኖረንም፤ ሁል ጊዜ ውጤቶቹ በሙሉ አይታዩንም፤ ጠላት ግን ጉዳቱ በስህተት በወደቀው ላይ ብቻ ሳይሆን ለሚያምኑትና በዚያ ሰው ተጽዕኖ ሥር ለወደቁት ለሌሎች ጭምር እንዲተርፍ አድርጎ በጉዳዩ ስለመገልገሉ ጥንቃቄና ቅድመ ዝግጅት ያደርጋል። ኢዮሣፍጥ በዚህ ወጥመድ ውስጥ የወደቀው ለብቻው አልነበረም፤ ሌሎችንም ወደዚያው መርቶ እንዲያዙበት አድርጓል፤ «እኔ እንደአንተ ነኝ» አለ፤ በተጨማሪም «ሕዝቤም እንደ ሕዝብህ ናቸው» አለ፤ ለእግዚአብሔር ሰው እንዲህ ባለው ዝቅተኛ ስፍራ ላይ ራስን ማስቀመጥ ምንኛ አሳዛኝ ነው! ለእግዚአብሔር ሕዝብም ወደዚህ ስፍራ መግባት እንደምን የከፋ ነው! ኢዮሣፍጥ «እኔ እንደ አንተ ነኝ» አለ፤ ይህ ቃሉ ግን እርሱ እንደተናገረው አልሆነም፤ እግዚአብሔር በአክአብ እንደፈረደ በእርሱ አልፈረደም፤ ልጓም የሌለው አካሄዱ ባስከተለበት አሳዛኝ ውጤት ውስጥም እንኳን ሆኖ እውነተኛ የሆነው ደህንነቱ ከዚህ ላይ ነው፤ የአክአብን እቅድ ሊፈጽም ከአክአብ ጋር ቢያብርም የሕይወቱ ፍጻሜ እንደአክአብ አልነበረም፤ አክአብ በጦር ሲወጋ እርሱ እንደአክአብ አልነበረም፤ ውሾች የአክአብን ደም ሲልሱ እርሱ እንደአክአብ አልነበረም፤ ጌታ እርሱን ከአክአብ እንዲለይ አድርጎታልና።

ነገር ግን ለሃይማኖታዊ ነገርም ይሁን ለበጎሥራ ወይም ለማናቸውም አላማ ክርስቲያን ከዓለም ጋር ሲቀናጅ በተግባር ኢዮሣፍጥ ለአክአብ እንዳለው «እኔ እንደአንተ ነኝ» እያለ እንደሆነ ልብ ልንል ይገባናል፤ ክርስቲያን አንባቢም «ይህ ትክክል ነውን?» ብሎ ራሱን ይጠይቅ፤ ይህንንስ ለማለት ዝግጁ ነውን? ምናልባት የምንተባበረውን ሰው ማንነት በዚህ መልኩ ማጥናቱ በሌላው ላይ መፍረድ አይሆንምን? ብለው የሚጠይቁ ይኖሩ ይሆናል፤ በእርግጥ እዚህ ላይ «በሌሎች ላይ ልንፈርድ አይገባም» ሲባል እንዲህ ዓይነቱን የሚመለከት አይደለም፤ ኢዮሣፍጥ ከሬማት ሲመለስ ነቢዩ ኢዩ ከመንገድ ላይ ጠብቆ «ከሐዲውን ታግዛለህን? ወይስ እግዚአብሔርን የሚጠሉትን ትወዳለህን?» ሲል ከተናገረው ቋንቋ እንደምንረዳው ኢዮሣፍጥ በአክአብ ላይ መፍረድ ነበረበት፤ በሌላው ላይ ሳይፈርድ ከሐዲውን ወይም እግዚ አብሔርን የሚጠላውን እንዴት ለይቶ ማወቅ ይችላል? እርግጥ ነው በውጭ ባሉት ላይ ልንፈርድ መብት የለንም፤ ይሁን እንጂ በምንተባበራቸው ላይ ልንፈርድ ግዴታ አለብን፤ ይህ ደግሞ በጥቂቱም እንኳን አንዱ በሌላው ላይ ያለውን ብልጫ የሚያሳይ አይደለም፤ ጉዳዩ «እኔ ካንተ ይልቅ ቅዱስ ነኝና ከእኔ ርቀህ ቁም» የሚል ሳይሆን «እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ ተለይቼ መቆም አለብኝ» የሚል ነው፤ ይህ እውነተኛው መርህ ነው፤ ከታወቀ ክፋት የምንለየው በእኛ ማንነት ላይ ተመሥርተን ሳይሆን በእግዚአብሔር

(ወደ ገጽ 13 የዞረ)

## የአጥቢያ .... ከገጽ 6 የዞረ

ወደጐን በሚኖራቸው መተሳሰብና ፍቅር ላይ ብቻ የተመሠረተ ነው።

በየስፍራው የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በመላዋ አንዲት ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ እንደመሆናቸው መጠን በእምነት፣ በትምህርት፣ በሥነ ምግባር እና በሚያከናውኗቸው የአምልኮ፣ የጸሎት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ እና የቃል አገልግሎት ስብሰባዎች ይዘት አንድ ሊሆኑ ይገባቸዋል። በአንዲት አጥቢያ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞች እንጀራ በሚቈርሱ /በጌታ ራት በሚካፈሉ/ ጊዜ በዓለም ሁሉ ካሉ አማኞች ጋር ያላቸውን አንድነት ይገልጣሉ። «..አንድ እንጀራ ስለሆነ፦ እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋ ነን፤ ሁላችን ያን አንዱን እንጀራ እንካፈላለንና» ተብሎ የተጻፈው ቃል ይህንን ያስረዳናል/1ቆሮ10:17 -18/። ስለሆነም በአንዲት አጥቢያ ጉባዔ የሚሰበሰቡ አማኞች በዓለም ሁሉ በሞላችው በክርስቶስ አካል ውስጥ መሆናቸውን ሳይዘነጉ የመላይቱን ቤተክርስቲያን አንድነት ሊጠብቁ ይገባቸዋል። በአንዲት አጥቢያ ቤተክርስቲያን የሚሰበሰቡ አማኞች እርስ በእርሳቸው ያላቸውን አንድነት ሊያጸኑና ሊጠብቁ የሚገባቸውን ያህልም በሌሎች አካባቢዎችም ከሚሰበሰቡ አማኞች ጋር ያላቸው ኅብረትና አንድነት ተጠብቆ እንዲኖር መትጋት አለባቸው። በኤፌ4:3-4 ላይ «በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ። በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት/እምነት/፣ አንዲት ጥምቀት፣ ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ» ተብሎ የተጻፈው ቃል «አንድ አካል» ተብላ በተገለጠችው በመላይቱ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሊኖር የሚገባውን «የመንፈስ አንድነት» ያስተምረናል። ይህም የመንፈስ አንድነት በቅዱሳት መጻሕፍት የተመዘገበን የክርስቶስንና የሐዋርያትን ትምህርት በአንድ ልብና በአንድ መረዳት በማመን እንዲሁም በአምልኮና በጸሎት ስብሰባዎች ባለው መለኮታዊ ሥርዓት ቃሉ በሚለው በአንድ መንገድ በመሄድ የሚገለጥ /የሚታይ/ ነው።

በአንዲት አጥቢያ ቤተክርስቲያን የስህተት ትምህርት ወይም ልዩ ወንጌል ገብቶ አማኞችን ቢያውክ ችግሩ የዚያች ጉባዔ ብቻ ሳይሆን የመላይቱ ቤተክርስቲያን በመሆኑ በሌላ ስፍራ ያሉት አብያተክርስቲያናትንም ይመለከታቸዋል፤ በሐዋ.ሥ. ምዕራፍ 15 ላይ እንደምናነበው በአንጾኪያ ቤተክርስቲያን ውስጥ «እንደሙሴ ሥርዓት ካልተገረዛችሁ ትድኑ ዘንድ አትችሉም» ብለው ያስተምሩ የነበሩ የሐሰት አስተማሪዎች የፈጠሩት ችግር በኢየሩሳሌም በሐዋርያትና በሽማግሌዎች እንዴት እንደተፈታ እናነባለን። በአንጾኪያ ቤተክርስቲያን የገባው የስህተት ትምህርት በኢየሩሳሌምም ሆነ በሌሎች ቦታዎች ያሉት አማኞችን የሚነካ በመሆኑ መንፈስ ቅዱስ በሚቆጣጠረው ስብሰባ በተደረገ ምክክር መዳን በሙሴ ሕግ እንዳልሆነ አሕዛብም በኢየሱስ ካመኑ ባይገረዙም «መዳን» እንደሚችሉ እንዲሁም ለጣዖት ከተሠዋ ከደምም፣ ከታነቀም፣ ከዝሙትም እንዲርቁ የሚገልጽ ውሳኔ ተወሰነ፤ ውሳኔውም በጽሑፍ ለአንጾኪያ ቤተክርስቲያን አማኞች ተላከ። የተላከውም ከቤተክርስቲያን በተመረጡት በይሁዳና በሲላስ እጅ ነበር፤ ይሁዳና ሲላስም ይህንኑ ተልእኮአቸውን በሚገባ እንዳከናወኑ እናነባለን /የሐ.ሥ15:22-35/። እዚህ ላይ ምንም ዓይነት ድርጅታዊ መዋቅር እንደሌለ ልብ ሊባል ይገባል፤ በአንጾኪያ ጳውሎስንና በርናባስን የሚከራከሩና አማኞችን የሚያናውጡ ሰዎች በመነሣታቸው እነጳውሎስ ከሽማግሌዎች ጋር ከአንጾኪያ ቤተክርስቲያን ተልከው ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ከሐዋርያትና ከሽማግሌዎች ከቤተክርስቲያንም ጋር ተመካክረው ለችግሩ መፍትሔ እንዲሰጡበት ተደርጓል፤ ይህ በፍጹም ፈቃደኝነትና በመተሳሰብ፣ በወንድማማች ፍቅር ላይ የተመሠረተና የመንፈስ አንድነትን ለመጠበቅ ከመትጋት የተደረገ አሠራር ነው።

በዘመናችን ብዙ የስህተት ትምህርቶች በዙሪያችን እየተሠራጩ ብዙዎችን የዋሃን አማኞችንም እያናወጡ የሚገኙበትን ሁኔታ እንመለከታለን፤ አንዲት አጥቢያ ቤተክርስቲያን በዓለም ሁሉ ካሉ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ባላት የእምነትና የትምህርት አንድነት የምታምን በመሆኗ የሚያናውጥ ልዩ ወንጌል/የስህተት ትምህርት/ ሲከሠት ከሌሎች አጥቢያ ቤተክርስቲያናት ጋር በመሆን የጋራ መፍትሔ ለመስጠትና በተረዱት እውነት ጸንቶ ለሌሎችም ለማዳረስ በአንድ መንፈስ መጋደል ይገባታል። ይህንን ለማድረግ ከወንድማማችነት አሠራር በቀር ምንም ዓይነት ድርጅታዊ ሰንሰለት ከሌሎች አጥቢያዎች ጋር እንዲያስተሳስራት አያስፈልግም።

በሌላ በኩል ደግሞ ቁሳዊ በሆኑ ነገሮች መረዳዳት/መደጋገፍ/ የሚያስፈልግበት ጊዜ ይኖራል። ይህም ቢሆን ያለምንም ድርጅታዊ መዋቅር ሲከናወን እንደነበር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናነባለን። በአካይያና በመቄዶንያ የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት በኢየሩሳሌም ቅዱሳን መካከል ያሉትን ድሆች ይረዱ ዘንድ በወደዱ ጊዜ በሐዋርያው በጳውሎስና በቲቶ አስተባባሪነት የገንዘብ መዋጮ አድርገው ነበር/ሮሜ15:25-27፤ 2ቆሮ8:1-7/። ይህንንም እርዳታ እንዲያሰባስቡ የተመረጡ ከቲቶ ሌላ ሁለት የታመኑ ወንድሞች ነበሩ/2ቆሮ8:16 -23/፤ ከዚያም የተሰበሰበው ገንዘብ በጳውሎስ አማካኝነት በኢየሩሳሌም ቅዱሳን መካከል ላሉት ድሆች ምጽዋት ተደርጎ ተሰጥቷል። ይህ ሁሉ ሥራ ሲሠራ በመዋቅር የተዘረጋ ድርጅታዊ አሠራር አልነበረም፤ በመካከል ከነበረ ፍቅርና መተማመን እንዲሁም መተሳሰብ ለእግዚአብሔርም ከነበረ እውነተኛ መታዘዝ የተነሣ የተፈጸመ ነው እንጂ። ዛሬም ሊሆን የሚገባው እንዲሁ ነው፤ አማኞች በአጥቢያ ቤተክርስቲያናቸው ገንዘብ እያሰባሰቡ እንደ አቅማቸው መጠን በሌላ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ያሉትን ድሆች ቅዱሳንን በሚያስፈልጋቸው ሁሉ ሊረዱ ይችላሉ፤ ምንም ዓይነት ድርጅታዊ አሠራር በሌለበት ሁኔታ የወንድማማችነት ፍቅር ብቻውን ይህን ለማድረግ ያስችለናል።

## ማጠቃለያ

በየአጥቢያው የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ወደ ላይ ራስ ከሆነው ክርስቶስ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ስላላቸው የሚመሩት በእርሱ መሆኑን ተመልክተናል፤ እንደዚሁም ወደጐን እርስ በእርሳቸው በወንድማማች ፍቅር ላይ የተመሠረተ ግንኙነት እንዳላቸውም አይተናል። ከምድራዊ አሠራር ተለይተን በክርስቶስ አካል ውስጥ ባለው መንፈሳዊ አሠራር ለመኖር ስንታዘዝ የሚሆነው ነገር ይህ ነው። ለክርስቶስ የነበራትን ታማኝነቷን ባጐደለችዋ ቤተክርስቲያን ግን ዓለማዊ አሠራር ከገባባት ዘመናት ተቈጥረዋል፤ ከ4ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ከዓለማውያን ነገሥታት ጋር ከተጋባች ወዲህ በየደረጃው ከዋና ከተሞች ጀምሮ በክፍለ ሀገርና በየከተማው እስከ ገጠር መንደሮች ድረስ በድርጅታዊ አሠራር ተዋቅራ ራስዋ በሾመቻቸው ባለሥልጣናት ወደመመራት ገብታለች፤ ይህም በአንዲት ከተማ ወይም መንደር ያለች ጉባዔ የግድ ወደ ድርጅታዊ አሠራር እንድትገባ አድርጓታል። በሰማይ ላለው ራስ ታማኝነቷን የምታሳይ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ግን እንደቀድሞው ሁሉ በመንፈሳዊ መንገድ ብቻ በእርሱ በክርስቶስ እና በመንፈሱ እየተመራች ከወገኖችም ጋር በፍቅር እየተገናኘች ለመኖር ትታዘዛለች። አንባቢው አንዲት የአጥቢያ ቤተክርስቲያን እንደምን መሆን እንዳለባት መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውንና በአሁኑ ወቅት ሰው በምን መልክና እንደምን እያደረጀት እንዳለ በውል ይረዳ ዘንድ በገጽ 19 ግርጌ ላይ የሚገኘውን ንጽጽር ይመልከት።

## ኢዮሣፍጥ...*ከገጽ 11 የዞረ*

ማንነት ላይ ተመሥርተን ነው፤ እርሱ «እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ» ብሏል።

ኢዮሣፍጥ ግን ይህንን ተለይቶ መኖርን ሊጠብቅ አልቻለም፤ እናም አስቀድሞ እንደተጠቆመው ራሱን ለውድቀት ዳርጎ ሌሎችንም ወደ ውድቀት መራ፤ ከዚህም እጅግ የከበረን ትምህርት እንማራለን፤ ኢዮሣፍጥ አስቀድሞ በነበረው መንፈሳዊ ትጋት ይህ ነው የሚባል ታላቅ ተጽዕኖ በሕዝቡ ልብ ላይ አሳድሮ እንደነበር መገመት እንችላለን፤ በተወሰነ ደረጃ እንዲወዱትና እንዲተማመኑበት አድርጓል፤ በእርግጥ በመሰጠት የሚተጉ ሰዎች ሊፈቀሩና ሊታመኑ ይገባል፤ ነገር ግን የግለሰቦች ተጽዕኖ የሚያመጣውን አደጋ እጅግ ታላቅ በሆነ ቅናት ነቅተን መጠበቅ ይኖርብናል፤ «ሕዝቤ እንደ ሕዝብህ» ነው ማለት የሚቻለው በሕዝቡ ላይ ከልክ ያለፈ ተጽዕኖ ያለው ሰው ብቻ መሆኑ አያጠራጥርም፤ «እኔ እንደ አንተ ነኝ» ማለት ይችላል፤ ሆኖም ግን እንዲህ ያለ ሰው ባይሆን ከዚህ ያለፈ ነገር ማለት አይችልም ነበር፤ ነገር ግን ከልክ ያለፈ ተጽዕኖው በተናጠል ሥራ ላይ ሲውል እርሱን ብርቱ የክፋት መሣሪያ አደረገው፤ ሰይጣን ደግሞ ይህንን ያውቃል፤ ዒላማውን ያውቃል፤ አንድ ተራ በሆነ የይሁዳ ሰው ላይ አላነጣጠረም፤ ይልቁኑ ዝናና ተጽዕኖ ያለውን ሊያገኝ ፈለገ፤ ምክንያቱም እርሱን ከመንገድ ማውጣት ከቻለ ብዙ ሌሎች ከእርሱ ጋር እንደሚሳሳቱ ያውቃልና።

አዎ ሰይጣን ዒላማውን አልሳተም፤ ያለጥርጥር ብዙዎች «በአክአብ ዘመቻ ብንሳተፍ ምን ጉዳት አለው?» ብለው ይሆናል፤ ምክንያቱም አንዳች ጉዳት ቢኖርበት ንጉሥ ኢዮሣፍጥን የመሰለ መልካም ሰው ባልተባበረ ነበር ብለው ያስባሉና፤ እንደዚሁም እርሱን በዚያ እስካየንው ድረስ ስለጉዳዩ መጨነቅ የለብንም ይሉ ይሆናል። በሌላ በኩል ደግሞ እንዲህ ያለ ቋንቋ በኢዮሣፍጥ ዘመን የለም ብንል እንኳ በእርግጥ ይህ አመለካከት በዘመናችን የብዙዎች ቋንቋ ነው፤ «እንደእነዚህ ያሉ መልካም ሰዎች ያሉባቸውና የተሳተፉባቸው እንዲህና እንዲያ ያሉ ነገሮች እንደምን የተሳሳቱ ሊሆኑ ይችላሉ?» ሲሉ ክርስቲያኖች የሚናገሩት ምንኛ ብዙ ጊዜ ነው! ይህ ዓይነቱ ምክንያት በፍጹም የተሳሳተ ነው፤ እንዲያውም ከተሳሳተ አቅጣጫ መጀመር ነው። ሌሎች ያሻቸውን ያድርጉ፤ እኛ ግን በመርህ ለመኳዝ ከእግዚአብሔር ተጠያቂነት አለብን፤ በጸጋና በትሕትና ነገር ግን ሙሉ በሙሉ የሌሎችን አካሄድ ከግምት ሳናስገባ የምናደርገውን ነገር በተመለከተ ስለተከተልነው መንገድ አግባብነት ያለውና ትክክለኛ የሆነ ምክንያት ልንሰጥ ይገባናል፤ በተጨማሪም መልካም ሰዎችም ከትክክለኛ መንገድ ሊወጡና የተሳሳተ ነገር ሊሠሩ እንደሚችሉ በሙላት እናውቃለን፤ ስለሆነም የምንመራባቸው አልነበሩም ወይም አይሆኑምም፤ «እርሱ ቢቆም ወይም ቢወድቅ ለገዛ ጌታው ነው»/ሮሜ14፡4/፤ በተለይ ከታመነ ዓላማ ጋር የሚያስፈልጉን ነገሮች መንፈሳዊ አእምሮ፣ በእግዚአብሔር ቃል የተነቃቃ ህሊና፣ እውነተኛ የሆነ በግል የምንወስደው የኃላፊነት ስሜት ናቸው፤ እነዚህ ነገሮች ከሌሉን መንገዳችን ጉድለት ያለው ይሆናል።

እንደ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ ያለና ካላቸው ስፍራ የተነሣ በጠባያቸው ሰፊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ጥቂቶች ናቸው ሊባል ይችላል፤ ይህንንም ለመረዳት በዚህ ዘመን በሚያሳዝን ሁኔታ በተረሳ አንድ እውነት ላይ ጥቂት መቆየት ያስፈልጋል፤ ይህም እውነት የክርስቶስ አካል አንድነትና የእያንዳንዱ አማኝ ጠባይ ደብዛዛም ቢሆን በአካሉ ላይ የሚያሳድረው ውጤት ነው።

ቤተክርስቲያን በምድር ላይ አንድ ስለመሆኗ የሚናገረው ታላቅ እውነት በእጅጉ መንፈሳዊ በሆኑና በተማሩ የጌታ ሕዝቦች ዘንድ እንኳን በአግባቡ መረዳትን አለማግኘቱና ቸል መባሉ ሊፈራ ይገባል፤ የዚህ ምክንያቱም እንዲህ ባሉ ሰዎች ዘንድ ቤተክርስቲያን አንድ አካል መሆኗን የሚገልጸው ይህ ዶክትሪን የሚታየው ቤተክርስቲያን በአዲስ ኪዳን ከተገለጠችበት ሁኔታ አንጻር ሳይሆን አሁን ካለችበት ሁኔታ አንጻር ስለሆነ ነው፤ ስለዚህም የቤተክርስቲያን አንድነቷ በእነዚህ ሰዎች ዘንድ መረዳትን ሊያገኝ አልቻለም፤ ይሁንና ስለዚህ ጉዳይ ቅዱሳት መጻሕፍትን መመሪያ ብናደርግ ምንም ችግር አይገጥመንም፤ በዚያም «አንድም ብልት ቢሠቃይ ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ይሠቃያሉ»/1ቆሮ12፡26/ ይላል፤ በኢዮሣፍጥ ዘመን የክርስቶስ አካል አልነበረችምና ይህ መርህ ያን ጊዜ ሥራ ላይ ሊውል አይችልም፤ በዚያን ጊዜ ብልቶች በእግዚአብሔር መጽሐፍ የተጻፉ ነበሩ፤ «ገና አልተሠሩምና» /መዝ139፡16/፤ ነገር ግን በእግዚ አብሔር ዓላማ ውስጥ ነበሩ፤ ያ ዓላማ ግን በኢዮሣፍጥ ዘመን እውን አልሆነም፤ ስለሆነም ብዙዎች በኢዮሣፍጥ ተመርተው ወደስህተት ቢሄዱም ይህ የሆነው ከላይ በተቀመጠው ምንባብ መሠረት አይደለም፤ ብዙዎች ወደሥቃይ የገቡት አንድ አካል ስለሆኑ ከአንዱ ብልት ጋር ለመሠቃየት ሳይሆን የአንዱን ምሳሌነት ስለተከተሉ ነው፤ ይህ ልዩነት ደግሞ ተገቢውን መረዳት ሊያገኝ ይገባዋል፤ ምንም ያህል የማይታወቅ ቢሆንም እንኳ በአካሄዱና በጠባዩ በሁሉም የቤተክርስቲያን ብልቶች ላይ ተጽዕኖ የማያሳድር የቤተክርስቲያን አባል/ብልት/ የለም፤ «አይሁድ ብንሆን፣ የግሪክ ሰዎችም ብንሆን፣ ባሪያዎች ብንሆን፣ ጨዋዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድጠ ንሆን ተጠምቀናልና፤ ሁላችንም አንድ መንፈስ ጠጥተናል» /1ቆሮ12፡13/። ስለሆነም አንድ ክርስቲያን በግዴለሽነት የሚመላለስ ከሆነ፣ በህብረት የማይተጋ ከሆነ፣ በ ጸሎትና በጥንቃቄ የማይተጋ ከሆነ፣ ራሱን የማይመረምር ከሆነ በእርግጥ መላውን አካል ይጎዳል፤ በተቃራኒው በመንፈሳዊ ጤንነትና ትጋት ሲመላለስ የሁሉንም በረከትና ጥቅም ያሳድጋል።

ኢዮሣፍጥ የአክአብን ማባበል ያለ ችግር አልተቀበለውም፤ «የእግዚአ ብሔርን ቃል አስቀድመህ ትጠይቅ ዘንድ እለምንሃለሁ» የሚለው አነጋገሩ አእምሮው በጉዳዩ ተጨንቆበት እንደነበር ያሳያል፤ ወዮ! አስቀድሞውኑ «እኔ እንደ አንተ ነኝ፤ ሕዝቤ እንደ ሕዝብህ ናቸው፤ በሰልፍም ከአንተ ጋር እንሆናለን» ካለ በኋላ ምሪት መፈለግ ከንቱ ነው፤ ማድረግ የምንፈልገውን ከወሰንን በኋላ ምሪት መሻት አሳዛኝ ሽንገላ ነው፤ ይህንንም ደጋግመን የምንፈጽመው ምንኛ ብዙ ጊዜ ነው! የድርጊት አቅጣጫችንን ከወሰንን በኋላ ሄደን ጌታን የምንጠይቅበት ጊዜ ምንኛ ብዙ ነው! እንዲህ ያለው አካሄድ ክፉ ነው፤ እግዚአብሔርን በከንፈር እያከበሩ በልብ በእርሱ ላይ ማመፅ ነው፤ እን ጠይቃለን ብለን የምንናገርለትን ምሪት በማግኘት ፋንታ ወደእኛ የሚላኩ የሚያስቱ መናፍስት ሊሆኑ እንደሚችሉ አንጠብቅምን/18፡21/? አክአብ አማካሪዎችን የሚያጣ ሰው አይደለም፤ በፍጥነትም እንደ ልቡ መሻት ሊመክሩት የተዘጋጁ «አራት መቶ ነቢያትን በአንድነት ሰበሰበ»፤ እነርሱም «እግዚአብሔር በንጉሥ እጅ አሳልፎ ይሰጣታልና ውጣ» አሉት፤ ይህ ደግሞ እርሱ የሚፈልገው ነው፤ እንደእነዚህ ባሉ ነቢያት አክአብ ለመርካቱም አንደነቅም፤ ለእርሱ የሚመቹ ናቸውና።

ነገር ግን ኢዮሣፍጥ «እንጠይቀው ዘንድ የእግዚአብሔር ነቢይ የሆነ ሌላ ሰው በዚህ አይገኝምን? ብሎ እንደ ጠየቀው ሁሉ በእነዚህ ነቢያት ፊት በመቅረብ እውቅና መስጠት እንዳልነበረበትም እርግጥ ነው፤ ለጌታ ታማኝ ሆኖ ቢሆን ኖሮ እነዚህ የሐሰት ነቢያት ቀርበው ምክር እንዳይሰጡ መብታቸውን በነፈጋቸው ነበር፤ ወዮ! ሙሉ ፊቱን ለዓለም ሃይማኖትና ለአገልጋዮቿ ሰጠ፤ በታማኝነት ነቢያቱን «ከፊቴ ሂዱ» በማለት የአክአብን ስሜት ሊጎዳ አልፈለገም፤ እነርሱም ትክክለኛ ሰዎች መስለው ቀርበዋል።

ግልጽና ታማኝ የሆነ ምስክርነት በሰይጣን አገልጋዮች ላይ መስጠት የማንችልበት የነፍስ ሁኔታ ውስጥ ራስን መክተት ምንኛ አስፈሪ ነገር

*(ወደ ገጽ 14 ይዞራል)*

## *ኢዮሣፍጥ*...*ከገጽ 13 የዞረ*

*ነው! አንዳንድ ጊዜ «የማንቃወም መሆን አለብን»፣ «የሰዎችን ስሜት መጉዳት የለብንም»፣ «እንደሆነ በሁሉም ቦታ ጥሩ ሰዎች አሉ» ሲባል ይደመጣል፤ ይሁን እንጂ እውነት እውነት ናት፤ እውነትን በሐሰት ወይም ሐሰትን በእውነት መለወጥ አንችልም፤ ነገር ግን ወደዚህ ክፉትን በግዴለሽነት ወደመመልከት የሚመራን ሌላ ነገር ሳይሆን ከዓለም ጋር ለመተባበር የመፈለጋችን ስውር መሻት ነው፤ ሆኖም ከዓለም ጋር ለመተባበር ከፈለግን ደግሞ ማድረግ ያለብን የራሳችንን ነገር በማጣት እንጂ የእግዚአብሔርን እውነት በመሠዋት አይደለም፤ ብዙውን ጊዜ «እውነትን በሚስብ መንገድ እናቅርብ» ተብሎ ግፊት ይደረጋል፤ ሆኖም እውነት ራሷ ፈጽሞ ከዓለም ብትወገድ ደስ ለሚሰኙ ሰዎች እውነትን ከጣዕማቸውና ከጠባያቸው ጋር የምትጣጣም ለማድረግ ሲባል የሚደረገው ጥረት እውነትን ተለዋዋጭ፣ ተለጣጭ፣ ወደተፈለገው ቅርጽ ተቀያሪ፣ ወይም ወደማንኛውም ርዝመት መሳብ የምትችል እንድትሆን የሚያደርግ ሙከራ ነው፡፡*

*ይሁንና እውነት እንደዚህ ልትሆን አትችልም፤ ወደዚህ ዓለም የፍላጎት ደረጃ እንድትወርድ ማድረግ አይቻልም፤ የያዟት ሰዎች እንደዚህ አድርገው ሊጠቀሙባት ቢፈልጉም እርሷ ግን ሁልጊዜ እንደነበረው አለምንና አካሄዷን በመቃወም ንጹሕ፣ ቅዱስና ታማኝ የሆነ ምስክርነትን ትሰጣለች፤ ድምጿ ታማኝ ባልሆኑ መስካሪዎቿ ተግባር ካልታፈነም በግልፅ ትናገራለች፤ ኢዮሣፍጥ አክአብን ደስ ለማሰኘት ብሎ ዝቅ ወዳለ ደረጃ በመውረድ ለእነዚህ የሐሰት ነቢያት እውቅና ከሰጠ ለእግዚአብሔር የሚሆንን አንዳች የተለየ ምስክርነትን ሊገነዘብ የሚችል ማን ነው? ሁሉም የጋራ ወደ ሆነ ወደ አንድ ደረጃ ዘቀጠ፤ ጠላትም ሁሉን ለራሱ አደረገ፤ የእውነት ድምፅ ጸጥ እንዲል ተደረገ፤ ነቢያቱ በሐሰት ተነበዩ፤ እግዚአብሔርም ተረሳ፤ ሰዎች በዚህ መንገድ ሲሄዱ ደግሞ ሁሌም የሚሆነው እንደዚሁ ነው፡፡*

*ስለሆነም እውነትን ለዓለማውያን እንድትመች አድርጎ የማቅረብ ጥረት ውጤቱ ሙሉ በሙሉ ውድቀት ሆኖ ይጠናቀቃል፡፡ እውነትን ለዓለም የምትመች ማድረግ አይቻልም፤ በራሷ ሰማያዊ ከፍታ ላይ ትቁም፤ ቅዱሳንም በሙላትና በጽናት አብረዋት ይቁሙና ኃጢአተኞችንም ወደእነርሱ ይጥሩ፤ ነገር ግን ዝቅ ወዳለው የዓለም የተዋረደ ጠባይ በመውረድ በውስጣቸው ያለው እውነት ኃይልን እንዲያጣ አያድርጉ፤ አካሄዳችንና የእግዚአብሔር እውነት የማይመሳሰሉ ከሆኑ ደግሞ ተቀራራቢ አድርገን ከምናቀርባቸው ይልቅ በሁለቱ መካከል ያለውን ግልፅ ልዩነት እንዳለ ማሳየቱ ይበልጣል፤ ከመንገዳቸው ጋር በመመሳሰል ለዓለማውያን ሰዎች አእምሮ እውነትን ለመንገር ካሰብን በትክክል እውነትን ለስውር ስድብና ንቀት እናጋልጣታለን፤ ኢዮሣፍጥ ከአክአብ አካሄድ ጋር በመመሳሰሉ ወይም የአክአብ የሐሰት ነቢያት ለሚሉት እውቅና በመስጠቱ እውነትን ሊገልጣት አልቻለም፤ ከዓለም ጋር የሚመሳሰል ሰው የክርስቶስ ጠላት፣ የክርስቶስ ሕዝብም ጠላት ነው፤ ከዚህ ሌላ ሊሆን ከቶ አይችልም፤ «ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ለመሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚ አብሔር ጠላት ሆኗል»/ያዕ4፡4/፡፡*

*ንጉሥ ኢዮሣፍጥን በተመለከተ ይህ ምንኛ በሙላት እውን ሆኗል! የእግዚ አብሔር ባሪያ የሆነውን ሚክያስን ለሚጠላ ለአክአብ ወዳጅና አጋር ሆነ፤ ከዚህም የተነሣ ምንም እንኳን ራሱ ጻድቁን ምስክር ባያጠቃም ስህተት ሠርቷል፤ ምክንያቱም ክፉውን ንጉሥ ደስ ለማሰኘትና ከአራት መቶ ክፉ ነቢያት ጋር አንድ ለመሆን ሲል ሚክያስ ባለመዋሸቱ ብቻ መጀመሪያ ሲመታና ቀጥሎም ወደ እስር ሲጣል ከአክአብ ጎን ተቀምጦ ያይ ነበርና፡፡ እርሱ ራሱ የሚሳተፍበትን ዘመቻ በታማኝነት ተቃውሞ በመመስከሩ ወንድሙ ሲደበደብና ወደ እስር ሲጣል በሚያይበት ጊዜ ኢዮሣፍጥ ምን ተሰምቶት ይሆን? ከአክአብ ጋር ያደረገው ወዳጅነት እርሱን ወደዚህ ውጤት እንዲገባ ግድ ብሎታልና የክፉት ምስክር ከመሆን አላመለጠም፤ ከዚህም በላይ ሰው ከዓለም ጋር ሲወዳጅ የሚመጣበት ችግር እንደሚያስበው በቀላሉ የሚታለፍ እንደማይሆን በጥንቃቄ ሊያውቀው ይገባል፤ ምክንያቱም ጠላት በግማሽ ስህተት አይረካም፤ በተቃራኒው ጻድቁን ከእግዚ አብሔር ህብረት እንዲወጣና እጅግ ወደከፋው የክፉት ዳርቻ እንዲደርስ ለማስገደድ ማናቸውንም ጥረት ያደርጋልና፡፡*

*የክፉት መጀመሪያ በግድብ ያለን ውኃ እንደመልቀቅ ነው፤ ትናንሽ ጅማሬዎች የሚፈሩ ውጤቶችን ያስከትላሉ፤ መጀመሪያ ከክፉ ጋር በሩቁ መነካካት፣ ቀጥሎ ደረጃ በደረጃ ክፉን መቅረብ፣ ከዚያም ክፉን መጨበጥ፣ በመጨረሻም ሆን ብሎ ወደ ክፉት ውስጥ ዘሎ በመግባት ሲጠናቀቅ ከእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት በቀር ከዚህ በኋላ ሊያድን የሚችል የለም፡፡ ኢዮሣፍጥ «ለአክአብ ጋብቻ ሆነ»፤ ከዚያም መስተንግዶውን ተቀበለ፤ ከዚያ በኋላ ግልጽ ወደሆነ ህብረት እንዲገባ በአክአብ ማባበል ተወሰደ፤ በመጨረሻም በሬማት ዘገለዓድ ጦርነት ተካፈለ፤ ለአክአብ «እኔ እንደ አንተ ነኝ» ብሎት ነበርና አክአብም ልክ እንደተናገረው እንደቃሉ «ልብሴን ለውጬ ወደሰልፍ እገባለሁ፤ አንተ ግን ልብስህን ልበስ» ብሎት እርሱን ሆኖ ወደሰልፍ እንዲገባ አደረገው፡፡*

*ስለሆነም በዚህ ዓይነት ኢዮሣፍጥ ሰብእናውን ሙሉ በሙሉ ለአክአብ ሰጠ፤ ስለዚህም «የሰረገሎችም አለቆች ኢዮሣፍጥን ባዩ ጊዜ የእስራኤል ንጉሥ ነው አሉ»፤ ይህ ለኢዮሣፍጥ እንደምን ያለ የከፋ ስፍራ ነው፤ ለእርሱ ከእስራኤል ነገሥታት ውስጥ የከፋውን ንጉሥ አክአብን ሆኖ መገኘቱ ከዓለም ሰዎች ጋር መተባበር የሚያስከትለው አደጋ አሳዛኝ ማረጋገጫ ነው፤ ለአክአብ «እኔ እንደአንተ ነኝ» ሲል እንደተናገረው ጌታ አላደረገበትም፤ እርሱ አክአብን መስሎ ቢቀርብና ሰዎች ከአክአብ እርሱን መለየት ባይችሉም ጌታ ኢዮሣፍጥ አክአብ አለመሆኑን ያውቃል፤ ጸጋ እርሱን ለየችው፤ በጠባዩም ይህንን ማረጋገጥ ነበረበት፤ ይሁንና «የሚያመልከውን እንደምን ከፈተና እንደሚያድነው ያውቃልና» እግዚአብሔር ስሙ ቡሩክ ይሁን፤ ታድነው ዘንድ የእግዚአብሔር እጅ ባትዘረጋለት ኖሮ ከማይድንበትና ራሱ ራሱን ካስገባበት ክፉት ውስጥ ባልዳነ ነበር፤ «ኢዮሣፍጥ ጮኸ፤ እግዚ አብሔርም ረዳው አምላኩም ከእርሱ መለሳቸው»፡፡*

*አሁን በኢዮሣፍጥ ሕይወት ውስጥ ወሳኝ በሆነ ነጥብ ላይ እንገኛለን፤ ራሱን ያስገባበትን ስፍራ ያይ ዘንድ ዐይኖቹ ተከፍተዋል፤ የሄደበትን መንገድ የሥነምግባር ክፉት ባይረዳ እንኳን ቢያንስ ቢያንስ ሊደርስበት የነበረውን አደጋ አይቷል፤ በሶርያ አለቆች ተከቦ ሳለ በአክአብ ፈንታ መሆን ምን ማለት እንደሆነ ተሰምቶታል፤ ሆኖም ግን ከተስፋ መቁረጥ ሸለቆ ውስጥ ወደ ላይ ወደጌታ መመልከትና በፍጻሜ ላይ ወደእርሱ መጮኽ በመቻሉ ተርፏል፤ እንዲህ ባይሆን ኖሮ ደግሞ ወደ ልቡ ጠልቆ ይገባ የነበረው የጠላት ፍላጻ የተሳሳተ ህብረት ማድረግ የሚያስከትለውን አሳዛኝ ውጤት ባሳየ ነበር፡፡*

*«ኢዮሣፍጥ ጮኸ»፤ ጩኸቱም እርዳታውን ለሚፈልጉ ሁሉ ጆሮቹ ወደተከፈቱ ጌታ ፊት ደረሰ፤ «ጴጥሮስም ወደ ውጭ ወጥቶ ምርር ብሎ አለቀሰ»/ሉቃ22፡62/፤ ከአባቱ ዘንድ የጠፋው አባካኙ ልጅም «ተነሥቼ ወደአባቴ እሄዳለሁና» አለ፤ አባቱም ሊገናኘው ወደ እርሱ ሮጠ፤ አንገቱንም አቅፎ ሳመው /ሉቃ15፡18-24/፤ ውኃ መያዝ የማይችሉ ጉድጓዶችን ለራሳቸው እንደማሱ ተሰምቶአቸው ወደ እርሱ ወደ ሕይወት ውኃ ምንጭ የሚመለሱትን የተባረከው ጌታ የሚገናኘው እንዲህ ባለ ሁኔታ ነው፤ ስለሆነም በአንዳች መልኩ ከክርስቶስ*

*(ወደ ገጽ 15 ይዞራል)*

## *ኢዮሣፍጥና*... *ከገጽ 14 የዞረ*

ተለይተው በዚህ ዓለም ጅረት እንደተወሰዱ የሚሰማቸው ሁሉ በእውነተኛ ትህትናና በሚፀፀት መንፈስ «እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምጼን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደእርሱ እገባለሁ፤ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ፤ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል» /ራእ3፡20/ ወዳለው ጌታ ቢመለሱ ስፍራ ያገኛሉ፡፡

አክአብን ስንመለከት እንደምን ይለያል! የሞትን ቁስል በእቅፉ ይዞ በሰረገላው ላይ እስከምሽት ራሱን ደግፎ ቢውልም እስከመጨረሻው ድረስ ድካሙን በመሰወር የልቡን መሻት ለመፈጸም ይፈልግ ነበር እንጂ እግዚ አብሔርን አልፈለገም፤ የሽንፈት ጩኸት፣ የንስሐ እንባና ወደላይ አቅንቶ ማየትን በእርሱ ላይ አንመለከትም፤ በሕይወቱ ሙሉ ያደርግ ከነበረው የተለየ በእርሱ ላይ አናይበትም፤ በጌታ ፊት ክፉ ሲያደርግ እንደኖረ እንደዚያው ሞተ፤ ራሱን ለመደገፍ የጣረው ጥረት ምንኛ ፍሬ ቢስ ነበር፤ ሞት ያዘው፤ ምንም እንኳን ለጊዜው እንዳልተጎዳ ለማስመሰል ራሱን ቢያበረታም «ፀሐይ በገባ ጊዜ ሞተ»፤ አሳዛኝ ፍጻሜ! «ክፉትን ለማድረግ ራሱን የሸጠ» ሰው ፍጻሜው ይህ ነው፤ የዓለም ተከታይ ለመሆን የሚፈልግ ማን ነው? ቀጥተኛና ንጹሕ ሕይወት አስፈላጊ መሆኑን ተረድቶ ሲያበቃ ከዓለም አካሄድና ጠባይ ጋር ራሱን የሚያደባልቅ ማን ነው? ሰላማዊና አስደሳች የሆነ የሕ ይወት ፍጻሜ ትክክለኛ መሆኑን ተረድቶ ነገር ግን ከዓለም እድል ፈንታ ጋር ራሱን የሚያያይዝ ማን ነው?

ክርስቲያን አንባቢዎች ሆይ፤ በጌታ እርዳታ የዓለምን ተጽዕኖ ከላያችን ላይ እናራግፍ፤ ከአካሄዷም ራሳችንን እናጽዳ፤ ዓለም ሳናስበው እንዴት እንደምትይዘን አናውቅም፤ ጠላት መጀመሪያ ቀላልና ክርስቲያናዊ ከሆነ ጠባይ ያለያየናል፤ ቀስ በቀስም ወደ ዓለም አመለካከት ጅረት ውስጥ እንዘፈቃለን፤ ስለሆነም ነቢዩ «ናዝራዊያኗ/አለቆችዋ/ ከበረዶ ይልቅ ጥሩ ከወተት ይልቅ ነጭ ነበሩ፤ ገላቸው ከቀይ ዕንቍ ይልቅ ቀይ ነበረ፤ መልካቸው እንደሰንፔር ነበረ፤ /ነገር ግን ከደረሰው ለውጥ የተነሣ/ ፊታቸው ከጥቀርሻ ይልቅ ጠቍሯል፤ በመንገድም አልታወቁም፤ ቁርበታቸው ወደ አጥንታቸው ተጣብቋል፤ ደርቆአል፤ እንደእንጨት ሆኗል» /ሰቆ4፡7-8/ ሲል የተናገረው አስፈሪ ንግግር በእኛ እንዳይደርስብን በተቀደሰ ቅናት፣ በነቃ አእምሮ፣ በክፉት እንዳንያዝ እንጠበቅ፡፡

አሁን ደግሞ በጥቂቱ ምዕራፍ 19ን እንመልከት፤ እዚህ ላይ ኢዮሣፍጥ ካለፈበት ነገር ሁሉ የተገኘውን የተባረከ ፍሬ እናያለን፤ ኢዮሣፍጥ «ወደቤቱ ወደ ኢየሩሳሌም በደህና ተመለሰ»፤ በደህና አመለጠ፤ የጌታ እጅ ከለለችው፤ ከአዳኝ ወጥመድም አዳነችው፤ ምንም እንኳን እርሱ ለአክአብ «እኔ እንደአንተ ነኝ» ቢልም እርሱን ከአክአብ ለለየው ጌታ ውለታ ይሰማዋል ማለት እንችላለን፤ አክአብ በውድቀትና በውርደት ወደ መቃብር ወረደ፤ ኢዮሣፍጥ ግን በደህና ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ ነገር ግን የተማረው ትምህርት እንዴት የተወደደ ነው! ከገደል አፋፍ እንደምን እንደተመለሰ ማሰብ እንደምን ደስ የሚያሰኝ ነው! ይሁን እንጂ ስለሠራው ሥራ እግዚ አብሔር ለእርሱ የሚናገረው ነገር አለው፤ ወደ ኢየሩሳሌም በደህና እንዲመለስ ቢያደርገውና ጠላት እንዳይጎዳው ቢከላከልለትም ስለኃ ጢአቱ ለህሊናው ሊናገር ይፈልጋል፤ በግል ሊያናግረው ከጦር ሜዳ ለይቶ አመጣው፤ «ባለራእዩ የአናኒ ልጅ ኢዩ ሊገናኘው ወጣ፤ ንጉሡንም ኢ ዮሣፍጥን ከሐዲውን ታግዛለህን? ወይስ እግዚአብሔርን የሚጠሉትን ትወዳለህን? ስለዚህ ነገር ቍጣ ከእግዚ አብሔር ዘንድ ሆኖብሃል» አለው፡፡ ይህ ደግሞ እጅግ ከፍ ያለ ጥያቄ ነው፤ ራሱንም ፍሬ አፍርቶአል፤ ኢዮሣፍጥም «ከቤርሳቤህ ጀምሮ እስከተራራማው እስከ ኤፍሬም አገር ድረስ ወደ ሕዝቡ ወጥቶ ወደ አባቶቻቸው አምላክ ወደ እግዚአብሔር መለሳቸው»፤ «በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አ ጽና»/ሉቃ22፡32/ ተብሎ ለጴጥሮስ እንደተነገረው አደረገ፡፡

ጴጥሮስ ይህን አድርጓል፤ ንጉሥ ኢዮሣፍጥም ይህንኑ አደረገ፤ መዋዠቅና ውድቀት በጌታ ርህራኄ ወደዚህ ዓይነቱ ውጤት ሲያመራ የተባረከ ነው፤ ይህን ደግሞ ሊያፈራ የሚችለው ሌላ ሳይሆን መለኮታዊ ጸጋ ብቻ ነው፤ በምዕራፍ 18 ኢዮሣፍጥ በሶርያ የጦር አለቆች ተከቦ ስናየውና አሁን ደግሞ በጌታ ፍርሃት ወንድሞቹን ለማስተማር የምድሪቱን ስፋትና ርዝመት ሲያካልል ስናየው «አቤት የእግዚአብሔር ሥራው» ብለን እንደነቃለን፡፡ እርሱ ግን እንዲህ ላለው ሥራ የተገባ ሰው ነው፤ የግዴለሽነት መንፈስ ከሚያፈራው መራራ ፍሬ በገዛ ሕይወቱ ያየና «የምታደርጉትን ተመልከቱ»/ቁ.6/ ማለት የተቻለው ሰው ነው፤ የተመለሰውና በራሱ ቅዱሱን የካደው ጴጥሮስ ያንኑ ላደረጉት ለሌሎች ሄዶ ሊነግርና ሊያስተምር፣ የእርሱንም ህሊና ከበደል ስላነጻለት ደም ሊመሰክርላቸው የተመረጠ ዕቃ ነበር፡፡

እንደዚሁ የተመለሰው ኢዮሣፍጥም ከሬማት ዘገለአድ ጦርነት ተመልሶ በወንድሞቹ ጆሮ ላይ ከበድ ባለ የማስጠንቀቂያ ድምፅ «የምታደርጉትን ተመልከቱ» ይል ነበር፤ ከወጥመዱ ያመለጠ እርሱ ወጥመዱ እንዴት እንደነበርና እንዴት ከእርሱም እንዳመለጠ ከሁሉ ይበልጥ ሊናገር ይችላል፡፡

አሁን ደግሞ የኢዮሣፍጥን ትኵረት የያዘ በጌታ ጠባይ ውስጥ ለየት ያለ ገጽታ አለ፤ ይኸውም «በአምላካችንም በእግዚአብሔር ዘንድ በደልና ለሰው ፊት ማድላት መማለጃም መውሰድ የለምና» ሲል እርሱ ራሱ የተናገረው ነው፤ ገብቶበት የነበረው ወጥመድ የአክአብ መማለጃ ነበር፤ «አክአብም ለእርሱና ከእርሱ ጋር ለነበሩት ሕዝብ ብዙ በጎችንና በሬዎችን አረደ፤ ከእርሱ ጋርም ወደ ሬማት ዘገለኣድ እንዲሄድ አባበለው»፡፡ ጴጥሮስ የሊቀካህናቱን ግቢ እሳት መሞቅ ተቀብሎ እሳቱን ከሞቀ በኋላ ጌታውን እንደካደ ኢዮሣፍጥም በአክአብ ስጦታ ልቡን በማሞቁ በአክአብ ማባበል በቀላሉ ተወሰደ፤ የዓለምን አየር እየተነፈስን ወይም ስጦታዋን እየተቀበልን በቀዘቀዘ መንፈሳዊነት ዓለም የምታቀርብልንን ማባበልና ሐሳብ እምቢ ማለት አንችልም፤ ራሳችንን በስተውጭ ነጻ አድርገን ስንገኝ ያን ጊዜ የምታቀርብልንን ሐሳብ እምቢ ለማለትና ድለላዋን ለማሸነፍ ራሳችንን በተሻለ ስፍራ ላይ እናገኘዋለን፡፡

ነገር ግን ኢዮሣፍጥ ከተመለሰ በኋላ በእጅጉ ሳያውቀው በመቅረቱ ለውድቀት በተዳረገበት መለኮታዊ ባሕርይ ላይ እንዴት ትኵረት እንዳደረገ መመልከቱ ትምህርት ሰጪ ነው፤ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ማድረግ ከማናቸውም ፈተና ሰውን የሚ ጠብቅ ዋነኛ ነገር ነው፤ ተቃራ ኒውን በእግዚአብሔር ውስጥ የማናገኝለት የምንፈተንበት ምንም ኃጢአት የለም፤ እናም ክፉን ከራሳችን የምናርቀው መልካም ከሆነው ጋር ህብረት በማድረግ ብቻ ነው፤ ይህ ቀላል የሆነ ነገር ግን ጥልቀት ያለው ተግባራዊ እውነት ነው፤ ኢዮሣፍጥ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት እያደረገ ሆኖ ቢሆን ኖሮ ከአክአብ ጋር ህብረት ማድረግን ባልፈለገ ነበር፡፡

የዓለማዊ ህብረት ጥያቄን የምንጠለከትበት ብቸኛ መለኮታዊ መንገድ ይህ ብቻ ነው አንልም፤ ራሳችንን እንዲህ ብለን እንጠይቅ፤ «ከዓለም ጋር ያለን ህብረት ከእግዚአብሔር ጋር ካለን ህብረት ጋር ጎን ለጎን መሄድ ይችላልን? በእርግጥ ጥያቄው ይህ ነው፤ የክርስቶስ ስም ከሚያስገኘው ትርፍ ሁሉ እየተካፈልኩኝ በዚያው ልክ ራሴን ከዓለም ሰዎች ጋር በመደባለቅ እነርሱ በቆሙበት መሠረት ላይ እየቆምኩኝ ያንን ስም ማስነወር እችላለሁን? ብሎ መጠየቅ በእርግጥ አሳዛኝ ጥያቄ ነው፤ ወደ እግዚአብሔር ፊትና «ከሐዲውን ታግዛለህን? ወይስ እግዚአብሔርን የሚ ጠሉትን ትወዳለህን?» ወደሚለው

*(ወደ ገጽ 17 ይዞራል)*

# የጥያቄዎቻችሁ መልሶች

⏭ ለእውነት ጋዜጣ አዘጋጆች፡-

በመጀመሪያ ሰላምና ጤናን እመኝላችኋለሁ። እኔ አዲስ ክርስቲያን ነኝ በመሆኑም እውነት ጋዜጣና ሌሎቹም መጻሕፍቶቻችሁ በእጅጉ ያስፈልጉኛል፤ በመቀጠል አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ እወዳለሁ።

በሉቃ2፡35 ላይ «…በአንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል አላት» ተብሎ ስለማርያም የተነገረው ቃል ምን ማለት እንደሆነ ብታብራሩልኝ ስል በጌታ ፍቅር እጠይቃለሁ።

ፍሬሕይወት አስፋው - ከአዲስ አበባ

<u>ከአዘጋጆቹ</u>፡ ይህን ቃል የተናገረው ሰው የእስራኤልን መጽናናት ይጠባበቅ የነበረው «ስምዖን» የተባለው አረጋዊ ነው። የተናገረውም ለኢየሱስ እናት ለማርያም ነው። ማርያም ህፃኑን ኢየሱስን ወደ መቅደስ ባስገባችበት ቀን ይህ ሰው ኢየሱስን አቅፎ እግዚአብሔርን እየባረከ አመስግኗል። ከዚያም በኋላ ለማርያም «እነሆ የብዙዎች ልብ ሀሳብ ይገለጥ ዘንድ ይህ በእስራኤል ላሉት ለብዙዎቹ ለመውደቃቸውና ለመነሣታቸው ለሚቃወሙትም ምልክት ተሾሞአል፤ በአንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል» አላት /ሉቃ2፡34-35/።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእስራኤል መሢሕ ሆኖ ቢመጣም እስራኤል ግን አልተቀበለችውም፤ እርሱ በእስራኤላውያን ተቀባይነት አለማግኘቱና መከራም የሚቀበል መሆኑ ኢየሱስ ከተወለደ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የተነገረው በዚህ በአረጋዊው በስምዖን ቃል ነው። ኢየሱስ ለእስራኤላውያን «ምልክት» ሆኖ ተነግሯል፤ ምልክትነቱም ማንነታችውን በተለይም የብዙዎቹን የልብ ሐሳብ የሚገልጥ ነው፤ ይህም ማለት የእርሱ በመሢሕነት መሾም የእያንዳንዱን እስራኤላዊ ማንነት ይገልጣል፤ «ለብዙዎቹ ለመውደቃቸውና ለመነሣታቸው ለሚቃወሙትም ምልክት ተሾሞአል» ይላል፤ እግዚአብሔር የሾመውን ይህን መሢሕ ባለመቀበሏ እስራኤል በአሁኑ ጊዜ ወደጐን ተትታለች፤ በእግዚአብሔር ፊት ወድቃለች። የመውደቃቸው ምክንያት እርሱን አለመቀበል እንደሆነ ሁሉ ወደፊት የእስራኤል ቅሬታ የሚድኑትና እንደገና ከወደቁበት የሚነሡት እርሱን በመሢሕነት በመቀበል ነው፤ እንደዚሁም «ለሚቃወሙትም» የሚል ቃል እናገኛለን ይህም በዚያን ከአይሁድ ኢየሱስን የሚቃወሙ ብዙዎች እንደሚሆኑ ያሳያል፤ ይህም በጲላጦስ የፍርድ አደባባይ ተገልጧል፤ ጲላጦስ «ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን እንግዲህ ምን ላድርገው?» ሲላቸው «ሁሉም ይሰቀል» አሉ። ገዢውም «ምነው? ያደረገው ክፋት ምንድር ነው?» አለ፤ «እነርሱ ግን ፡- ይሰቀል እያሉ ጩኸት አበዙ»/ማቴ27፡22-23/። ይህም የእነርሱን ተቃዋሚነት በብርቱ ይገልጣል።

እንግዲህ አረጋዊው ስምዖን «በአንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል» ብሎ ለኢየሱስ እናት ለማርያም የተናገራትን ቃል ከኋላ ካሉት ቃላት ጋር አያይዘን ስንረዳው በነፍሷ የሚያልፈው «ሰይፍ» ሌላ ምንም ሳይሆን ልጇ ኢየሱስ የእስራኤል ህዝብ «ይሰቀል» እያሉ ሲቃወሙና ያም ተቃውሞ አድጎ እርሱ በመስቀል ተሰቅሎ ስታየው በነፍሷ ውስጥ የሚሰማትን ጥልቅ የኀዘን ስሜት የሚመለከት ነው። ሰይፉ የሚያልፈው በነፍሷ ውስጥ እንጂ በሥጋዋ እንዳልሆነ ማስተዋል ያሻል። በነፍስ ውስጥ የሚያልፍ ሰይፍ ደግሞ ፊደል በፊደል የሚታወቀው የሳለ የብረት ሰይፍ ሳይሆን መንፈሳዊ ባሕርይ ያለው ሰይፍ ነው፤ ያም ነፍስን ወግቶና ሰንጥቆ የሚያልፍ ሰይፍ ብርቱ ኀዘን እንደሆነ እንረዳለን። «ጌታም ነፍሴ እስከሞት ድረስ እጅግ አዘነች» እንዳለ በማቴ26፡38 ላይ ተጽፎልናል። እንዲህ ያለ ኀዘን በነፍሷ ውስጥ እንደሚያልፍ ከዚህ ቃል መረዳት እንችላለን። በእርግጥም ጌታ በመስቀል ላይ ተቸንክሮ በተሰቀለበት በዚያን እለት «በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱ የእናቱም እኅት የቀለዮጳም ሚስት ማርያም መግደላዊትም ማርያም ቆመው ነበር። ኢየሱስም እናቱን ይወደው የነበረውንም ደቀመዝሙር በአጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ እናቱን «አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ» ሲላት እንዲሁም ደቀመዝሙሩን «እናትህ እነኋት» ብሎ ነበር፤ በዚህን ጊዜ በእርግጥም የቆሰለ ሥጋውን፣ የፈሰሰ ደሙን እየተመለከተች በነፍሷ ያለፈው የኀዘን ሰይፍ እንዴት ያለ ይሆን? በእናትነቷ ለእርሱ ካላት የበረታ ፍቅር አንጻር ይህ በእርግጥ ሊሆን የሚችል ነው።

// ……………………………//

⏭ ለእውነት ጋዜጣ አዘጋጆች፡-

ከሁሉ አስቀድሞ የእግዚአብሔር ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ፤ ከእናንተ ጋር ተጻጽፌ የጠየቅኋቸውን እውነት ጋዜጣንና የኦሪት ዘጸአት ትርጓሜን ስለላካችሁልን በእግዚአብሔር ስም አመሰግናለሁ፤ የቀረውንም እንደምትልኩልኝ ተስፋ አደርጋለሁ፤ በመቀጠል ለምጠይቃችሁ ጥያቄ መልስ እንደምትሰጡኝ በመተማመን ጥቄዎቼን አቀርባለሁ።

1. እንደሚታወቀው በሀገራችን አንድ ሰው ሲሞት ከሞተ ከ3ኛው ቀን ጀምሮ ተዝካር ይደገሣል፤ በተጨማሪ ሐውልት ተሠርቶ ካህናቱና ምእመናኑ በተሰበሰቡበት ምርቃት ተብሎ ሥርዓተ ጸሎት ይደርጋል፤ ይህንን ሥርዓት በየትኛው መጽሐፍ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ ጠይቄ ሊያስረዳኝ የሚችል ስላላገኘሁ በስፋት የምታውቁ ከሆነ ብታብራሩልኝ፤

2. ስለጾም ማወቅ ፈልጌ ነው፤ በተለመደው ባህል እንደሚታወቀው 7 የተለያዩ አጽዋማት አሉ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግን እነዚህን አጽዋማት የሚገልጽ ምንም ነገር የለም፤ እስኪ ስለ እነዚህ አጽዋማት የምታውቁትን ያህል ብታስረዱኝ መልሱን እጠብቃለሁ፤

አሴተ ድንግል- ከሻኪሶ

<u>ከአዘጋጆቹ</u>፡ ጠያቂያችን የጋዜጣችንና የመጻሕፍቶቻችን አገልግሎት ተጠቃሚ በመሆንሽ ደስ ብሎናል፤ እውነትን ለማወቅ በተነቃቃ ስሜት ውስጥ ሆነሽ በቅንነት ያቀረብሻቸውን ጥያቄዎች ተመልክተን የሚከተለውን ምላሽ አቅርበናል።

1. የመጀመሪያው ጥያቄሽ ተዝካርንና የሐውልት ምርቃትን የሚመለከት ነው፤ አንቺ እንዳልሽው በእርግጥ በአንዳንድ የሃይማኖት ተቋማት ሥርዓቱን የሚገልጽ የተለየ መጽሐፍ ሊኖር ይችላል፤ እኛ ግን የሚገባን ነገር ቢኖር ተዝካርና የሐውልት ምርቃት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሌለ የሰው ሥርዓት መሆኑን ነው፤ ተዝካር ማለት መታሰቢያ ማለት ነው፤ በተለመደው የቋንቋ አጠቃቀም ደግሞ ለሙታን መታሰቢያ እንዲሆን የሚደገስ ድግስ ነው፤ በልማዱ መሠረት በ3ኛው ቀን ተዝካር የሚደገስ አይመስለንም፤ በ7ኛው በ12ኛው በ40ኛው በ80ኛው በመንፈቁና በዓመቱ ብሎም በየ7ዓመቱ ተዝካር የመደገስ ልማድ አለ፤ በኤኮኖሚ ላይ ከሚያደርሰው ቀውስና ከጎጂ ባህልነቱ አንፃር እድሮችም ተዝካርን ለማስቀረት እየጣሩ እንደሆነ ይሰማል፤ ከክርስትና እውነት አኳያ ግን የሙታን መታሰቢያ የሚሆን ድግስ መደገስ እግዚአብሔርን ለሚያመልክ ሰው መንፈስን የሚያሳድፍና ኀሊናን የሚያረክስ ተግባር ነው፤ ምክንያቱም የሚደገሰው ድግስ ለሞቱት ነፍሳት ይጠቅማል ተብሎ ስለሚታሰብ ድርጊቱ ከሙታን መናፍስት አምልኮ ጋር የተቆራኘ ነውና።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ክርስቲያኖች ሲሞቱ ምንም ዓይነት መታሰቢያ ሲደረግላቸው አናይም፤ ለምሣሌ የእስጢፋኖስን ሞት አስመልክቶ የተጻፈው ቃል «በጸሎት የተጉ ሰዎች እስጢፋኖስን ቀበሩት ታላቅ ልቅሶም አለቀሱለት» ከሚል በቀር ተዝካር ደገሱለት፣ ሐውልት አቆሙለት የሚል አናነብም/የሐ.ሥ8፣2/፤ አማኞች ሰው ሲሞትባቸው የሚወዱት ሰው ስለተጠለያቸው እንባቸውን አፍስሰው ሊያለቅሱ ይችላሉ። ጌታ ኢየሱስ አልዓዛር በመሞቱ እንባውን አፍስሶ ነበር፤ አይሁድም «እንዴት

*(ወደ ገጽ 18 የዞረ)*

## ኢዮሣፍጥ ...*ከገጽ 15 የዞረ*

የሚፈትሽ የእግዚአብሔር እውነት ብናመጣው ጉዳዩ በቀላሉ መልስ ያገኛል፤ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት የሌለው ልብ ሊጥለው የማይፈልገውን የሐሰት መሸፈኛ እውነት ገፍፋ ትጥለዋለች፤ የነገሮችን እውነተኛ ጠባያቸውን ማየት የምንችለውም እውነት የማይሳሳት ጮራዋን በመንገዳችን ላይ ስትፈነጥቅ ብቻ ነው።

መለኮታዊ እውነት የአክአብንና የኤልዛቤልን አደራረግ እንዴት ራቁቱን እንዳስቀረው ልብ እንበል፤ ኤልዛቤል በሚዘገንን ክፋቷ ላይ መልካም ካባ ደርባ «ናቡቴ ሞቷል እንጂ በሕይወት አይደለምና በገንዘብ ይሰጥህ ዘንድ እንቢ ያለውን የኢይዝራኤላዊውን የናቡቴን የወይን ቦታ ተነሥተህ ውሰድ» ስትለው በደስታ ነበር፤ ጉዳዩን የፈጸመችው እንዲህ ባለ መንገድ ነው፤ ነገር ግን ጌታ ያየው እንዴት ነበር? «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ገድለህ ወረስኸውን?» /1ነገሥ20/፤ ይህም በእኛ አነጋገር «ገድለህ ዝርፊያ ፈጸምክን?» ማለት ነው፤ እግዚአብሔር እውነታዎችን ያያል፤ በእርሱ ሲመዘኑ ሰዎችና ነገሮች ትክክለኛ ስፍራቸውንና ዋጋቸውን ያገኛሉ፤ በእርሱ ዘንድ ላይ ላዩን የሚታይ ቅብ፣ ማስመሰል፣ መገመት የለም፤ ሁሉም እውነታ ነው፤ የኢዮሣፍጥ ጉዳይም የታየው እንደዚሁ ነው፤ በሰዎች ግምት ሃይማኖታዊ ተደርጎ የሚታየው የእርሱ አካሄድ በመለኮታዊ ግምጋሜ በቀላሉ ከሐዲውን መርዳትና ጌታን የሚጠሉትን መውደድ ነው ተብሏል፤ ሰዎች በጭብጨባ ይቀበሉት ይሆናል፤ ነገር ግን «ቀኊጣ ከእግዚአብሔር ዘንድ» ሆኖበታል።

ይሁንና ኢዮሣፍጥ ውድቀቱ ስላስተማረው ጠቃሚ ትምህርት ሊያመሰግን ይገባዋል፤ ይበልጥ በእግዚአብሔር ፍርሃት እንዲመላለስና ለሌሎችም ይህንኑ እንዲያሳይ አስተምሮታል፤ ይህ የሚናቅ አይደለም፤ እርግጥ ነው በዚህ መንገድ መማር አሳዛኝና አሳማሚ ነው፤ ነገር ግን በውድቀታችንም ስንማር መልካም ነው፤ በአሳማሚ ልምምድም ከዓለም ጋር መቀላቀል የሚያስከትለውን አስፈሪ ክፋት ለሌሎች መንገርም መልካም ነው፤ ዓለማዊ ህብረት የሚያሳድፈን መሆኑን በከፍተኛ ሁኔታ ከተረዳን ለሌሎች ውጠታማ አስተማሪዎች እንሆናለን፤ በሚበልጥ ክብደትም «ተጠንቀቃችሁ አድርጉ» የምንል እንሆናለን፤ ዳግመኛም «በርትታችሁም አድርጉ እግዚአብሔር መልካም ከሚያደርግ ጋር ይሁን» እንላለን/19፡11/።

በምዕራፍ 20 ላይ ኢዮሣፍጥን ከምዕራፍ 18 በተሻለ ሁኔታ ላይ እናገኘዋለን፤ እዚህ ላይ በጠላት እጅ ሲፈተን እንመለከተዋለን፤ «እንዲህም ሆነ፤ ከዚያ በኋላ የሞዓብና የአሞን ልጆች ከእነርሱም ጋር ምዑናውያን ኢዮሣፍጥን ሊወጉ መጡ»፤ ኢዮሣፍጥ የጠላት ዒላማ ሆኖ ከምናየው የአክአብ ቸርነትና መስተንግዶ ዒላማ ሆኖ ስናየው የበለጠ ስጋት ያድርብናል፤ ይህ መሆኑም ትክክል ነው፤ ምክንያቱም በአንደኛው ሁኔታ በቀላሉ በእስራኤል አምላክ እጅ የሚወድቅ ሲሆን በሁለተኛው በሰይጣን ወጥመድ ውስጥ ይወድቃል፤ ትክክለኛው የእግዚአብሔር ሰው ስፍራ ሙሉ ሙሉ ከጌታ ጠላቶች ጋር በተቃርኖ ውስጥ መሆን እንጂ በተዛምዶ ውስጥ መሆን አይደለም።

ከጌታ ጠላቶች ጋር ተባብረን ሳለን መለኮታዊ ርህራኄና ምሪትን ከጌታ ልንጠብቅ አንችልም፤ ስለሆነም ስህተት መሆኑን በሚያውቀው ጉዳይ ላይ የጌታን ምክር መጠየቅ ለኢዮሣፍጥ ባዶ ነገር መሆኑን እናስተውላለን፤ አሁን በፊታችን ባለው ነገር ግን እንዲህ አይደለም። ስለዚህም «እግዚአብሔርን ሊፈልግ ፊቱን ሲያቀና» እና «በይሁዳ ሁሉ ጾምን ሲያውጅ» በእርግጥ ከልቡ ነበር፤ ይህ እውነተኛ ሥራ ነው፤ ከዓለም እጅ እንደሚመጣ ፈተና ያለ ጻድቁን ከዓለም ወደመለየት ስፍራ እንዲሸሽ የሚያደርግ ምንም የለም፤ ዓለም በእኛ ደስ ስትሰኝ ወደእርሷ የመሳብ አደጋ አለ፤ ዓለም ስትጠላን ግን ወደ ጠንካራው ምሽጋችን እንሸሻለን፤ ይህ ደግሞ አስደሳችና ጤናማ ነው። ኢዮሣፍጥ ለሞዓባውያን ወይም ለአሞናውያን «እኔ እንደ እናንተ ነኝ» አላለም፤ እነርሱም እንዲህ እንዲያስብም አያደርጉትምና እርሱም ይህ እንደዚህ እንዳይደለም ያውቃል፤ ስለሆነም ዓለምን በተመለከተ ትክክለኛ ስፍራችንን ማወቅ ምንኛ መልካም ነው!

ኢዮሣፍጥ ወደ ጌታ በጸለየው ጸሎት ውስጥ ሦስት ለየት ያሉ ነጥቦች አሉ/ቁ.6-12/፤

1ኛ. የእግዚአብሔር ታላቅነት
2ኛ. ምድሪቱን በተመለከተ ለአብርሃም የተሰጠው የተስፋ ቃል
3ኛ. የአብርሃምን ዘር ከምድሪቱ ለማባረር የጠላት ሙከራ

ናቸው።

ጸሎቱ መለኮታዊ እውቀት የሞላበት እጅግ የተወደደና ትምህርት ሰጪ ነው፤ በጸሎቱም ጉዳዩን በአብርሃም አምላክና በአሞንና በሞዓብ ልጆች እንዲሁም በሴር ተራራ ሰዎች መካከል ያለ ጥያቄ አደረገው፤ እምነት ሁልጊዜ የምታደርገው እንዲህ ነው፤ ጉዳዩም ሁልጊዜ አንድ ነው፤ «ከሰጠኸን ርስት ያወጡን ዘንድ መጥተዋል» አለ፤ አንተ የሰጠኸንን ሊወስዱ መጥተዋል ብሎ መናገሩ ነው፤ ይህም አስቀድሞ እንደነበረ ቃልኪዳኑን እንዲጠብቅ ጉዳዩን ለእግዚአብሔር መስጠቱ ነው፤ ደግሞም እንደዚህ አለ፤ «አምላካችን ሆይ አንተ አትፈርድባቸውምን? ይህን የመጣብንን ታላቅ ወገን እንቃወም ዘንድ አንችልም፤ የምናደርገውንም አናውቅም ነገር ግን ዓይኖቻችን ወደ አንተ ናቸው»፤ በእርግጥ እንዲህ ባለ ሁኔታ ችግሩን ከእግዚአብሔር ጋር ለሚያደርግ ለእርሱ ከወዲሁ ድል ተጠብቆለታል ማለት እንችላለን፤ ኢዮሣፍጥም ይህንኑ ተገንዝቧል፤ «ከሕዝቡም ጋር ተማክሮ በሠራዊቱ ፊት የሚሄዱትን፣ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ የሚሉትንም የቅድስናውን ውበት የሚያመሰግኑትንም ለእግዚአብሔር የሚዘምሩትንም መዘምራን አቆመ»፤ ጦርነቱ ሳይጀመር ምስጋናን የሚያሰማ ከእምነት በቀር ሌላ አይደለም፤ «እምነት የተስፋን ቃል እርግጠኛ አድርጎ ይቆጥራል»፤ እምነት አብርሃምን እግዚአብሔር ለዘሩ ከነዓንን እንደሚሰጥ እንዲያምን እንዳስቻለው ሁሉ ኢዮሣፍጥን ደግሞ እግዚአብሔር በዚያ ሕዝቡን እንደሚጠብቃቸው እንዲያምን አስቻለው፤ ስለዚህም ምስጋናን ለማቅረብ ድል እስኪገኝ ድረስ መጠበቅ አላስፈለገውም፤ ድሉ በሚያስገኝለት ሙሉ ውጤት ከወዲሁ ሊቆም ቻለ፤ ሕዝቡ ገና ወደምድረበዳ በመግባት ላይ ቢሆኑም እምነት «በቸርነትህ የተቤዠሃቸውን ሕዝብህን መራህ፤ በኃይልህ ወደቅዱስ ማደሪያህ አገባሃቸው» ሊያስብላቸው እንደቻለ /ዘጸ15፡13/ እርሱም ከወዲሁ ሊያመሰግን ችሏል።

ነገር ግን ለጠላት በእጃቸው በጦር መሣሪያ ፋንታ የዜማ ዕቃ የተሸከሙ ሰዎችን ማየት ምንኛ እንግዳ ይሆን! ሕዝቅያስም በኋላ በጦር መሣሪያ ምትክ ማቅ ለብሶ ለጦርነት የተዘጋጀበት መርህም ከዚህ ጋር አንድ ነው/ኢሳ37፡1/፤ አዎ ሁለቱም አንድ ናቸው፤ ምክንያቱም ሁለቱም ሰዎች የሰለጠኑት በአንድ ትምህርት ቤት፣ ሁለቱም የተዋጉት ለአንድ ዓላማ ነበርና። ከነጠባዩ፣ ከነሥርዓቱ፣ ከነመመሪያው ከአሁኑ ዘመን ጋር በምናደርገው ፍልሚያ የእኛም ጦርነት እንዲሁ ይሁን፤ ከሁሉም በላይ «የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ማጥፋት የምንችልበትን የእምነት ጋሻ እንያዝ»፤

አክአብን ተከትሎ በሬማት ዘገለአድ በነበረውና ከጌታ ጋር በጠላቶቹ በሞዓባውያን ላይ በወጣው ኢዮሣፍጥ መካከል ያለው ልዩነት ምንኛ ታላቅ ነው! በእያንዳንዱ ገጽታው ምንኛ የተለየ ነው! የጌታን እርዳታና ምሪት የፈለገበት አኳኋንና መንገድም ይለያል፤ ጦርነቱን የመራበት መንገድም

*(ወደ ገጽ 18 ይዞራል)*

## ኢዮሣፍጥና ...ከገጽ 17 የዞረ

ይለያል፤ አቤት ፍጻሜውም ምንኛ ይለያል! በጠላት ተከብቦ በተስፋ መቁረጥ በመጮኽ ፊንታ ሳይዋጋ ድል የሰጠውን፣ ጠላቶቹ እርስ በእርሳቸው እንዲጠፋፉ ያደረገውን፣ በምሕረቱ ከጨለማው የአኮር ሸለቆ አውጥቶ ወደ በረከት ሸለቆ ያመጣውን የአባቶቹን አምላክ ዝማሬ ዘመረ፤ የተባረከ ልዩነት! ይህም እኛን ሙሉ በሙሉ በመለየት ኅዳናና በጌታ ጸጋ ታማኝነት ላይ በዘላቂነት ወደመደገፍ ይምራን፤ የበረከት ወይም የምስጋና ሸለቆ የእግዚአብሔር መንፈስ እኛን የሚመራበት ቦታ ነው፤ ነገር ግን ከዚህ ዓለም አክአቦች ጋር ከተባበርን የእነርሱን እቅድ ለመፈጸም ወደዚያ አይመራንም፤ «ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ፤ ርኩሱንም አትንኩ ይላል ሁሉንም የሚገዛ ጌታ፤ እኔም እቀበላችኋለሁ፤ ለእናንተም አባት እሆናለሁ፤ እናንተም ለእኔ ወንድ ልጆችና ሴት ልጅ ትሆናላችሁ» /1ቆሮ6፡17-18/ ተብሏልና፡፡

ዓለማዊነት የምስጋናን መንፈስ የሚያጠፋበት መንገድ አስደናቂ ነው፤ እንዲህ ላለው መንፈስ ሙሉ በሙሉ ጠላት ከመሆኑም ባሻገር ከተገባበት ወደጥልቅ ኹከት ነፍስን ይመራታል፤ ወይም ፈጽሞውኑ ወደለየለት ግልጽ ክህደትና ሁሉንም መልካም ነገሮች ወደመተው ይከተናል፤ ኢዮሣፍጥን በተመለከተ የደረሰበት የመጀመሪያው ነው፤ በመዋረድ እንዲመለስ ሆነ፤ ወደሚበልጥም በረከት ገባ፡፡

ነገር ግን ፍጻሜዬ እንደዚያው እንደኢዮሣፍጥ ይሆናል ብሎ ተስፋ በማድረግ አንድ ሰው ወደ ዓለማዊነት ቢገባ በእርግጥ አሳዛኝ ነው፤ ይህ ከልክ ባለፈ ከንቱ ድፍረት የተሞላ ተስፋ ነው፤ በኃጢአት የተሞላ ምኞት! ንጹሕ፣ ዝግ ያለና ሰላማዊ የሆነ አካሄድን የሚያደንቅ ነገር ግን እንዲህ የሚያስብ ማን ነው? «ጌታ የሚያመልኩትን እንዴት ከፈተና እንደሚጠብቅ ያውቃል»/2ጴጥ2፡9/፤ ታዲያ ራሳችን ሆን ብለን ራሳችንን ወደፈተና እናግባን? እግዚአብሔር ከዚህ ይጠብቀን፡፡

አዎ የሰውን የልቡን ክፉ ሐሳብ ጥልቀት ማን ያውቃል? የተወሳሰቡ እንቆቅልሾቹን ማን ይፈታል? እንዲህ ያለ ከባድ ትምህርት ከተማረ በኋላ ኢዮሣፍጥ ዳግመኛ የከሐዲዎችን ፍላጎት ሊፈጽም ወይም ከልክ ያለፈ ስስታቸውንና እቅዳቸውን ሊተባበር ይችላል ብሎ ማን ያስባል? ከገዛ ልቡ ምንነት አንዳች የተማረ ሰው ካልሆነ በቀር ማንም ይህ ይሆናል ብሎ አይገጠምትም፤ ይሁን እንጂ እርሱ አድርጎታል፤ «ከዚህም በኋላ የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ ሥራው እጅግ ክፉ ከሆነ ከእሥራኤል ንጉሥ ከአካዝያስ ጋር ተባበረ፤ ወደተርሴስም የሚሄዱትን መርከቦች ያሠሩ ዘንድ አንድ ሆኑ፤ መርከቦቹንም በዔጽዮንጋብር አሠሩ፤ የመሪሳም ሰው

(ወደ ገጽ 20 ይዞራል)

## ዳግመኛ ...ከገጽ 11 የዞረ

አእምሮ በላይ የሆኑ ነገሮችን በእምነት ለመቀበል የሚያስችል ነገር ነው፡፡ መለኮታዊና መንፈሳዊ ጠባይ ያላቸውን የእግዚአብሔርን ሥራዎች ስለተነገረን ወይም ስለተማርን ብቻ የምንቀበላቸው ነገሮች ናቸው፤ ስለዳግመኛ መወለድ እየተናገረ ያለው እርሱ ኢየሱስ ነው፤ እርሱ ደግሞ የሚናገረው ሰማያዊ ነገር ነው፤ ኒቆዲሞስ ሊያውቀውና ሊገባው ባይችልም ኢየሱስ ግን የሚናገረው የሚያውቀውን ነው፤ የሚመሰክረውም ያየውን ነው፡፡ እንዲህ ለማለት የሚያስችለው የእርሱ የኢየሱስ ማንነት ነው፤ እርሱ በሰማይ የሚኖር የሰው ልጅ ነው፤ በኒቆዲሞስ ፊት ሆኖ በሰማይ በአባቱ እቅፍ ያለ አምላክ ነው፤ ይህን የተረዳ ደቀመዝሙር ኢየሱስ የሚናገረውን ሁሉ እውነት ነው ብሎ ለማመንና ለመቀበል ልቡን ይከፍታል፤ ዳግመኛ መወለድ በሥጋ ዓይን ሳይታይ በመንፈሳዊ መንገድ የሚከናወን ቢሆንም ኢየሱስ ያስተማረው ትምህርት ስለሆነ በእርግጥም እውነት ነው፡፡

አንተስ አንባቢ በዘመንህ የእግዚአብሔርን ቃል ምን ያህል ጊዜ ሰምተሃል? ለሰማኸውስ ቃል ከእምነት የሚነሣ መታዘዝን አሳይተሃልን? ካላሳየህ ለምን ዘገየህ? ዘመንህ እንደሣር አበባ ወይም ጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፍዋለት መሆኑን

(ወደ ገጽ 20 ይዞራል)

## የጥያቄዎቻችሁ... ከገጽ 16 የዞረ

ይወደው እንደ ነበር እዩ» ብለው ነበር /ዮሐ11፡36/፡፡ ስለዚህ ከፍቅራችን የተነሣ እያለቀስን ሙታኖቻችንን ልንቀብር እንችላለን፤ ከዚህ በተረፈ ግን መሪር ወደ ሆነ ኀዘን መግባት የትንሣኤን ተስፋ መዘንጋት ነው፤ የሙታን መታሰቢያ ወይም ተዝካር መደገስም ሆነ ሐውልት ማቆም በኢአማንያን ዘንድ የተለመደ ሥራ ነው፡፡ ሐውልት መሥራቱንና የሐውልት ምርቃቱን አንቺ ያልሻቸው ሰዎችም በአንዳንድ ቦታዎች እየተቃወሙ መሆኑ ይሰማል፡፡ ኢየሱስ የግብዞች ሥራ አድርጎ የተቃወመውን ይህን ተግባር አማኞች አይፈጽሙም /ማቴ.23፡29/፤ ባጠቃላይ ይህ የክርስቲያኖች ልማድ ሊሆን አይገባም፡፡ ሆኖም ክርስቲያኖች ነን እያሉ በሚችስም ተዝካር የሚደግሱ ሐውልት የሚያቆሙ ወገኖች ይህንን የሚያዝዝ ምንም ዓይነት መጽሐፍ ቢኖርም ያ መጽሐፍ ሰይጣን ሰዎችን በሙታን መታሰቢያ ለማጥመድ የሚጠቀምበት መጽሐፍ መሆኑን አውቀው ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ሊመለሱ ይገባል፤ አንቺም እኅታችን ያን የስህተት መጽሐፍ ለማወቅ ያለሽን ፍላጐት አቁመሽ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሕይወት የሚናገረውን እውነት ለማወቅ እንድትተጊ እንመክርሻለን፤ እኛም የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት የማቅረብ አላማ ብቻ ነው ያለን፡፡ የክርስቲያኖች መጽሐፍ «መጽሐፍ ቅዱስ» ብቻ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል፤ ሌላው ሁሉ የሰው ሀሳብና የፈጠራ ድርሰት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያብራሩ ጽሑፎችም በማብራሪያነታቸው ከመርዳት በቀር ቋሚ መመሪያ/ሥርዓት/ በመሆን የሚያገለግሉ አይደሉም፡፡

2. በሁለተኛ ደረጃ እኅታችን ያቀረብሽው ጥያቄ ደግሞ ጾምን የሚመለከት ነው፤ በመሠረቱ ጾም መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን አንዱ ክርስቲያናዊ ሕይወት ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ራሱ 40 ቀንና 40 ሌሊት ጾሟል/ማቴ4፡1-2፤ሉቃ4፡1-2/፤ በተጨማሪም ሰይጣን በጾምና በጸሎት እንደሚወጣ ጌታ ተናግሯል /ማቴ17፡21፤ ማር9፡29/፤ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖችም ይጦሙ ነበር /የሐ.ሥ.13፡2-3/፤ ስለሆነም ክርስቲያን ከጸሎት ጋር በጾም ወደ ጌታ ሊቀርብ ይገባዋል፡፡ ሆኖም ሳምንታዊም ሆነ አመታዊ የጾም ጊዜያት እንዲኖሩ በጌታም ሆነ በሐዋርያት የታዘዘና በመጽሐፍ ቅዱስ ተደንግጎ የተመዘገበ ነገር የለም፡፡ በጉባዔ ደረጃ ሁሉም የአጥቢያ ጉባዔ አባላት እንዲጾሙ ቢያስፈልግ ወንድሞች ተመካክረው ጾም ሊታወጅ ይችላል፤ በየግልም አማኞች በራሳቸው ፕሮግራም መሠረት ሊጾሙ ይችላሉ፡፡ ጾም አንድ ግልጽ ምክንያትን መሠረት በማድረግ የሚፈጸም ተግባር ነው፡፡ ለምሣሌ በንስሐ ወደ ጌታ ለመቅረብ፣ የሰይጣን ፈተናን ለመቋቋምና ለመዋጋት፣ ልንወጣው በማንችል ችግር ውስጥ ስንሆን፣ ከጌታ መፍትሔን ለመጠየቅ፣ ስለ ሌሎች ወገኖች ለመማለድ፣ ስለ በሽተኞች ለመጸለይ .... ወዘተ ሲፈለግ ከጸሎት ጋር የሚፈጸም ጾም ልንጾም እንችላለን፡፡

ሰባቱ «አጽዋማት» ተብለው ከሚቆጠሩት ውስጥ ዓቢይ ጾም /ሁዳዴ/ ወይም ጾመ ኢየሱስ እየተባለ የሚጠራው በመጽሐፍ ቅዱስ ይገኝ የለም ወይ? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኢየሱስ 40 ቀንና 40 ሌሊት እንደ ጾመና በሰይጣን እንደተፈተነ ተጽፏል እንጂ ክርስቲያኖች በየዓመቱ የኢየሱስ ጾም እያሉ እንዲጾሙ አልታዘዘም፤ ኢየሱስ ራሱም አንድ ጊዜ ከጾመው በኋላ እስኪሰቀል ድረስ በኖረባቸው 3 ዓመታት ውስጥ በየዓመቱ አልጾመውም፤ ሐዋርያትም ኢየሱስ

(ወደ ገጽ 19 ይዞራል)

**ጥያቄዎቻችሁ...** ከገጽ 18 የዞረ

ከገጽ 18 የዞረ

የጸመውን ጾም በየዓመቱ እንጹም ብለው አልጾሙም፤ ሌሎች እንዲጾሙም አላስተማሩም፤ ይህ በኋላ ዘመን በሰው ሥርዓት የተወሰነና የተጨመረ ነው፤ ረቡዕና ዓርብንም በየሳምንቱ ጹሙ የሚል ትእዛዝ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም፤ ረቡዕ ምክረ አይሁድ የተፈፀመበት ዓርብ ጌታ የተሰቀለበት ስለሆነ እንጾማለን የሚለውም የሰው ሀሳብ ነው እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም፤ ጾመ ነነዌ የሚባለውን የ3 ቀን ጾምም በነነዌ ሰዎች ታሪክ ለማስታከክ ቢሞከርም በየዓመቱ የሚጾም መደበኛ ጾም እንዲሆን አልታዘዘም፤ ታሪኩ የሚገኘው በትንቢተ ዮናስ ም3 ውስጥ ሲሆን የነነዌ ሰዎች በዮናስ ስብከት አምነው ንስሐ በገቡ ጊዜ ለ3 ቀናት ያህል እንደጾሙ እና የእግዚአብሔር ምሕረት እንደተጠ ደረገላቸው ያስረዳል፤ ሆኖም እንኳን በአዲስ ኪዳን በዚያው በብሉይ ኪዳን ዘመንም እንኳ ዓመታዊ ጾም አልነጠ በረም፤ የገና ጾም /ጾመ ነቢያት/፣ የሰኔ ጾም/ጾመ ሐዋርያት/፣ ጾመ ፍልሰታና ጾመ ገሃድ/ጋድ/ የሚባሉትም በመጽሐፍ ቅዱስ ፈጽሞ የማይታወቁና በሰዎች የተደነገጉ ሥርዓቶች ናቸው:: ጌታ ኢየሱስ ስለሽማግሌዎች ወግ ብለው የእግዚአብሔርን ቃል የሻሩትን ሰዎች «እናንተ ግብዞች ኢሳይያስ ስለ እናንተ ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፤ ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው፤ የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል ብሎ በእውነት ትንቢት ተናገረ» ብሏቸዋል/ማቴ15:7-9/:: ከዚህ አንፃር ሲታይም በሰው ሥርዓት የተመሠረቱትን አጽዋማት በመጾም ለጌታ የሚቀርብ አምልኮ ከንቱ አምልኮ ነው፤ ልብን ከጌታ አርቆ አፍአዊ ሥርዓትን መፈጸም ኢየሱስ እንደተናገረው ግብዝነት ነው:: በመሆኑም በክርስቶስ ደም የተዋጀች ነፍስ ከሰው ሥርዓት ፈ

# ጸጋው ሲጎድል

በጉልበት አይሆን በጥረት
በእንባ በለቅሶ በስለት
በጾም በጸሎት በስግደት
ድህን በመርዳት በማብላት
ያለንን ሁሉ በመስጠት
በአንድ እግር መቆም ለዓመታት
ዳገት ቁልቁለት በመውጣት
በአማላጅ በኩል ለመግባት

በሥጋ ጥበብ በሥጋ ዘዴ
እግር እያለ መዳህ በዳዴ
ጽድቅ የለም እና ከቶም ደኅንነት
ከሞት አምልጠ ሕይወትን ማግኘት
ይልቅ ለሕይወት
ለሕያው እውነት
ለማይኳደል ቅዱስ ደኅንነት
ለማይሸረፍ የኀሊና ዕረፍት
«ጸጋው» ነው እውነት
የ'ውነት ደኅንነት
ጉልበት ጨርሶ አቅምን አጥቶ
ልብ ተወግቶ ኅሊና ሻግቶ
ደክሞ ቆዝሞ ሁሉን ሰጥቶ
ተስፋ ሲነጥፍ ጉድለት ሲበዛ
ክፍተት ሲፈጠር ኑሮ ቢንዛዛ
ሥጋ መንፈስን አስሮ ሲገዛ
ምሬት ይነግሣል
ተስፋ ይነጥፋል
ጭንቅ ይበረታል
ኃጢአት ያይላል
ክፋት ይነግሣል
ፍቅር ይጠፋል
እምነት ይደክማል
ጠላት ያቅራራል
ሞት ይፎክራል

*ጸጋ ሲጎድል ............*
ልብ ያመነታል
ግራ ይገባል
መንገድ ይጠፋል
ሰላም ይታጣል

*ጸጋው ሲጎድል...........*
እውነት ከስህተት ይመሳሰላል
ዓመፃ ከጽድቅ ይደባለቃል
ዘፈን ከመዝሙር ይቀላቀላል
ይስሐቅ ከእስማኤል
ተስማምቶ ያድራል
በቤተመቅደስ ንግድ ይደረጃል
ቀን ይዘመራል ሌት ይደነሳል
ያለም ጥላዋ መቅደስ ይታያል
የፌዝ አምልኮን
ልብ ይናፍቃል
ሐቅ አልባ ተረት
ጆሮን ይሞላል

*ጸጋ ከሌለ......*
.
ማን ይበረታል
ማን ያንቀላፋል
ማን ይፀልያል
ማን ይፈወሳል
ማን ቆሞ ይሄዳል
ማን ይዘምራል
ማን ያስተምራል
ማን ያዳምጣል
ፀጋው ነው ድሉ
የእምነት ደውሉ
የተስፋ ቃሉ
የጽድቅ አክሊሉ
እዚያ ነው ትግሉ
የድል ምስጢሩ
የህይወት ክብሩ
የኅብረት ድሩ
የፍቅር በሩ
ጸጋው ነው ምክሩ
የድል ምስጢሩ
የሐቅ ሥሩ
ሥር መሠረቱ
ጽኑ አለቱ
ኃይል ጉልበቱ
ጸጋው ነው በሩ
የኛ ድንበሩ

| መጽሐፍ ቅዱሳዊት አጥቢያ ቤተክርስቲያን | በሰው የተደራጀች አጥቢያ ቤተክርስቲያን |
|---|---|
| 1. በሰማያዊ ራስ በክርስቶስ ትመራለች:: | 1. በምድራውያን ራሶች ትመራለች:: |
| 2. ተጠሪነቷ ለክርስቶስ ብቻ ሲሆን የየትኛውም ሌላ አጥቢያ ቅርንጫፍ አይደለችም፤ እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ለሰማያዊ ራሷ ቀጥተኛ ተጠሪነት አላት:: | 2. ተጠሪነቷ እንደየሥልጣን ተዋረዱ ለሚመሯት ባለሥልጣናትና ቢሮዎች ነው፤ ከዋና ከተማ ጀምሮ በየደረጃው ከክፍለሀገር እስከ ወረዳ ላሉት የበላይ አካሎቿ ቅርንጫፍ ናት:: |
| 3. አንድነቷ የተመሠረተው 66ቱ ቅዱሳት መጻሕፍት በሚናገሩት ትምህርት ላይ ባለ ሙሉ እምነት ነው:: | 3. እርስ በእርሷ ያላት አንድነት የተመሠረተው አባሎቿ በጋራ በሚቀርጹት መተዳደሪያ ደንብ፣ በጋራ በሚስማሙበት የእምነት መግለጫ ወይም ዶክትሪን ነው:: |
| 4. ከሌሎች አጥቢያዎች ጋር ያላት ግንኙነት በፍቅርና በወንድማማችነት ላይ የተመሠረተ ነው:: | 4. እርስ በርሷ የምትገናኝው በማኅተም፣ በበላይ ባለሥልጣናት ፊቃድና ፊርማ ወይም በጋራ በምታዋቅረው ኮሚቴ ይሆናል:: |
| 5. የምትሰበሰበው በኢየሱስ ስም ብቻ ነው:: | 5. የምትሰበሰበው ቅርንጫፍ በሆነችበት ድርጅት ስያሜ ወይም መሥራቾቿ ተሰብስበው በመረጡላት ስያሜ ነው:: |
| 6. አገልጋዮቿ መንፈስ ቅዱስ በጸጋ የሚገልጣቸው ናቸው:: | 6. የሚያገለግሏት በበላይ ኃላፊዎች የተሾሙ፣ በቢሮዎች የሚመደቡ፣ ከማሰልጠኛ ተቋማት ተመርቀው የሚቀጠሩ፣ ወይም በድምፅ ብልጫ የሚመረጡ ናቸው:: |
| 7. የጸሎትና የአምልኮ ጉባኤዎቿ በመንፈስ ቅዱስ ብቻ ይመራሉ፤ አባሎቿ በሙሉ የካህናትነት መብታቸውን ሥራ ላይ ያውላሉ:: | 7. የአምልኮና የጸሎት ስብሰባዎች የግድ አስቀድሞ በተደነገገ መንገድ በተመደቡ ሰዎች የሚመሩ ናቸው፤ አባሎቿ በሙሉ የካህናትነት መብታቸውን ካለማወቃቸው የተነሳ አይገለገሉበትም፤ የሚያውቁትም እንዲገለገሉበት የሚያስችላቸው ሁኔታ የለም:: |

## ኢዮሣፍጥና ... ከገጽ 18 የዞረ

የዶዳያ ልጅ አልዓዛር ከአካዝያስ ጋር ተባብረሃልና እግዚ አብሔር ሥራህን አፍርሶታል ብሎ በኢዮሣፍጥ ላይ ትንቢት ተናገረ፤ መርከቦቹም ተሰበሩ ወደ ተርሴስም ይሄዱ ዘንድ አልቻሉም»/20፡35 -37/። ሰው ምንድነው? ምስኪን፣ ተሰናካይ፣ ወዳቂ፤ ተጠራጣሪ ፍጥረት፤ ሁሌም ወደአዲስ ሞኝነትና ክፋት የሚሮጥ! ኢዮሣፍጥ አስቀድሞ ከአክአብ ጋር በመግጠሙ ከደረሰበት ውድቀት ገና ከመመለሱ ብዙም ሳይቆይ ከአካዝያስ ጋር ገጠመ፤ ከሶርያውያን ቀስት ያመለጠው በብዙ ችግር ማለትም በጌታ ልዩና እጅግ የበዛ የርህራኄ ጣልቃገብነት ነው፤ እናም ዳግመኛ ከእስራኤልና ከኤዶም ነገሥታት ጋር ህብረት ፈጥሮ ሞዓባውያንን ሊዋጋ ሲል እናገኘዋለን።

ኢዮሣፍጥና ለየት ያለ መንገዱ እንዲህ ያለ ነው፤ ነገር ግን የተወሰነ «መልካም ነገር ተገኝቶበታል»/19፡3/፤ ወጥመዱ ግን ዓለማዊ ህብረት ነው፤ የእርሱንም ታሪክ ከማጥናት የምንማረው ትምህርት ያንን ክፋት አውቆ መጠበቅ ነው፤ ያለማቋረጥ «ውጡና የተለያችሁ ሁኑ» የሚል ድምፅ በጆሮአችን ላይ ልንሰማ ያስፈልገናል፤ በነፍሳችን መከራ ሳይገጥመንና ምስክርነታችን ሳይበላሽ በማናቸውም መንገድ ከዓለም ጋር ራሳችንን ቀይጠን በእርሷም መርሆዎችና አመለካከቶች ልንመራ ፈጽሞ አንችልም።

በማጠቃለያው ማስገንዘብ የምንፈልገው አንድ ነጥብ «ኢዮሣፍጥ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ» የሚለውን ማንበብ ለመንፈስ እፎይታን የሚሰጥ መሆኑን ነው/21፡1/፤ ምክንያቱም በስተመጨረሻ ኢዮሣፍጥ የጠላት ወጥመድና መሣሪያዎች ከማይደርሱበት ስፍራ መሄዱን እርግጠኝነት ስለሚሰማን ነው፤ በተጨማሪም «በጌታ የሚሞቱ ሙታን ብፁዓን ናቸው፤ ከድካማቸው ያርፉ ዘንድ» /ራእ14፡13/ በሚለው የመንፈስ ቡራኬ ውስጥ ገብቶአልና አዎ ከግጭት፣ ከወጥመድና ከፈተና ሁሉ አርፎአል። ■

## ዳግመኛ ...ከገጽ 18 የዞረ

ዘነጋኸውን? የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሽ ለመሆን አትፈልግምን? ለዚህም ትበቃ ዘንድ አሁኑኑ ለእግዚአብሔር ቃል አዎንታዊ ምላሽ ስጥ። በዚህ ዓይነት በእምነት ብትታዘዝ በዳግመኛ መወለድ የእግዚአብሔር ልጅ የመሆን ሥልጣን ከጌታ ትቀበላለህ፤ በመንግሥቱም ውስጥ ስፍራ ይኖርሃል። ለዚህም ጌታ ይርዳህ ። ■

## አዳዲስ መጻሕፍት

### በቅርብ ቀን ለንባብ የበቁ

1ኛ. የመጽሐፈ ሩት ትርጓሜ
2ኛ. የእውነትን ቃል በአግባቡ መለየት

## ከዝግጅት ክፍሉ

«እውነት» ጋዜጣንም ሆነ በአሳታሚው የሚታተሙ ለሌሎች መንፈሳዊ መጻሕፍትን ለማንበብ የሚፈልግ ሁሉ ዋጋ እንዲከፍል ሳይጠየቅ ፍላጎቱን በመግለጥ ብቻ ሊያገኝ ይችላል፤ አገልግሎቱ ሙሉ በሙሉ በበጎ ፈቃድ የገንዘብና የእውቀት አስተዋጽዖ የሚካሄድ የጸጋ አገልግሎት ነው፤ በዚሁ መልክ ጋዜጣውንም ሆነ ሌሎችን መጻሕፍት ለብዙዎች ማዳረስ እንድንችል እግዚአብሔር ልቡን ያነሳሳው አማኝ በፖስታ ቤት በሐዋላ ለአሳታሚው የገጠ ንዘብ አስተዋጽዖውን መላክ ይችላል።

እግዚአብሔር በጸጋ ያለዋጋ ከሰጠው የቃሉ ማዕድ ተካፋይ ለመሆን የምትሹ ሁሉ የሚከተሉትን ኅትመቶች በመጻጻፍ ማግኘት የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን፤

1. ደብተራ ኦሪት
2. መካነ ኅሩያን
3. የዕብራውያን መልእክት ትርጓሜ
4. ጦማረ ጽድቅ
5. የኦሪት ዘፍጥረት ትርጓሜ
6. መንፈስ ቅዱስ አካል ያለው መለኮት
7. የአዲስ ኪዳን መካከለኛ
8. የኦሪት ዘጸአት ትርጓሜ
9. መጽሐፈ ሰዓታት በመቅደሱ ሚዛን
10. መጽሐፈ ሩት ትርጓሜ
11. የእውነትን ቃል በአግባቡ መለየት ናቸው።

መጻሕፍቱንም ሆነ ጋዜጣውን ለማግኘት በአሳታሚው አድራሻ በመጻፍ ይ ጠይቁ፤ ወይም በሚከተሉት ስልክ ቁጥሮች ይደውሉ፤

ከዚህ ቀደም ከእነዚህ መጻሕፍት በከፊል ተጻጽፋችሁ ያገኛችሁ አንባቢያን መ

| | | | |
|---|---|---|---|
| አሰላ | 02-311312 | አዲስ አበባ | 01-774677 |
| ጎባ | 06-611373 | በደሌ | 07-450365 |
| ደ/ብርሃን | 01-813147 | ዲላ | 06-310384 |

ጠየቅ የምትችሉት ያልደረሷችሁን መጻሕ ፍት ብቻ መሆኑን እንገልጻለን፤

COPY RIGHT© BGNLJ

`EUNET´ IS PUBLISHED BY : BGNLJ
NON PROFIT ORGANIZATION DEVOUTED TO THE PROPAGATION OF BIBLE TRUTH, P.O.Box 14787, ADDIS ABABA, ETHIOPA

ላኪ/SENDER

BGNLJ
ፖ. ሣ. ቁጥር 14787
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

BGNLJ
P.O.Box 14787,
ADDIS ABABA, ETHIOPA.

ለ/To

ቴምብር